

ከጠባሳው በስተጀርባ ...

ገጽ 18



አሳሳቢው የቢሮ ህንጻ ኪራይ ወጪ

ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 119 ታኅሣሥ 29 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትሪያርክ



ብፁእ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ



ፓስተር ጻዲቁ አብዶ



ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ

# ምዕመናን በዓሉን የተጎዱ ወገኖችን በመደገፍ እንዲያከብሩ የኃይማኖት አባቶች አሳሰቡ

**ሄለን ወንድምነውና ዳግማዊት ግርማ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ሲያከብር በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች በመደገፍ ሊሆን እንደሚገባ የኃይማኖት አባቶች አሳሰቡ፡፡ አባቶቹ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ የተገኘው የሰላም ጅማሮ ወደሙሉ ሰላም እንዲሸጋገር ሁሉም አካላት የድርሻቸውን እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስ አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የልደት በዓልን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ሁሉ በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች በተለመደው የመተጋገዝ ቅዱስ ባህል መሰረት እርስ በርስ በመረዳዳት በዓሉን ሊያከብሩ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተከሰተው አለመግባባት በአጠቃላይ በሕዝቡ ላይ የደረሰው ስብራት ከባድ መሆኑን ያወሱት አቡነ ማቲያስ፤ የዓለም ማኅበረሰብ የተቻለውን ድጋፍ ሁሉ በማድረግ ሕዝቡን እንዲያግዝ፣ መንግሥትና ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች የተጀመረው የሰላም ጉዞ እንዳይቀለበስ በከፍተኛ ኃላፊነት እንዲሠሩ አሳስበዋል፡፡

ብፁዕነታቸው፣ የተገኘው የሰላም ተስፋ ወደፍጹም አስተማማኝ ሰላም በምሉዕነት እንዲያድግ ሁሉም በኃላፊነት ሊሰራ ይገባል ሲሉ በአጽንዖት ገልጸዋል፡፡

ምዕመናን.. ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የደብረ ማርቆስ አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ግንባታ 25 በመቶ ደርሷል

**ሄለን ወንድምነው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የደብረ ማርቆስ አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ የግንባታ ሥራ 25 በመቶ መከናወኑን የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ዘየደ አበራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ግንባታው ጥር ወር 2014 ዓ.ም የተጀመረው የአየር ማረፊያ ግንባታ ሥራ የመሬት ማስተካከል ሥራ በተያዘለት የጊዜ ገደብ መሠረት እየተከናወነ ይገኛል።

ዋነኛው የአፈር የጠረጋ ሥራ 85 በመቶ ደርሷል። የአፈር ቆረጣውና ሙሌት ሥራዎች ደግሞ እያንዳንዳቸው 60 በመቶና 30 በመቶ ደረጃ ተከናውነዋል ሲሉ አስታውቀዋል።

እንደ ኢንጅነር ዘየደ ገለጻ፤ ለፕሮጀክቱ የኮንስትራክሽን ወጪ ከ505 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት መመደቡን የገለጹት ኢንጂነር ዘየደ፤ አውሮፕላን ማረፊያው ግንባታ በ153 ሄክታር መሬት ላይ እየተከናወነ ይገኛል።

የግንባታው ዋና የሥራ ክፍል የመሬት ቆረጣና የአፈር ሙሌት እንደሆነ የገለጹት ኢንጅነር ዘየደ ፤ይህም በዕቅዱ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።

የደብረ ማርቆስ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








አቶ ቢራራ መለሰ

# ኅብረተሰቡ በበዓላት ወቅት ለጤና እክል ከሚሆኑ የአመጋገብ ሥርዓቶች እንዲጠነቀቅ ጥሪ ቀረበ

**ሄለን ወንድምነው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ኅብረተሰቡ በበዓላት ወቅት ለጤና እክል ከሚሆኑ የአመጋገብ ሥርዓቶች ሊቆጠብ እንደሚገባ የጤና ሚኒስቴር አሳሰበ፡፡

ኅብረተሰቡ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “የልደት በዓል መለያየት የጠፋበት፣ ኅብረትና አንድነት የጸናበት ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል መለያየት የጠፋበት፣ ኅብረትና አንድነት የጸናበት ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) አስታወቁ። ለመላ የክርስትና እምነት ተከታዮችም ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በመልዕክታቸው እንዳሰፈሩት፤ በክርስቲያኖች ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የዕርቅ መጀመሪያ ተደርጎ ይታሰባል። ከልደቱ በፊት በፈጣሪና በፍጡር፣ በሰማይና በምድር፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ታላቅ የጠብ ግድግዳ ተገንብቶ ለብዙ ዘመናት ቆይቷል።

የልደት በዓል “ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ” የሚለው የፈጣሪ ቃል በተግባር መፈጸም የጀመረበት፤

“የልደት.. ወደ ገጽ 4 ዞሯል










የዲፕሎማሲ ሥራችንን ተሻጋሪ ስምና ዝና ካላቸው ተቋማት ጋር ማቀናጀት እንደሚገባ ተገለጸ

ገጽ 3

ዜና

# ከአራት ሺህ በላይ እንስሳት ዕርድ ለመፈፀም ዝግጅት ተደርጓል

ገመቹ ከድር


ፋይል

አዲስ አበባ ፡- በበዓሉ ከአራት ሺህ በላይ እንስሳት እርድ ለማከናወን አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጋቸውን የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት እና ከአዲስ አበባ ሉካንዳ ነጋዴዎች ማኅበር አስታወቁ፡፡ ኅብረተሰቡ ሕገ ወጥ እርድ ለመከላከል የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

አዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት አስተባባሪ አቶ አትክልት ገብረሚካኤል በጽሕፈት ቤታቸው ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት ፤ ድርጅቱ ንጽሕናውን የጠበቀ የዕርድ አገልግሎት ለመስጠት ተገቢውን ዝግጅት አድርጓል።

የእርድ ሂደቱ ቅድመ እና ድህረ ዕርድ ምርመራዎችን በማድረግ ጤንነቱ በባለሙያ ከተረጋገጠ በኋላ ለኅብረተሰቡ እንደሚሰራጭ ገልጸዋል። ይህንን ለማድረግ ከሠራተኛው ጋር መግባባት ተደርሷል፣ለዕርድ የሚሆኑ ግንባታ እና ለማሰራጨት የሚያስችሉ የመኪናዎች ጥገናዎች ተደርጓል። ድርጅቱ እርድ አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ተረፈ ሥጋ ውጤቶች ወደ ተረፈ ምርት እንዲቀየሩ በማድረግ የአካባቢ ጥበቃ እያደረገ ይገኛል ፡፡

ኅብረተሰቡ ሕገወጥ እርድ ለመከላከል የበኩሉን አስተዋጽዖ ሊያደርግ ይገባል ያሉት አቶ አትክልት ባለፉት አምስት ወራት ብቻ 170 በጎች እና 35 ከብቶች በተደረገላቸው ቅድመና ድሕረ ምርምራ እንዲወገዱ ተደርጓል ብለዋል ፡፡

እንደ አቶ አትክልት ገለጻ፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሕገወጥ እርድ ምክንያት በዓመት አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ገቢ ያጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አካባቢ ብክለት ያስከትላል፣ ለእርባታ የሚሆኑ እንስሳት ለእርድ በማዋል የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ ሕጋዊ ቄራ እና ሕጋዊ ነጋዴዎችን በማዳከም ሰፊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ስለሚያስከትል ሁሉም ሕገወጥ እርድን መከላከል አለበት ብለዋል ፡፡

ለበዓሉ በርካታ እንስሳት ወደ ድርጅት እንደሚመጡ ገልጸው፣ ሦስት ሺህ ትላልቅ ከብቶች እና አንድ ሺህ የሚሆኑ ትናንሽ እንስሳት በድምሩ ከአራት ሺህ እንስሳት በላይ እርድ አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊውን ዝግጅት ማጠናቀቁን ገልጸዋል ።

አዲስ አበባ ሉካንዳ ነጋዴዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አየለ ሳህለ በበኩላቸው ማኅበሩ ኅብረተሰቡ የሚፈልገውን አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት ማድረጉን ገልጸዋል።

ማኅበሩ የኅብረተሰቡን እና የአካባቢውን ጤንነት የጠበቀ እርድ አገልግሎት ለመስጠት በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ በቅድመ እና ድሕረ ምርመራ ውጤት መሠረት የሚወገዱ እንስሳትን ካሳ ለማኅበሩ አባላት በመክፈል ሕገወጥ ዕርድ ለመከላከል የበኩሉን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገልጸው ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ሕገወጥ እርድ ለመከላከል የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በተስፋ - አዲስ ብርሃን የፈነጠቀላቸው የካንሰር ታማሚ ሕፃናት

ዳግማዊት ግርማ


ፎቶ፡- ሐዱስ አብርሃ

ሕይወት አንዴ ብቻ የሚገኝ ብርቅ ስጦታ ነው። በዚህ የመኖር ሂደት ውስጥ በሕይወት ኗሪ የሰው ልጅ ባለብዙ ዓይነት ትልልቅ ሸክሞች ባለቤት ይሆናል። ሁለተኛና ሦስተኛ፣ ታናሽና ታላቅ፣ ዘመድና ባዳ የሌለው የአንድ ጊዜ ዕድል ብቻ ነው መኖር። ባንዲት ኑረት ውስጥ ዝንታለም ለመኖር በመልካምነት ድልድይነት ላይ መመላለስ ያሻል፤ ከልብ መሰጠትም የዚሁ ሁነት አልፋና ኦሜጋ ነው። ደግ መሆን ወንዝ ያሻግራል፤ በማይፈርስ አንቱታ መንናጸፊያ ያስሞሽራል። በክፉት ወጥመድ ተለክፈው የሚኳትኑ በርከት ያሉ እንዳሉ ሁሉ በመልካምነት ምርኩዝ ዘመንን የተሻገሩ እልፍ ቅኖችም አሏት ይህቺ ዓለም።

ከውድማ በሚልቅ የሕይወት አዙሪት ውስጥ ባለ የመኖር ትንቅንቅ ነፍስያ መቸና እንዴት ከምድር ገፅ ላይ እንደምትሰረዝ ማወቅ አዳጋች ነው። በመኖር ረጅም ጉዞ ውስጥ ለነጎደና በበረታ ድካም ውስጥ ለከረመ ሁሉ፤ እንኳን ከተራራ ገዝፈው መላ አልባ ለሆኑ ጉዳዮች ከእፉየ ገላ የቀለሉቱ እንኳን አስትንፋስን ለመንጠቅ ግብ ግብ የገጠሙ ያህል አሳር እያስበሉ ሕይወትን ከመርግ ያከብዷታል። ሕይወት የመከራ ጅራፏን ገምዳ ግርፊያዋን የምታበረታው በብላቴንነት ዕድሜ ላይ ሲሆን ደግሞ ክብደቱ ቃል አጥቶ ይለያል።

ጨቅላነት የዕድሜ ንጋት ብርሃናትን ሰትሮ ተስፋን በልብ የሚያሰንቅ፤ የረጅም ጉዞዎች መነሻ ነጥብ ነውና ይህ የእምቡጥነት ወቅት ሰው በተስፋ የሚሞላበትን አድማስ ተሻግሮ ለመጨበጥ ልብ በጉጉት የምትቃትትበት የፍኖት አሃዱ ነው። በዕድሜ መባቻ ላይ የሚኖር ሰው የነገ ስንቁን ለመሰነቅ በብሩህ ተስፋም ለመጥገብ ከራስም በላይ የወላጅ ብርቱ ኃላፊነት ስር ኗሪ ነው። ልጅ አበባ ነው፤ ያለወላጅ ጥም አርኪነት የማይፈካ፤ ልጅ ተክል ነው አናትና አባት ካልደገፉት የሚጠወልግና የሚደርቅ፤ ልጅ ሁሌም በቤተሰብ የበረታ እንክብካቤ ከከፉ ተከልሎ የሚታለፍ ለጋነት ነው።

ልጆች ሲታመሙ የሚታመመው፣ ሲኃሳቆሉ የሚኃሳቆለው ወላጅ ነው። ህመም በበረታ ጊዜ፣ ያኔ ቤትን ጭንቅ ወርሶት፤ ታዛን ውድማ ይጋረጥበታል። ህመም በተለይ ደግሞ አሁን የምናወራለት ህመም ምህረትን አያውቅም። በክፍለዘመኑ የሰው ልጅን ሕይወት በመቅጠፍ የሚቀድመው የለም። የብዙዎችን ሕይወት ጨካኝ ጎራዴውን ከአፎቱ መዝዞ እየሰየፈ እልፎችን ወደ ጥልቁ ልኳል። የበሽታው ትልቁ ክፋት ደግሞ በሰዎች ውስጥ መኖሪያውን ከትሞ መኖሩ ሳይታወቅ ዓመታት ሊነጉዱ ማስቻላቸው ነው። በሽታው የመውለጃዋን ቀን እንደምትጠብቅ ነፍሰጡር የመሞቻ ቀንን አስቆጥሮ ወደ ሞት የሚገፋ አረመኔም ነው። እልፍ ሰዎች በቤተሰባቸው መሀል የካንሰር ተጠቂ ሲገኝ መግቢያ ምድር መውጫ መንገድ ይጠፉቸዋል።

እኛም ለዛሬ ይህ በሽታ ከሚያደርሰው ጉዳት ሸክም ተጋርቶ የሕይወትን መንገድ ለማቅለል ከሚተጋ አንድ ማዕከል ተገኝተናል። በካንሰር የተጠቁ ህፃናትን የሚንከባከበው የዚህ ማዕከል ማኅበራዊ ሠራተኛ ኃላፊ የሆኑትን ወይዘሮ ፋንቱ ሀዋዝን በማናገርም ተከታዩን ልናስቃኛችሁ ወደድን።

እግር ጥሎት ፒያሳን የሚያቋርጥ ይህን ቦታ የመጎብኘት እድል አያጣም። መመላለሻውን በሰባዎቹ ደረጃዎች ላይ ያደረገ ሰው ስፍራውን ያውቀዋል። በደረጃዎቹ አናት ላይ በኩራት ተጀቡኗል። የሰባ ደረጃን ዳገት ወጥቶ የጨረሰ ሰው የመንገዱ ፍፃሜ የዚህ መርጃ ማዕከል ደጃፍ ነው።

ድርጅቱ የአሥር ዓመት ዕድሜ ታዳጊ ነው። በኢትዮጵያውያን የጊዜ ቀመር በሁለት ሺህ አምስት ነው የተቋቋመው። የምሥረታው መነሻም እንዲህ ነበር፤ በካንሰር የተጠቃ ልጇን ለማሳከም የምትደክም አንዲት ልበ ቀና እናት ነበረች። ነዋሪነቷ በመዲናይቱ አዲስ አበባ ነው። ታማሚ ልጇን ለመፈወስ ብዙ ትንከራተት ነበር። ልጇን በማሳከም ላይ ሳለች የራሷን ልጅ መድኃኒት አስወግታ ለቀጣይ እያስፈለጋት ለሌሎች ታካሚዎች ትሰጥ ነበር። በዚህ የሕይወት ገጠመኟ ከክልል የሚመጡ ሰዎች የሚደርስባቸውን ችግር ለመገንዘብ ችላለች። ስለ ህመሙ የሚያውቀውን ማውጋት ይቀላልና ይህንን ችግር የተመለከቱ የህክምና ባለሞያዎችና ልጆቻቸውን አሳክመው የዳነላቸው ሌሎችም ቤተሰቦች ተጨምረው ‘ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድሁድ’ ድርጅት ተከፈተ።

ድርጅቱ ጅማሬውን በቡና ጠጡ ፕሮግራም አደረገ። ለታማሚና ቤተሰቦቻቸውም የሥነ- ልነቦና ምክር መስጠትም የስራው አካል ሆነ። እንዲህ እንዲያ እየተባለ የታማሚዎችን ልጆች በትራንስፖርት በማመላለስ እርዳታውን ቀጠለ። በጊዜ ሂደት ተስፋ አዲስ ታማሚ ህፃናቱን የሚመግብ፣ የሚያለብስ፣ የሚያጥብና የሚደግፍ ሆኖ ወደ ትልቅ ተቋምነት ተለወጠ።

የታማሚዎቹ ወላጆች ከልጆቻቸው ህመም ባልተናነሰ እልፍ ነገሮች በመንገዳቸው ላይ አሉ። የእነዚህ ህፃናት ወላጆች ልጆቻቸውን ለማሳከም የሚመጡት የሕይወትን ብዙ መሰናክሎች አልፈው ነው። ህክምናቸውን ከቀለሱት ሰፊ ጎጇቸው በሰው ባህር በተሞላችው አዲስ አበባ እየመጡ ህክምናቸውን ይከታተላሉ። ከዚህ ሁሉ ከባድ ጉዞ በኋላ ደግሞ በድህነት የሳሳው ኪሳቸው ለማረፊያ ታንሳለች። በዚህም ህክምናውን በአግባቡ ሳያገኙ እልፎች ሕይወታቸውን ለበሽታው ክፋት ይሰዋሉ።

ድርጅቱ ልጅን ከወላጅ ሳይነጥል ይደግፋል። በማዕከሉ ታማሚዎች በቀጠሮ ጊዜያቸው ከሚጎዱት ጉዳቶች ከልሎ ይይዛቸዋል። በአብዛኛው ከአዲስ አበባ ውጪ የሚመጡ ከመዲናይቱ ወገን የሌላቸው ልጆቻቸውን ማስጠጊያ ያጡ ዜጎች የድርጅቱ ደግ ጎን ተጋሪዎች ናቸው። ማረፊያቸውን በድርጅቱ የቀለሱ ህፃናት ህመም የደቆሳቸው፣ ከማይችሉት ህመም ትግል የገጠሙ ተስፋ እንደ ዳቦ የራባቸው ናቸው።

በዚህ ቤት እልፍ ቤተሰቦች እፎይታን አግኝተዋል። ምስጋና ለድርጅቱ ይሁንና ወላጆች የልጃቸው ህመም እንጂ ማረፊያ ማጣት የጭንቀታቸው አካል አልሆነም። በተስፋ አዲስ ውስጥ ወላጆች የልጆች ማረፍያ፣ ምግብ መድሃኒት ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ጉዳይ አያስጨንቃቸውም ምክንያቱም ድርጅቱ ነው የሚችላቸው። ልጆች በቀን አምስቴ ወላጆች ሶስቴ ይመገባሉ።

ድርጅቱ ትኩረቱን ከመርዳት ባሻገር ታማሚዎች ሰው አለኝ ጓደኛ ቤተሰብ አለኝ ብለው እንዲያስቡ በብዙ ይተጋል። እልፍ ባለ ቀና ልቦች ደስታና ኀዘናቸውን ከልጆቹ ጋር በማዕከሉ በመገኘት ያሳልፋሉ። ልደታቸውን በማዕከሉ የሚያከብሩም የትየለሌ ናቸው።


ረዳት ኮሚሽነር ሸዋይርጋ ግዛው


አቶ ክበበው ሚደቅሳ

# ጠጥቶ ማሽከርከር ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ዳግም ተጀመረ

በሪሁ አረጋ

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ተቋርጦ የነበረው ጠጥቶ የማሽከርከር ደምብን የመተላለፍ ቁጥጥር ዳግም መጀመሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡ በመዲናዋ በየዓመቱ ከ450 በላይ እግረኞች በትራፊክ አደጋ እንደሚሞቱም ገልጿል፡፡

በአዲስ አበባ ፖሊስ የትራፊክ ቁጥጥር መምሪያ ኃላፊ ረዳት ኮሚሽነር ሸዋይርጋ ግዛው እንደተናገሩት፣ በጠጥቶ ማሽከርከር ላይ የሚደረገው የቁጥጥር ሥራ ባለፉት ሁለት ዓመታት በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ተቋርጦ ነበር፡፡

ቁጥጥሩ በጠጥቶ ማሽከርከር ምክንያት የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ያሉት ረዳት ኮሚሽነሩ፤ ቁጥጥሩ የኮቪድ-19 የጥንቃቄ ፕሮቶኮሎችን በጠበቀ መልኩ እንደሚከናወንም ገልጸዋል።

ቁጥጥሩ እንዲከናወን የተወሰነው ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ እና ከጤና ሚኒስቴር ፈቃድ በመገኘቱ መሆኑን የጠቆሙት ኮሚሽነሩ፣ ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር በተመረጡ 40 ቦታዎች ላይ እንደሚደረግም ተናግረዋል፡፡

በጥንቃቄ ጉድለት በተለይ የደህንነት ቀበቶ እና የሞተር ብስክሌት ሄልሜት (ጭንቅላትን ከአደጋ የሚከላከል ባርኔጣ) አጠቃቀም የሚከሰት ትራፊክ አደጋ በከፍተኛ ሁኔታ ተሻሽሏል ብለዋል።

በመዲዋ በብዛት ለትራፊክ አደጋ የሚጋለጡና የሚጎዱት እግረኞች ሲሆኑ በየዓመቱ ከ450 በላይ ሰዎች እንደሚሞቱ የጠቀሱት ረዳት ኮሚሽነሩ፤ አሁን ላይ ችግሩን ለመቅረፍ ብሎም የቁጥጥር ሥራውን በብቃት ለማከናወን ልዩ ልዩ ግብዓቶች መሟላታቸውን ተናግረዋል።

የትራፊክ አደጋም በአመዛኙ በአምራች የእድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች ላይ በመሆኑ በተጎጂ ቤተሰቦችና በማኅበረሰቡ ላይ ከባድ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናን በማስከተል ላይ እንደሚገኝም ኮሚሽነር ሸዋይርጋ ጠቁመው፤ የትራፊክ አደጋዎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ ምላሽ ለመስጠት እና የሕግ ማስከበር ሥራዎችን ለማጠናከር በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ክበበው ሚደቅሳ በበኩላቸው በጠጥቶ ማሽከርከር ላይ ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችሉ በቂ ግብዓቶች መሟላታቸውን ገልፀው፤ በቀጣይም በቁጥር ውስንነት የሚታይባቸውን የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ለማሟላት እየተሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

አሽከርካሪዎች አልኮል ጠጥቶና ከፍጥነት ወሰን በላይ ባለማሽከርከር ሙያዊ ግዴታቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው ያሳሰቡት አቶ ክበበው፣ በተለይም ከገና በዓል ጋር ተያይዞ የአንድም ሰው ሕይወት በትራፊክ አደጋ እንዳይጠፋ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

የትራፊክ አደጋን ለመከላከል እግረኞችም ሆኑ አሽከርካሪዎች ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀም ሥነ-ሥርዓት መከተል እንዳለባቸው መክረዋል፡፡

# የኃይል አቅርቦት እንዳያጋጥም ከፍላጎት ጋር የሚመጣጠን 3 ሺ 500 ሜጋ ዋት ኃይል ዝግጁ ተደርጓል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ የኃይል አቅርቦት እንዳያጋጥም ከፍላጎት ጋር የሚመጣጠንና ተጨማሪ 3 ሺ 500 ሜጋ ዋት ኃይል ዝግጁ መደረጉን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኃይል አቅርቦቱ አስተማማኝ እንዲሆን የሚያስችሉ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በተለይም የገና በዓልን አስመልክቶ የኃይል አቅርቦት ችግር እንዳያጋጥም ከፍላጎት ጋር የሚመጣጠንና ተጨማሪ የሆነ ኃይል ዝግጁ ነው፡፡ ሁሉም የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎችና ሁሉም ዩኒቶች ፍተሻ ተደርጎላቸው ዝግጁ ተደርገዋል፡፡

አቶ ሞገስ እንደገለጹት፤ የሚመነጨው ኃይል ተጓጉዞ ማከፋፈያ ጣቢያ ድረስ እስኪደርስ ያለው የማስተላለፊያ መስመርና የማከፋፈያ ጣቢያዎች ፍተሻ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ የሚያስፈልገው ኃይል ዝግጁ ሆኗል፡፡ የገና በዓል በተለምዶ ከሌሎች በዓላት የተለየ የኃይል አጠቃቀም ፍላጎት እንዳለ ከዚህ በፊት ያሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የዘንድሮው የገና በዓል ምን ያህል ኃይል እንደሚያስፈልግ ተጠንቶ በቂ ኃይል እንዲቀርብ ተደርጓል ብለዋል፡፡

ሥራው የኃይል አቅርቦት ብቻ አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በጋራ በመሆን በዓሉ ያለምንም የኃይል አቅርቦት ችግር እንዲጠናቀቅ ለማድረግ በጋራ ውይይት ተደርጎ ሁለቱም ተቋማት ዝግጁ ናቸው ብለዋል፡፡ የኃይል ማከፋፈያና ማስተላለፊያ መስመሮች ጣቢያ የኦፕሬሽን ዘርፍ ያሉ ዘጠኝ ሪጅኖች ካሉት ኦፕሬተሮች ጋር በመሆን ችግር እንዳያጋጥም ካጋጠመም በፍጥነት መልሶ መጠገን ለማስቻል ተጠባባቂ የጥገና ባለሙያዎች ቡድን ተዋቅሮ ዝግጁ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት የኤሌክትሪክ ኃይል ተቋርጦባቸው የነበሩ አካባቢዎች ሁሉም በሚባል ደረጃ ካለፉት ሁለት ሳምንታት ወዲህ ኃይል ማግኘት መጀመራቸውን የገለጹት አቶ ሞገስ፤ ባለፈው ዓመት የገና በዓል ሁለት ሺ 500 ገደማ ኃይል መቅረቡን አስታውሰው በዚህ ዓመት በአፋርና ትግራይ ያሉ ከተሞች ኃይል ማግኘታቸውን ተከትሎ 3 ሺ 500 ሜጋ ዋት ኃይል ዝግጁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ፍላጎቱን ታሳቢ ያደረገ የገና በዓል የኃይል አጠቃቀም ላይ ምንም ችግር እንዳያጋጥም ሶስት ሺ 500 ሜጋ ዋት ኃይል ዝግጁ ተደርጓል፡፡ ይህም ከፍላጎቱ በላይ ከ500 በላይ ሜጋ ዋት ዝግጁ ነው፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት የኤሌክትሪክ ኃይል ተቋርጦባቸው የነበሩ አካባቢዎች ሁሉም በሚባል ደረጃ ካለፉት ሁለት ሳምንታት ወዲህ ኃይል አግኝተዋል፡፡

የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተሩ፤ ወደ ውጭ ምርት የሚልኩ ኢንዱስትሪዎች ያለምንም ችግር ሥራቸውን እንዲሠሩ ተደርጓል፡፡ ከፍተኛ የሆነ የኃይል ተጠቃሚ የሆኑ የሀገር ውስጥ ምርት አምራች ኢንዱስትሪዎች ግን ትናንትና ዛሬ እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ ክልከላ ተላልፏል፡፡ ይህ የተደረገው ከፍተኛ ኃይል ሲጠቀሙ ጫና ተፈጥሮ የኃይል መዋዠቅ እንዳይፈጠር ለማድረግ ነው፡፡

ባለፈው ዓመት ሁለት ሺ አምስት መቶ ገደማ ኃይል መቅረቡን ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፤ በዚህ ዓመት በአፋርና ትግራይ ያሉ ከተሞች ኃይል ማግኘታቸውን ተከትሎ አቅርቦቱ መጨመሩን ተናግረዋል፡፡ በአፋር ክልል ጭፍራና ሀራ ገበያ በስተቀር አብዛኛው አካባቢዎች ኃይል ማግኘታቸው የኃይል ፍላጎት በተለይም በበዓላት ወቅት እየጨመረ እንዲመጣ ማድረጉን አቶ ሞገስ ገልጸዋል፡፡



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን

# የዲፕሎማሲ ሥራችንን ተሻጋሪ ስምና ዝና ካላቸው ተቋማት ጋር ማቀናጀት እንደሚገባ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የዲፕሎማሲ ሥራችንን ተሻጋሪ ስም፣ ዝናና መሠረት ካላቸው ተቋማት ጋር ማቀናጀት፣ ማስተሳሰርና ማመጋገብ እንደሚገባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ተናገሩ።

የገና በዓልን በማስመልከት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር «ባህላችን ለዲፕሎማሲያዊ ትስስራችን መሠረት ነው» በሚል መሪ ቃል ለአምባሳደሮች የተዘጋጀ ስፖርታዊ ውድድር በትናንትናው ዕለት በሱሉልታ ከተማ ተካሂዷል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፤ ስፖርት ለዲፕሎማሲያችን ሁነኛ መለያችንና አቅማችን፤ ባሕልም ለዲፕሎማሲ አንዱ መሠረት ነው። ስፖርት የሕይወታችን ቀመርና አካል መሆኑን በመረዳት ባሕላችን በማድረግ በዲፕሎማሲ ዘርፍ ውጤት ማስመዝገብ ያስፈልጋል ብለዋል።

የዲፕሎማሲ መገለጫዎች ብዙ ናቸው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሯጮች የኢትዮጵያን ባንዲራ በዓለም አደባባይ ሲያውለበልቡ ዲፕሎማሲያዊ ተጽዕኖው የጎላ ነው። ሌሎች ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች በሙሉ የዲፕሎማሲያችን ቁልፍ ተደርገው መወሰድ ይኖርባቸዋል ብለዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የዲፕሎማሲው ቁልፍ ብራንዳችን ነው። ተሻጋሪ ስም፣ ዝናና መሠረት ካላቸው ተቋማት ጋር የዲፕሎማሲ ሥራችንን በእጅጉ ማቀናጀት፣ ማስተሳሰርና ማመጋገብ እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ማብራሪያ፤ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የበለጸገ ማኅበረሰብ ለመገንባትና የአምራች አቅምን ለማሳደግ ያለው ሚና ትልቅ ነው። አምባሳደሮች በሱሉልታ በነበራቸው የስልጠና ፕሮግራም ላይ ውጤታማ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ነበር። በሁሉም የስልጠና ቀናት ጠዋት ጠዋት የሚያደርጉት ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እንደ ጥሩ ባህል ሊወሰድ ይገባል። ወደፊት ባህልና የስፖርት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን በተለያዩ ተቋማት ስፖርታዊ ባሕል እንዲሰፋና እያደገ እንዲሄድ ይሠራል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች ባሉበት አገር የኢኮኖሚና ወታደራዊ አታሼዎች እንዳሉ ሁሉ የባሕል አታሼዎች እንዲኖሩን እንፈልጋለን። ስፖርት ለዲፕሎማሲ ያለው ጠቀሜታ ጠንካራ ነው። ለሀገራት ትስስርና ለሕዝቦች የእርስ በእርስ መጠናከር ያለው ሚና ትልቅ በመሆኑ ባሕላችን ልናደርገው ይገባል። ኢትዮጵያን ወክሎ በውጭ አገር የሚሄድ ሁሉ የኢትዮጵያን ባህላዊ ስፖርትን እንዲያስተዋውቅ ሲሉ አሳስበዋል። ከበርካታ ሀገራት ጋር የባህል ትስስር እንዲኖረን መሥራት አለባችሁ ሲሉ ለሚሲዮን መሪዎች መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ኢኮኖሚውን ስኬታማ ለማድረግ የአምራች ኢንዱስትሪው በጠንካራ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ሊደገፍ ይገባል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የአገር በቀል ኢኮኖሚ ስትራቴጂን ለማሳካት የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በጠንካራ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ሊደገፍ እንደሚገባ የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ መላኩ አለበል ገለጹ።

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት "ችግር ፈቺ ምርምርና ልማት ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘላቂ እድገትና ተወዳዳሪነት" በሚል መሪ ሀሳብ ከባለሃብቶችና ከተመራማሪዎች ጋር ምክክር ተደርጓል።

በምክክር መድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ባለፉት ዓመታት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ለማሻሻል በተለይም የሀገር በቀል ኢኮኖሚን ለመተግበር በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አምራች ኢንዱስትሪው ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል። ዘርፉ ግቡን የሚያሳካው በምርምር ሥራ ሲደገፍ በመሆኑ አምራቹ ባለሃብትና ተመራማሪዎች በቅንጅት ሲሠሩ ነው።

ባለፉት ዓመታት በቆዳ፣ በጨርቃጨርቅ፣ በፋርማሲና በሌሎች ዘርፎች በርካታ ጥናቶች ሲሠሩ ቆይተዋል ያሉት ሚኒስትሩ የተሠሩ የምርምር ሥራዎች ከመደርደሪያ የዘለለ ተግባራዊ ባለመደረጋቸው የአምራች ኢንዱስትሪው የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልቻለም ብለዋል።

ለዚህም የቅንጅት ጉድለት በመኖሩ፣ ባለሃብቱንና ጥናቱን በማቀናጀት በፖሊሲ የተደገፈ ሥራ ባለመሠራቱ እንደሆነ በመጠቆም፣ ይህን ችግር ለመቅረፍ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር "የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ"በመንደፍ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪው ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ የምርምር ሥራዎች የአምራች ኢንዱስትሪው ባለሀብቶች በቅንጅት መሥራት አለባቸው። ይህ ሲሆን የማምረት አቅም ያድጋል ብለዋል።

አቶ መላኩ አምራች ኢንዲስትሪው በመጪዎቹ አስር ዓመታት ከፍተኛ ሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የገቢ ምርቶችን በመተካት፣ የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም እንዲያሳድግ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ገቢ እንዲያድግ ተስፋ ከተጣለባቸው ዘርፎች ቀዳሚው መሆኑን ጠቁመው፤ አምስት ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም 85 በመቶ እንዲሆን የገቢ ምርትን በመተካት ረገድ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ዘርፉ ትልልቅ ግቦችን ማሳካት የሚችለው በጠንካራ የምርምርና የጥናት ሥራዎች መደገፍ ሲቻል መሆኑን



የኢንዱስትር ሚኒስትሩ መላኩ አለበል

የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ ከሁሉም ዘርፎች ጠንካራ ውድድር ያለበት የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ነው። ከቻይና፣ ማሌዥያ፣ ከአውሮፓና ከሌሎች ሀገራት የተመረተ ምርት ኢትዮጵያ ገብቶ መወዳደር የሚችለው ከአምራች ኢንዱስትሪው ጋር ነው። የኢንዱስትሪ ምርቶች ግብዓትና ምርቶች መዳረሻቸው ድንበር የለውም። ስለዚህ የአገር ጥንካሬን ከሚለኩና እውቀትን በስፋት ከሚሹ የሥራ መስኮች መካከል የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ትልቁን ስፍራ የሚይዝ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ በሀገር ደረጃ የተያዙ ትልልቅ እቅዶችን ለማሳካት በጥናትና ምርምር የተደገፉ ጠንካራና ተወዳዳሪ የሆኑ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ሲፈጠሩ ነው። ኢኖቬሽን፣ግንኙነት፣ ምርምር ሳይኖር ሀገርን ተወዳዳሪ ማድረግ አይቻልም። ያደጉ አገራት በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ጎልተው እንዲወጡ ካስቻሏቸው ዘዴዎች አንዱ ምርምር ላይ በሠሯቸው ተግባራት ነው።

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሚልኬሳ ጃገማ፣ ኢንስቲትዩቱ ከተሰጠው ተልዕኮ አንዱ ጥናትና ምርምር በማካሄድ አምራች ኢንዱስትሪው ምርትና ምርታማነቱ አድጎ ተወዳዳሪ ሆኖ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ማድረግ ነው። ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የድጋፍና ክትትል ሥራዎችን የሚሠራ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ምርምሮችን ከዩኒቨርሲቲዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ትግበራ ላይ እንዲውል ለማድረግ እየተሠራ ነው።

የአምራች ኢንዱስትሪውን በጥናት ለመደገፍ 67 የሚሆኑ የጥናትና የምርምር ሥራዎች መሠራታቸውን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ ከምርምሮቹ ውስጥ አምስት የሚሆኑት ለአምራች ኢንዱስትሪው ባለሃብቶች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል። በቀጣይም ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

ዜና

# መንግሥት በከተሞች የዲጂታል አሠራሮችን በማስፋፋት ለዜጎች ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ:- በከተሞች የዲጂታል አሠራሮችን በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መንግሥት ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ ተናገሩ።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር "ኢትዮጵያ 2050" የተሰኘው ተነሳሽነትን መነሻ ያደረገ ውይይት አካሂዷል።

ተነሳሽነቱ 2050 የሚኖረውን የሕዝብ ቁጥር የሚያስተናግድ ዝግጅት ላይ ያተኮረ ሲሆን ፖሊሲ አውጪዎች፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ ምሑራን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በአንድ በማሰባሰብ ወደ ፊት ሊያራምዱ የሚችሉ ሃሳቦችን ማፍለቅ የምክክሩ አጀንዳ ነው።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ በከተሞች የዲጂታል አሠራሮችን በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መንግሥት ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ነው ብለዋል።

የኤሌክትሮኒክ ግብይት አዋጅ፣ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ፣ የጀማሪ ቴክኖሎጂ ድርጅቶች (startup) አዋጅ፣ የግል ዴታ ጥበቃ አዋጅ፣ የዲጂታል መታወቂያ እና ሌሎችንም ምቹ ሁኔታዎችን መንግሥት እየፈጠረ መሆኑን አብራርተዋል።

እየጨመረ የሚሄደውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር የሚያስተናግድ የዲጂታል አሠራሮችን መዘርጋትና ለዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ ለማድረግ ቅንጅታዊ አሠራር ወሳኝ መሆኑንም ተናግረዋል።

ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ውይይቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በአንድ መድረክ በማገናኘት የልምድ ልውውጥ ለማድረግ እና አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ የሚያስችል መሆኑን ይጠቁማል።

## የደብረ ማርቆስ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የጊዜ ገደብ ቀድሞ ለማጠናቀቅ ጥረት እንደሚደረግ ኢንጂነር ዘየደ አስታውቀዋል።

የግንባታ ሥራው ከዚህ በፊት በነበሩት ጊዜያት በካሳ ክፍያ መዘግየት ምክንያት ተጓቶ እንደነበር የጠቆሙት ኢንጅነር ዘየደ ፤ አሁን ላይ ደግሞ የጠጠር መፍጫ ቦታ ባለማግኘታቸው በበለጠ ፍጥነት እንዳይሠራ እክል መሆኑን ገልጸዋል።

ለግንባታው የሚሆን ጠጠር በሚፈለገው ልክ በአካባቢው መቅረብ ከቻለ በተያዘው በጀት ዓመት የአስፓልት ሥራውን ሳይጨመር ሌሎች ሥራዎችን በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ እንደሚችሉ የጠቆሙት የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ፤ ግንባታውን ከተያዘለት የጊዜ ገደብ ቀድሞ ለማጠናቀቅ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የደብር ማርቆስ አውሮፕላን ማረፊያ እንደሀገር ያለውን የትራንስፖርት አማራጭ የሚያሳድግ መሆኑን የጠቆሙት ኢንጅነር ዘየደ፤ የአየር ማረፊያው ግንባታ ሲጠናቀቅ በአንድ ጊዜ አንድ ትልቅ አውሮፕላን ማሳረፍ እንደሚችል እና ሦስት አውሮፕላኖችን ማቆም የሚያስችል አቅም እንደሚኖረው አስታውቀዋል።

የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ስለሺ ተመስገን በበኩላቸው፤ የአየር ማረፊያ ግንባታው ሲጠናቀቅ አካባቢውን የኢንቨስትመንት ተመራጭ ለማድረግና ምርቶችን በፍጥነት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እንደሚረዳ ተናግረዋል፡፡

ደብረማርቆስና አካባቢው የበርካታ ቅርሶች ባለቤት እንደመሆኑ መጠን የአውሮፕላን ማረፊያው መሠራቱ ለቱሪስት ፍሰቱ መጨመር መንገድ የሚከፍት መሆኑን ምክትል ከንቲባው ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት በአየር ማረፊያው ግንባታ እስከ 500 ለሚደርሱ የአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለ ፕሮጀክት መሆኑን አስታውቀዋል።

የአየር ማረፊያውን ግንባታ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ግሩፕ የሚያሠራው ሲሆን፤ ሥራውን በተቋራጭነት እየሠራው ያለው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ነው፡፡ በአማካሪነት ደግሞ ፕሮሚነንት ኢንጅነሪንግ ሶልሽንስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር እየተሳተፈበት ይገኛል።

ግንባታው ጥር 9 ቀን 2014 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታውቋል።

## ኅብረተሰቡ በበዓላት ወቅት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በጤና ሚኒስቴር የሥርዓተ ምግብ ከፍተኛ አማካሪው አቶ ቢራራ መለሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ በበዓል ወቅት ከሚከሰት የጤና መታወክ መከላከል እንደሚያስችል ተጠቁሟል፡፡

በጤና ሚኒስቴር የእናቶችና ሕጻናት ጤናና የሥርዓተ ምግብ ዳይሬክቶሬት የሥርዓተ ምግብ ከፍተኛ አማካሪ፤ አቶ ቢራራ መለሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በርካቶች በበዓል ወቅት ከወትሮው የተለየና ቅባታማ ምግቦችንና የተለያዩ የአልኮል መጠጦችን የመጠቀም ልምድ አላቸው፡፡

ይሁንና ልምዱ ከጤና አንጻር የማይመከርና ለከፋ ችግር የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ ቅባት የበዛባቸውን ምግቦች መቀነስና፣ የአልኮል መጠጥ አጠቃቀምን የተመጠነ ማድረግ ይገባል ሲሉ ሙያዊ ምክር አስተላልፈዋል።

ከበዓላት በፊት ቅባት ያልበዛባቸውን ምግቦች እየወሰዱ የቆዩ ሰዎች ልክ የበዓል ዕለት በአንድ ጊዜ ቅባታማ ምግቦችን በብዛት ሲወስዱ፤ ለምግብ አለመፈጨት ችግር፣ ለማስመለስ፣ ለተቅማጥ በሽታና ለሌሎች የሆድ ሕመሞች የመጋለጥ ዕድሉ ከፍተኛ ይሆናል ብለዋል።

በተጨማሪም ለጨጓራ ሕመም ለሌሎች ከሆድና ተያያዥ የጤና እክሎች የሚያጋልጠውን ችግር ከወዲሁ ቅድመ ጥንቃቄ በማድረግ ማስቀረት ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

በበዓል ቀን ቅባትና በርበሬ የበዛባቸውን ምግቦች በብዛት ከመውሰድ መቆጠብና የአልኮል መጠጦችን አብዝቶ አለመጠቀም ይመከራል።

እንደ አቶ ቢራራ ገለጻ፤ የአልኮል መጠጥ በበዓል ወቅትም ሆነ ከበዓል ውጪ ባሉ ቀናት አብዝቶ መጠቀም ለሥርዓተ ምግብ መዛባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በተለይ ደግሞ በበዓል ወቅት አልኮል መጠጥ አብዝቶ መጠቀም ከቅባት ምግቦች ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዲባባሱ ምክንያት ይሆናል።

ቅባት የበዛባቸውን ምግቦች በተቻለ መጠን መቀነስና በአንድ ጊዜ ብዙ መጠን ያለው ምግብ አለመመገብ በበዓል ወቅት የሚከሰቱ የጤና ጠንቆችን ለመከላከል እንደሚረዳ አቶ ቢራራ አሳስበዋል፡፡

አቶ ቢራራ እንዳስታወቁት፤ ሁሉም ማኅበረሰብ በማንኛውም ጊዜ የተመጣጠነ የአመጋገብ ሥነ ዘዴን ቢከተል የተስተካከለ ጤና እንዲኖረው ያግዛል።

ሁሉም ማኅበረሰብ በበዓል ወቅት በይበልጥ ስለጤናው ጥንቃቄ ማድረግ ቀዳሚው ትኩረት ሊሆን ያሉት አቶ ቢራራ፤ በአጋጣሚ ችግሩ ቢፈጠር የጤና ባለሙያ ማማከር እና ወደ ጤና ተቋማት ሂዶ ተገቢውን ሕክምና ማግኘት አስፈላጊ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

ከዚህ ባለፈ በበዓልም ሆነ ከበዓል ቀናት ውጪ የአካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ጤናን የመጠበቅ ልምድ ሊዳብር እንደሚገባ የሥርዓተ ምግብ አማካሪው አስታውቀዋል።

## ምዕመናን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊ አመራር ላይ ከሚገኙ ኃላፊዎች ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማክበር ይጠበቃል ያሉት ፓትሪያርኩ፤ ሁሉም አካላት ለመልካም ነገር እንዲተባበሩ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዚዳንት ብፁዕ ካርዲናል ኣቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን በበኩላቸው፤ በብቸኝነት የሚገኙትን፣ የተገለሉትን፣ የአልጋ ቁራኛ የሆኑትንና አቅመደካሞችን ሁልጊዜ ማስታወስ ይገባል ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ በፌዴራል መንግሥትና ሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ የተገኘው ሰላም ቀጣይነት እንዲኖረው ሁሉም በትብብር እንዲሠራ አደራ ብለዋል።

በተገባው ቃል መሠረት የአፈፃጸሙ ድርጊት ተገዢ በመሆን ለመላው ሕዝብና በግጭቱ ዙሪያ ለሚገኙ ወገኖች ዘላቂ ሰላምና የሕዝቦች ቀና ግንኙነት እንዲመሰረት በአዲስ ምዕራፍ ተባብሮ መሥራት ያስፈልጋልም ብለዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻዲቁ አብዶ በበኩላቸው፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት በዓል ሲያከብር በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ምክንያት ከቤታቸው የተፈናቀሉና በችግር ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል::

በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት ወቅት ቤተክርስቲያናቸው የሰላም ጥሪዋን ስታሰማ መክረሟን ያወሱት ፓስተር ፃዲቁ፤ የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በተተገበሩ የሰላም አማራጮች የተሰማቸውን ደስታ በመግለፅ ሰላሙ ዘላቂ እንዲሆን አባታዊ መልዕክታቸውንም አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ፕሬዚዳንት ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ ባስተላለፉት የበዓል መልዕክታቸውም፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስን ልደት በዓል ሲያከበር የተለያየ ችግር የደረሰባቸውን ወገኖች በተለይም ተንከባካቢና አሳዳጊ የሌላቸውን ህጻናት፣ አቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንን፣ ህሙማንን፣ በድህነት የሚማቅቁና ተፈናቅለው የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

የክርስቶስ ልደት በዓል የሚያስታውሰውና የሚያስተምረው መሰረታዊ ቁም ነገር እርቅና ሰላምን ተግቶ መፈለግ መሆኑን ያስታወሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ምዕመናኑ የክርስቶስን ፈለግ በመከተል በተለይም አገሪቱ ሰላምንና መረጋጋትን እጅግ በተጠማችበት ወቅት ልዩነትንና ክፉ ውጤትን ለማስቀረት ዋጋን በመክፈል ሊሆን ይገባል ብለዋል። በመሆኑም ለበዓሉ አከባበር ከሚሰጠው ዋጋ ሰላምና አንድነት እጅጉን የላቀ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል።

የተጀመረው የሰላም ስምምነት አፈጻጸሙ በሚገባ ተተግብሮ የእርስ በእርስ እልቂት እንዲቆም፣ የሰብዓዊ ድጋፎችና የተለያዩ አቅርቦቶች መሟላት የሚታየው ጅምር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ፕሬዚዳንቱ አሳስበዋል።

በምዕራቡና በደቡብ የአገሪቱ ክፍሎች በተለይም በአራቱም የወለጋ ዞኖች ያለው የጸጥታ ችግር፣ የንጹሐን ሕይወት መጥፋትና ደም መፍሰስ እንዲሁም የንብረት መውደም ትኩረት የሚሻ ጉዳይ በመሆኑ በሰሜኑ ክፍል የሚታየው እርቅና ሰላም በተጠቀሰው አካባቢም እውን እንዲሆን ጠይቀዋል።

## "የልደት በዓል መስያየት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በአምላክና በሰው ልጆች መካከል ዕርቅ የተወጠነባት ዕለት ናት ሲሉ በመልዕክታቸው አስፍረዋል።

በዓሉ መለያየት የጠፋበት፣ ኅብረትና አንድነት የጸናበት፤ መለኮትና ሥጋ፣ ሕያውና ሟች፣ ዘላለማዊና ጊዜያዊ፣ ፈጣሪና ፍጡር፣ ሰማያዊና ምድራዊ፣ ምሉዕና ውሱን፣ በተዋሕዶ አንድ ሆነው አዲስ የምሥራች የተበሰረበት መሆኑን ገልጸዋል።

ክፉው በዘራው ዘር መለያየት ነግሦ፣ በሰማይና በምድር መካከል የማይሞላ ገደል ተፈጥሮ እንኖር ነበር። በጠብና በመለየት ምክንያት ኀዘንና ሰቆቃው በዝቶ በሰው ልጆች ታሪክ ጊዜው ዘመነ-ፍዳ ይሰኝ ነበር ብለዋል።

የክርስቶስ መወለድ የራቀን አቅርቦ፣ የጠፋውን አግኝቶ፣ የፈረሰውን ገንብቶ፣ የፍዳውን ዘመን ወደ ምሕረት በመቀየር በዘላለማዊ ዕርቅ አንድ አደረገን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

የልደቱ ብሥራት እረኞችን ከሜዳ፣ ሰብዓ ሰገልን ከሩቅ ከምሥራቅ ወደ አንድ አምጥቷል፤ ሰዎችን ከምድር ጠርቷል፤መላዕክትን ከሰማይ አውርዷል። ተራርቀው የሚኖሩትን አሰባስቦ በአንድነት እንዲዘምሩ ያደረጋቸው ጉዳይ ከትናንት ለየቅል ታሪካቸው ይልቅ የነገ የጋራ ተስፋቸው ብሩህ ሆኖ ስለታያቸው ነው ብለዋል።

እንደ መልዕክቱ ከሆነ፤ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ መለያየት የመጣው እንዲሁ አይደለም። ሆን ተብሎ ተሠርቶበት ነው። ክፉው ሆን ብሎ የልዩነትን ዘር ዘርቶና አብቅሎ፣ የጠላትነትን ፍሬ እንዲያፈራ አድርጓል። ልዩነቱም ከመለያየት አልፎ ወደ ጠላትነት እንዲሻገር ሠርቷል። ጠላትነቱም አዳምን ከገነት አፈናቅሏል። አቤልን በቃየል አስገድሏል።

አንድነትም የመጣው በብዙ ልፋትና መሥዕዋትነት እንጂ እንዲሁ በቀላሉ አይደለም። ዛሬ የምናከብረው ልደት ያስፈለገውም መለያየት ብቻ ሳይሆን በመካከላቸው ጠላትነት እንዲሰፍን የተሠራባቸውን ወገኖች አንድ ለማድረግ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን የነገዋን ኢትዮጵያ የተሻለች ለማድረግ ከልደቱ ታሪክ ብዙ ትምህርት ብንወስድ ይጠቅመናል። ዛሬ እዚህም እዚያም የምናየው የመለያየትና የመጠፋፋት አባዜ የባህሪያችን አይደለም፤ መለያየቱ የውስጥና የውጭ ባዕዳን አንድ ሆነው የዘሩብን ዘር ውጤት ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልክዕታቸውን አስፍረዋል።

የታኅሣሥ መከር የሚዘራው በሐምሌ ነው። አንዳንድ ሰዎች ትናንትኮ እንዲህ ያለ ነገር አልነበረም ይላሉ። ዘሩ ከምድር በታች በመብቀል ላይ ስለነበረ አላስተዋልነውም። ሰርዶው አድጎ እግር መጥለፍ ስላልጀመረ አልተቸገርንም ብለዋል።

እንክርዳዱ በዝቶ ራስ ማዞር ስላልጀመረ አልታወቀንም። እሾሁ አፍጥጦ ሰውነት መቧጠጥ ስላልጀመረ አልለየነውም። አሜከላው በርክቶ እግር ለማድማት ስላልደረሰ ከቁብ አልቆጠርነውም። እንጂ ክፉው ዘርስ እየበቀለ ነበረ ሲሉ ጠቁመዋል።

ወደ አዲሱ ዘመን፣ ወደ አዲሱ ብርሃን እንምጣ። ወደ አዲሱ ማንነት፣ ወደ አዲሱ ምዕራፍ እንምጣ። አዲስ የጋራ ታሪክ ስንሠራ፤ የትናንቱ ታሪክ ያግባባናል። አዲስ መንገድ ስንጀምር የትናንቱ መንገድ አያጣላንም። አዲስ ዘመን ስንወጥን ያለፈው ዘመን አያለያየንም። አዲስ ዓላማ አንግበን ከተነሣን፣ የትናንቱ ዓላማ አያጨቃጭቀንም ብለዋል።

እንደ መልዕክቱ፤ የጠላታችን ዓላማ አንዳችንን ጠቅሞ ሌላችንን መጉዳት ሳይሆን ሁላችንንም ማጥፋት ነው። ጠላት ክልልን ከክልል፣ ዞንን ከዞን፣ ወረዳን ከወረዳ፣ ጎጥን ከጎጥ፣ ቤተሰብን ከቤተሰብ፣ ባልን ከሚስት፣ ልጆችን ከወላጆች እያባላ ዓለምን ሁሉ የግጭትና የጠብ ዐውድማ ማድረግ ነው ምኞቱ።

ስለዚህ ቆም ብለን እናስብ። መንገዱ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የሚበጅ፣ ለሁላችንም በቅቶ የሚተርፍ፣ አዲስ ማንነትን ይዘን እንደገና መወለድ ነው። ታሪክ ማለፉ አይቀርም። ታሪክ መለወጡም አይቀርም። ቁም ነገሩ የታሪክ ተከሳሽና ተወቃሽ ወይንስ ተዘካሪና ተሞጋሽ እንሆናለን? የሚለው ነው በማለት ዶክተር ዐቢይ መልዕክታቸውን አስፍረዋል።

## ከአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

አአፕልኮ AAPDC



# እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን እና ልማት ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 74/2014 በተሰጠው ስልጣን እና ተግባር መሠረት የከተማዋን ገፀ ምድራዊ፣ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እቅድ በማዘጋጀት እና አፈፃፀሙን በመከታተል ብሎም በመቆጣጠር በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የአካባቢ ልማት ፕላኖችን ተግባራዊ እንዲሆኑ እና ከመሪ ፕላኑ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ከበርካታ ተግባራቱ መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ስለሆነም ኮሚሽኑ ከተማዋ ዘመናዊ፣ስልጡን እና በፕላን የምትመራ ለማድረግ እያደረገ ያለውን ጥረት በመገንዘብ የከተማ ነዋሪዎች እና የፕላን ተግባሪ ተቋማት ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ የድርሻቸውን እንዲወጡ ኮሚሽኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

በዚህ አጋጣሚ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን እና ልማት ኮሚሽን ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሠላም አደረሳችሁ!!! እያለ የመልካም በዓል ምኞቱን ይገልጻል፡፡

አአፕልኮ AAPDC

**“የከተማ ፕላን ለዘላቂ ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት”**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ኮሚሽን**
**መልካም በዓል!!!**

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

## ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የ14 ኛ ዙር የቤት ዕድለኞች ውል ለመዋዋል የሚጠበቅባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን በእጅጉ ከሚገዳደራቸው ዐበይት ችግሮች መካከል የመኖሪያ ቤት እጥረት አንዱ ነው። የከተማ አስተዳደሩም ይህን የኅብረተሰቡን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ በዘላቂነት ለመፍታትና ችግሩን ለመቅረፍ በተለይ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የተቀናጀ የቤቶች ልማት መርሐ ግብር ቀርጾ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በመገንባትና በማስተላለፍ ላይ ይገኛል።

ይሁን እንጂ የቤት ልማትና አስተዳደር ሥራዎች አፈጻጸሙ ከኅብረተሰቡ የቤት ልማት ፍላጎትና ተጠቃሚነት አንጻር የግንባታ ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ሁኔታ መዘግየት እና አዳዲስ ፕሮጀክቶች አለመጀመር ይስተዋላል። እንዲሁም ከቤት ልማት ማስተላለፉና ማስተዳደሩ አንጻር ለክትትልና ለቁጥጥር ሥራ በማያመች መልኩ መደራጀቱ፣ የተግባርና የኃላፊነት መደራረብ መኖሩ፣ የኅብረተሰቡን የቤት ጥያቄ ለመመለስ የአሠራርና የአደረጃጀት ክፍተቶች ታይተውበታል። በተጨማሪም በየዕለቱ ወደ ከተማዋ ፈልሶ ከሚገባው ሕዝብ አንጻር በመዲናዋ የሚስተዋለውን የቤት አቅርቦትና ፍላጎት ልዩነት ለማጣጣም አልተቻለም።

ሆኖም በሀገሪቱ የመጣውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ እንደ ከተማ አስተዳደር ችግሩን ለመፍታት ጥናቶች በማካሄድ እና መሠረታዊ መነሻ ምክንያቶችን በመለየት በቤቶች ማልማት፣ ማስተላለፍና ማስተዳደር ላይ የነበረውን አደረጃጀትና አሠራር በማሻሻል እንዲሁም የለውጥ አመራሩ ቁርጠኛ አቋም ይዞ የቤት ልማት ሥራው ለክትትልና ለቁጥጥር ሥራ በሚያመች



አቶ ጋሻው ተፈራ፤

መልኩ አደራጅቶ በማከናወን በ2011 ዓ.ም ዕጣ የወጣባቸውን ከ61 ሺ. በላይ ቤቶች አጠናቆ ለቤት ዕድለኞች አስረክቧል።

ከዚህ ባሻገር ከተማ አስተዳደሩ በ14 ኛ ዙር የ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም 18 ሺ. 930 ቤቶች፣ በ40/60 ደግሞ ስድስት ሺ. 843 ቤቶች እንዲሁም ተጨማሪ 18 ስቱዲዮ ቤቶች በድምሩ 25 ሺ. 791 ቤቶችን ዕጣ የማውጣት መርሐ ግብር በቅርቡ ተካሂዷል። ከዚህ አንጻር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የ14 ኛ ዙር 20/80 እና 3ኛ ዙር 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቤት ዕድለኞች የውል መዋዋያ ቀን ከሰኞ ጥር 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት ባሉት 60 የሥራ ቀናት ውስጥ ባለ ዕድለኛው ወይም ወኪሉ ቀርበው መዋዋል እንደሚጠበቅባቸው አሳስቧል። ውል የመዋዋያ ቦታው መገናኛ በሚገኘው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅጥር ግቢ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ውስጥ ነው። ስለዚህ የ14 ኛ ዙር 2080 እና 3ኛ ዙር 4060 የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቤት ዕድለኞች ውል ለመዋዋል ሲመጡ ማሟላት ስለሚጠበቅባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በሚመለከት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ጋሻው ተፈራ የሰጡንን ማብራሪያ እንደሚከተለው ይዘንላችሁ ቀርበናል።

### የቤት ዕድለኞች ውል ለመዋዋል ሲመጡ ማሟላት የሚጠበቅባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

* ዕጣው የደረሰው ግለሰብ ውል ለመፈፀም በአካል መቅረብ፤
* በውጭ የሚኖሩ ጉዳያቸውን በውክልና ለማስጨረስ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አውተንቲኬት ሆኖ የመጣ ውክልና ማቅረብ፤
* የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ዋና እና 2 ፎቶ ኮፒ፤
* የጋብቻ የምስክር ወረቀት ዋና እና 2 ፎቶ ኮፒ፤
* ያላገባ/ች ከሆነ/ች 6 ወር ያላለፈው የምስክር ወረቀት፤
* ያገባ/ች ከሆነ/ች የትዳር አጋር የታደሰ መታወቂያ ዋና እና ፎቶ 2 ኮፒ፤
* የምዝገባ ማረጋገጫ (print out) ዋና እና 1 ፎቶ ኮፒ፤
* የምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና እና 1 ፎቶ ኮፒ፤
* የባንክ ምዝገባ ማረጋገጫ ከተመዘገቡበት ባንክ የሚቀርብ ዋና እና 1 ፎቶ ኮፒ፤
* የባንክ የቁጠባ ደብተር ዋና እና 2 ፎቶ ኮፒ (ፎቶ ባለው በኩል)
* የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TIN) ዋና እና 2 ፎቶ ኮፒ፤
* ቅጽ -09 (ከወረዳ ተሞልቶ ታሽጎ የሚላክ) ዋና እና 1 ፎቶ ኮፒ፤
* የጠፋ ሰነድ ካለ የፖሊስ ማስረጃ ዋና እና 1 ፎቶ ኮፒ፤
* 4x4 የሆነ ጉርድ ፎቶ ግራፍ 4፤
* ፍቺ ካለ:- በፍርድ ቤት የፀደቀ ፍቺ ዋና እና 2 ፎቶ ኮፒ፤
* የንብረት ክፍፍል ዋና እና 2 ፎቶ ኮፒ፤
* ባለ ዕድለኛው በሞት ከተለየ:- የውርስ አጣሪ ሪፖርት ዋና እና 2 ፎቶ ኮፒ፤
* የወራሽነት ማስረጃ ዋና እና 2 ፎቶ ኮፒ ባለዕድለኛው ወይም ወኪሉ ይዞ መቅረብ ይጠበቅበታል። ስለዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ሳያሟላ የሚመጣ ማንኛውም ባለጉዳይ አይስተናገድም።

ሆኖም በውጭ ሀገር የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያዊ ከላይ የተጠቀሱትን ማሟላት የግድ ሆኖ የታደሰ ፓስፖርት ወይም የሎ ካርድ (ቢጫ ካርድ) የታደሰ፤ በውክልና ከሆነ የውክልና ወረቀቱ በጀርባው በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ማህተም የተረጋገጠ፤ የተወካይ የታደሰ መታወቂያ ይዞ መቅረብ ያስፈልጋል። ነገር ግን በመመሪያ ቁ/3/2011 አንቀጽ 1እና 2 መሠረት ባለእድለኞች ወይም ወኪላቸው ምዝገባ ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ባሉት 60 የሥራ ቀናት ውስጥ ቀርበው ካልተዋዋሉ ቤቱን እንዳልፈለጉት ተቆጥሮ ተመላሽ ይደረጋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

## የዘመን እንግዳ

# ‹‹ ከችግር የመውጫ መንገዳችን ቁጭ ብሎ መነጋገር ፤ እውነታውን መቀበልና ይቅር መባባል ናቸው››

## - ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ ካሣ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

በቅድስት ሥላሴ መንፈሣዊ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ምግባር እና የመንፈሳዊ ፍልስፍና መምህር ናቸው -ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ ካሣ ። ውልደታቸው በአዲስ አበባ፤ ኮልፌ አጠና ተራ ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ሰባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቀዋል። ከልጅነታቸውም ወደቤተክርስቲያንና መንፈሳዊ ሕይወት ያዘነብሉ ስለነበር ወደ መናገሻ ማርያም ገዳም አምርተው ለሁለት ዓመታት የአብነት ትምህርት ተምረዋል። በምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት አማካይነት በ1989 ዓ.ም ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብተው በ1993 ዓ.ም በቲኦሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ከዛም ለአንድ ዓመት በጠቅላይ ቤተክህነት የውጭ ግንኙነት መምሪያ ውስጥ በረዳት የሥነ ጽሑፍና የምርምር ባለሙያ ሆነው አገልግለዋል።

በመቀጠልም በውጪ ሀገር የትምህርት ዕድል አግኝተው ወደ ቤልጅየም ሄዱ። በእዛም በሉቨን ዩኒቨርሲቲ በሃይማኖት ጥናት ነገረ መለኮት ሁለት የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲሁም በነገረ መለኮት ሥነ ምግባር የዶክትሬት ትምህርታቸውን አግኝተዋል። ፍልስፍናውን ዘልቀው ብዙ እውቀት ቀስመዋል፤ ያላቸውንም ለሌሎችም አካፍለዋል። የዶክትሬት ጽሑፋቸውን ያማከራቸው ለነበረው ፕሮፌሰር ረዳት ተመራማሪ ሆነው ለሁለት ዓመት ሠርተዋል። “Theanthropic Ethics in Conversation with Autonomy and Heteronomy” በሚል ርዕስ ያዘጋጁት መጽሐፍ በአማዞን የኦንላይን መጽሐፍ መሸጫ ድረ ገጽ ለአንባቢያን አቅርበዋል።

“በትረ ሃይማኖት፦ የተዋሕዶ ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮ እና የምዕራባውያን ፍልስፍና በሚን ጸባረቅ ባቸው ክርስቲያናዊ አመለካከቶች ላይ የሚሰነዘረው ትችታዊ ዕይታ” የሚል መጽሐፍ ጽፈዋል።

ከቤልጅየም የ16 ዓመት ቆይታቸው በኋላ ለሀገራቸው አንዳች ነገር በእውቀታቸው ማበርከት እንዳለባቸው በማመን እና በሥነ ምግባር ደግሞ ስለሀገር ማኖር ያለባቸውን አበርክቶ ከግምት ውስጥ በማስገባት በ2010 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል።

ከእዛም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በመምህርነት፣ በአካዳሚክ ምክትል ዲን ኃላፊነትና ዩኒቨርሲቲ ከሆነ በኋላ ደግሞ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ለአራት ዓመት በመሥራት በተቋሙ መማር ማስተማር ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክተዋል። በአሁኑ ወቅትም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ምግባር፣ የፍልስፍናና የመንፈሳዊነት ትምህርቶችን በማስተማር እያገለገሉ ይገኛሉ።

ለዛሬ‹‹የዘመን እንግዳችን›› አድርገን የመረጥናቸው ከፍልስፍና፣ ከሀገር ሰላም፣ ከይቅርታና ከመረዳዳት ጋር ተያይዞ ከእሳቸው ሰፊ ትምህርት እንደምናገኝ በማሰብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ አዲስ አበባ መሐል አራዶች መንደር ተወልደው በመንፈሳዊ ሕይወት ረጅም ጉዞ መጓዝ የቻሉበት ምስጢር ምንድን ነው?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** ወደ ቤተክርስቲያን እንድገባ ያደረገኝ ገና ልጅ ሆኜ ብዙ የፍልስፍና ጥያቄዎች ነበሩኝ። ከሕልውና ጋር የተያያዙ እኔ ማን ነኝ፣ ሕይወት ምንድን ነው የሚሉና በወጣትነት ዘመናችን ልንመልሳቸው የማንችላቸው ምናልባትም ከባድ የሚባሉ ጥያቄዎች ወደ አዕምሯችን ይመጣሉ። እነዚህ ጥያቄዎች አዕምሮዬን



ፎቶ፡ እዩብ ተፈሪ

ያናውጡት ስለነበር ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት ስል ወደ ቤተክርስቲያን አመራሁ፤ መልስም አገኘሁ። ስለዚህ መልስ ካገኘሁበት የበለጠ ልገፋበት ይገባል፤ ማገልገል ካለብኝም ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው በሚል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄ ወደመናገሻ ገዳም ገባሁ።

ከተማ ውስጥ ብዙ የሚያታልሉ፣ አዕምሮ የሚይዙና የሚያዘናጉ ነገሮች ባሉበት ሁኔታ ወደቤተክርስቲያን መሄድ ይከብዳል። ግን እኔ ዕድለኛ ሆኜ አባቴ በሥነ-ምግባር ነው ያሳደገኝ። ብዙ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳደሩ ነገሮች እንዳይጫኑኝ ትልቅ ሥራ ሠርቷል። አሁንም ድረስ ወደ ሥነ ምግባር እንዳዘነብል ያደረገኝ ሥነ ምግባራዊ መመሪያዎቹ ይመስለኛል። የአባቴ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ትልቅ ቦታ አለው። የእነዚህ ድምር ውጤት በቤተክርስቲያን ትምህርት እንድዘልቅ እና ካህን እንድሆን አስችሎኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ቤልጂየም የተጓዙበት አጋጣሚው ምን ነበር?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ስንመረቅ በከፍተኛ ማዕረግ ስለጨረስኩኝ፤ አውሮፓና አሜሪካ ያሉ የትምህርት ተቋማትን የማግኘት አጋጣሚ ተፈጠረ። በዚህም ቤልጂየም ተቀበሉኝ። ከዚህም ደግሞ የመንፈሳዊ ኮሌጁ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ጢሞቲዎስም የድጋፍ ደብዳቤ ፃፉልኝ። በወቅቱም ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን ወደ ቤልጂየም ሊበን ዩኒቨርሲቲ በማምራት ሁለተኛ ዲግሪዬን የመማር ዕድል አገኘሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የአውሮፓ መንፈሳውያን ዓለማዊነት የተጫናቸው እንደሆነ ይነገራል። እርስዎ ደግሞ ቀደም ሲል ከገዳማውያን ጋር ነበሩ። እነዚህን ነገሮች ለማስማማት አልተቸገሩም?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** ቤልጂየም በአካዳሚክ ዐውድ ብሎም እንደ አውሮፓ መንፈሳዊ ተቋማትና ትምህርት ቤቶች በብዛት ፍልስፍና የተጫናቸው ናቸው። ሁሉም አስተምህሮ በፍልስፍና የተቃኘ ነው። ሃይማኖቱ፣ ኢኮኖሚው፣ ሳይንሳዊ ጥናቱ፣ የትምህርት ተቋምና ባህሉ፣ የፍልስፍና ተፅዕኖ አለበት። እስካሁንም የፍልስፍና እይታ የበላይ ሆኖ ያለበት ነው። እዚህ ደግሞ ፍልስፍናን እንደ አንድ ኮርስ እንማረው እንጂ በገዘፈ መልኩ የተመለከትናቸው አልነበሩም። እኛ ትምህርተ መለኮትን የምናውቀው በዶግማ መሠረት ነው። ከሕይወት ጋር የምናቆራኘው እንጂ እንደ እውቀት፣ ፍልስፍና፣ የአዕምሮ የማወቅ ጠባይ የሚወሰድ አይደለም። ስለዚህ ሁሉም ነገር ፍልስፍና ሲሆን የአካዳሚክ ዐውዱ በራሱ ከለመድነው የሚቃረን ጠባይ አለው። የአካዳሚክ ዐውዳቸውም እኛ ከምናውቀው በጣም ይለያል። ይህን ለማቻቻል ትንሽ ለማላመጥና ማዋሃድ ጊዜ ይፈልግ ነበር። ማኅበረሰቡም ከኢትዮጵያ በጣም የተለየ፣ ግላዊነት የተላበሰና ብዙ ነገሮች ዝግ ናቸው። አየሩም ከባድ ነበር።

በመሆኑም ስድስት ወራት አስቸጋሪ ስሜት ነበር፤ በሂደት ግን ነገሮች እየተስተካከሉ መጡ። ወደቤልጂየም በሄድኩ በአምስት ወራት ልዩነትም ባለቤቴ ወደዚያ መጣች። እዚያ ጥሩ ነገሩ ለመማር ብዙ ግብዓቶች በሚፈለገው ሁኔታ ይገኛሉ። ከየትኛውም ቦታ መጽሐፍት ይገኛሉ። እነዚህ በመሟላታቸው ከማኅበራዊ ዐውድ መውጣቱ እንዳለ ሆኖ ግን ለማንበብ ዕድል ይሰጣል። እኛም አዕምሮን ለትምህርት በመስጠት ለ16 ዓመታት በአውሮፓ አሳልፈያለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በአውሮፓ ሁሉ ነገር ፍልስፍናው የተጫናው ከሆነ፤ እርስዎ ከመንፈሳዊነት እወጣለሁ ብለው አልሰጉም?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** በፍፁም! ይህ ያልሆነበት ምክንያት አንደኛው ገዳም ለሁለት ዓመት ቆይቻለሁ። በዚህ ስማረው የነበረው ትምህርትና አገኛቸው የነበሩ አባቶች ሕይወቴ ላይ ያተመው መንፈሳዊ ስሜት አለ። አምስት ዓመታት ቲኦሎጂ ተምሬያለሁ። በተጨማሪም ሳገኛቸው የነበሩ መንፈሳዊ መምህራን፣ እየሄድኩ ስማርባቸው የነበሩ ዐምደ ሃይማኖት፣ ግቢ ገብርኤል ሰንበት ትምህርት ቤት፣ ቅድስት ማሪያም፣ ፈለገሕይወት ሰንበት ትምህርት ቤትና ሌሎች የሰንበት ትምህርት ቤቶች የምወስዳቸው ኮርሶች እና በግሌ ሳደርጋቸው የነበሩ ጥረቶች፣ ብሎም የግብፁ አቡነ ሺኖዳ ይጽፏቸው የነበሩ መጽሐፍትን ከግብጽ ወንድሞችና እህቶች በገፍ ስለምናገኝ አነባቸው ነበር። እነዚህ የሕይወት ዕይታዬን በእምነት እንድገነባውና ራሴን እንዳዘጋጅ አግዞኛል። በተጨማሪም እውቀት የማስፋት እንጂ ከነበረኝ እምነት ዐውድ ውጪ እንድወጣ የሚያደርገኝ ነገር አላጋጠመኝም።

በእርግጥ ፍልስፍና አስቸጋሪ ነው። ሁሉንም ነገሮች በምክንያት ስለሚያስረዳ እውነት ይመስላል። ብዙ ሰዎች ቁጭ ብለው በአንድ ጉዳይ በተለያየ አመክንዮ የተለያየ ዕይታና አቋም ያሳያሉ። በዚህ ጊዜ ልብ አንድ ቦታ ማረፍ ይቸገራል፤ ይህን ለማግኘት ማንበብ ይመጣል። በመጨረሻ ወደአመነበት ይወስዳል። ከዚህ በዘለለ ግን በእኔ ሕይወት ላይ የፈጠረብኝ ተፅዕኖ የለም።

**አዲስ ዘመን፡- የክርስትና እምነትን በተመለከተ ብዙ ጊዜ አትመራመር ይባላል። ከዚህ አንጻር ፍልስፍና አይከብድም ?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** እርሱ ከፍርሃት ነው፤ እኔ አልስማማም። ክርስትና በጭፍን የሚገባበትና የምንከተለው አይደለም። በጭፍን የምንከተለው ከሆነ በጣም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም አንድ የሚያሳምን ነገር ሲገኝ ጥለኸው ትሄዳለህ። ክርስትና ደግሞ ምክንያታዊ ነው። አዕምሮን የማሸነፍ አቅም አለው። ይህ ማለት በፍልስፍናው የሄዱ ትልልቅ አስተማሪዎችን የሚያቀርቧቸውን አመክንዮችን የመጋፋትና የማሳመን አቅም አለው።

ክርስትና ምክንያታዊና አመክንዮአዊ ነው፤ መገለጥ ይችላል። በየትኛውም አግባብ ጥያቄ ለሚያነሱ መልስ መስጠት ይችላል። እኔም ይህን የበለጠ እንዳሰፋው ዕድል ሰጥቶኛል።

በተለይም የአራተኛው ክፍለ ዘመን አባቶች የምንላቸው እነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አትናቲዎስ፣ ባስሊዮስና የመሳሰሉት በአቴንስ ይሰጥ የነበረውን የግሪክ ፍልስፍና የተማሩ ግን ደግሞ ክርስትናን የታደጉ፣ ፍልስፍናን መጠቀሚያ መሣሪያ አድርገው ያስተማሩ አባቶች ናቸው። እነዚህን የማንበብ ዕድል አግኝቻለሁ። ለምሳሌ እነ ዮሐንስ አፈወርቅ አመክንዮና የማሳመን ጥበብ ተምረዋል። ይህን ከመማራቸው በፊት ወንጌልን፣ ታሪክን፣ የክርስትና የእምነት አስተምህሮ ተምረዋል፤ ያውቃሉ። ስለዚህ ክርስትናውን ይዞ ፍልስፍናውንና የማሳመን ጥበብን መጠቀሚያ ነው ያደረጋቸው። ፍልስፍናውን ስለምንፈራ እና የሚመራመሩ ሰዎች ይክዳሉ ተብሎ ስለሚታመን እንጂ ፍልስፍና ክርስትና ፊት የሚቆምበት የጠነከረ አቋም የለውም። ሂደቱን ጠብቆ ከሄደ ችግር የለውም። ችግሩ ግን እምነትን ባልተረዳንበት ፍልስፍና ቀድሞ ከገባ አደገኛ ነው። በራሱ መንገድ ክርስትናን ለመጫን የሚሞክረው

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ፍልስፍና ነው።ትልቅ ተግዳሮት ነው። በዚህ ዘመን የሁሉም ነገር መለኪያና መስፈሪያ አዕምሮህ ነው ብለው እምነትን አውጥተው ጥለውታል።

**አዲስ ዘመን፡- ፍልስፍና ሰፊና ጥልቅ ነው። ሀገራችን ደግሞ ካላት ጥንታዊነትና ጠንካራ የሃይማኖቶች አስተምህሮ አንጻር ሴሎች ለእኛ የነበራቸው አተያይ ምን ይመስላል?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** በነበረኝ አካዳሚክ ቆይታ ከቅዱሳት መጽሐፍት፣ የብሉይ፣ የሀዲስ ኪዳን፣ የሥነ ምግባር መምህራን ጋር ብዙ ጊዜ የምንጨቃጨቅባቸው ምክንያቶች ነበሩ። በኋላ ሲገባኝ እየተውኩት መጣሁ። እነርሱ ሁሉንም ነገር የሚያዩት በሳይንሳዊ ፍልስፍና ነው። የቲኦሎጂ አስተማሪ ሆነው የዳርዊንን የዝግመተ ለውጥ ቲዎሪ የሚቀበሉ ናቸው። የሰው ልጅ ከጦጣ የመጣ ነው የሚሉ ናቸው። የማያምኑበትን ነው የሚስተምሩት፤ ይህ ለእነርሱ እውቀት ነው። አንድ ዓለማዊ ትምህርት እንደ ማጥናት እንጂ ከማንነታቸው ጋር የተቆራኘ አይደለም። እኛ ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ በማለፋችን ብዙ ጊዜ የሚቃረኑና የማይስማሙ ነገሮችን እያነሳን እንነጋገራለን። አባቶቻችን «አንድም» እያሉ በትርጓሜ ያስቀመጡት ለእነርሱ እንግዳ ነው፤ አያውቁትም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የመርገም እና የመመረቅ ሃብት የተሰጣቸውን አንድ አድርገው የሚረዱና የሚከራከሩ ናቸው። ይሁንና መርገምና ምረቃን በአንድ ዓይን አስተካክለው የሚረዱ አሉ። ስለዚህ ዝም ብሎ ለመስማት ካልሆነ የማያግባቡ በርካታ ጉዳዮች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ቅኝ ያልተገዛች፣ በዕምነት ደግሞ ጥንታዊት ከሆነች ሀገር የሄደ ተማሪ እና በቅኝ ግዛት ውስጥ የነበሩ ሀገራት ተማሪዎች እንዲሁም ከምዕራባውያን አስተማሪዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዴት አቻቻሉት?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** ለኢትዮጵያውያን ያላቸው እይታ የተለየ ነው፤ እንደ ሌላው ሀገር አያዩንም። በፀሎት ቤታቸው ውስጥ ከኢትዮጵያ በተለያዩ መንገዶች የወሰዷቸው መጽሐፍትና ሥዕላት አላቸው ግን አያውቁትም፤ አያነቡትም ሆኖም ያከብሩታል። መምህራኑም ጭምር ለኢትዮጵያ የተለየ እይታ አላቸው። በቡሉይ ኪዳን ውስጥ በርካታ ቦታ የኢትዮጵያ ሥም መነሳቱና ቅኝ ያልተገዛን መሆናችንንም ያውቃሉ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ነገር ሲነሣ በትኩረት ይመለከቱታል። በመማሪያ ክፍል ውስጥም የአተያይ መሠረታዊ ልዩነት አለ። የተማርንበትና የምንጠይቅበት አተያይ ስለሚለይ ይገረማሉ፤ እንጂ አይቀበሉም። እኛም እነርሱንም መቀበል አንችልም። ከአፍሪካ እና ሌሎች ሀገራት የመጡትም ይፈተናሉ።

ሁሉም ከሁሉም አቅጣጫ የሚለው ነገር አለ፤ የዕውቀት ብፌ አለ። በመሆኑም ለማሳመን አስቸጋሪ ነው። ብዙ ጊዜ በክፍል ውስጥ ክርክር አድርጌ አውቃለሁ። ሰምተውት የማያውቋቸውን ነገሮችንም ለመስማት ይገደዳሉ። እነርሱ ከሚያውቁት አዲስ እይታ እንዲኖራቸው አድርገናል። አካዳሚያቸው ከክርስቶስ በፊት በነበረ ፍልስፍና የተቃኘ በመሆኑ ፍልስፍናው ተጭኗቸዋል። ስለዚህ እነርሱ እኛ ላይ የራሳቸውን ፍላጎት ለመጫን እንጂ ለመቀበል ብዙም የሚጓጉ አይደሉም። ቅኝ ባለመገዛታችን እኛ ስንናገርም፤ ስንራመድም ነጮቹን በጣም ያስገርማቸዋል። ሌሎች እጥፍ ዘርጋ ሲሉ እኛ የተለየ ስሜት አናሳይም። እዚያ ሆነን ዓድዋን እናስታውሳለን። አባቶቻችን የበታችነት ስሜት እንዳይሰማንና ከላያችን ላይ የገፈፉልን ስሜት ዋጋው በጣም ትልቅ እንደሆነ እንረዳለን። ከሥም አወጣጣችን ጀምሮ በራሳችን ቀለምና ስያሜ ነው ያለነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመንፈሳዊውም ሆነ በፍልስፍናው ሰላም የሚጀምረው ከማን ነው?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** ሰላም የሚጀምረው ከራስ ነው። ከሰዎች የውስጥ ስብዕና ይጀምራል። ሰላም ፈልገን በሰዋዊ ኃይል የሚመጣ ሳይሆን ከፈጣሪ ጋር ስንሆን የሚገኝ ውጤት ነው። ሰው ከራሱ ጋር የታረቀ መሆን አለበት። መጀመሪያ አንደበት ከሕሊና ጋር፣ የምንናገረው ከውስጥ ካለው ሐሳብ ጋር የተስማማና የተዋሐደ መሆን አለበት። ልቡ የተከፋፈለ፤ ውስጡ የተበታተነና ራሱን መቆጣጠር ያልቻለ ሰው ከሌሎች ጋር ጤናማ ግንኙነት አይኖረውም። በቤተሰብ፣ በሥራ ቦታ፣ በማኅበረሰብ ሆነ በየትኛውም ቦታ መጀመሪያ ሰላም መቅደም አለበት። የሰው ልጅ ደሴት ስላልሆነና ሕይወቱ ከሌሎች ጋር የተገናኘ በመሆኑ መስተጋብሩ ሰላማዊ መሆን አለበት። ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ሰላማዊ እንዲሆን መጀመሪያ ከአምላኩ ጋር ያለው ግንኙነት መቅደም አለበት። ምክንያቱም የሕልውና መገኛው እግዚአብሔር ስለሆነ። ከእናትና አባቱ ጋር ሰላማዊ ያልሆነ ሰው ከማኅበረሰብ ጋር ሰላማዊ የመሆን ዕድሉ ጠባብ ነው። ስለዚህ ሰላም የሚመነጨው ከራስ ነው። ሰላም ትርጉሙ ብዙ ነው። ሙሉ ውሕደት የሚመጣው የስብዕና ግንባታ የሚዳብረው፣ የአዕምሮ ልዕልና የሚመጣው ብሎም ነገሮችን የምናይበት ዓውድ መነሻው ሰላም ነው።

አንዳንድ ጊዜ ጦርነት በሌለበት ጦርነት አለ፤ የጦር መሣሪያ በሌለበት ግጭት አለ፣ አካላዊ ግጭት ባይገንበትም ውስጣቸው እርስ በእርስ የሚታኮሱ፣ በውስጣቸው የሚገዛገዙ ሰዎች አሉ። ይህ የመጀመሪያው የፀብ መነሻና መንደርደሪያ ነው። ይህ ከስሜት ጋር አለመናበብ ነው። መሰል ሁኔታ ውጤቱ መገለጫው ይቆይ ይሆናል እንጂ ግጭት አለ። ስለዚህ ሰላማዊ ሁኔታ መፍጠር ይገባል። ሰላም ከራስ ይጀምራል፤ ሰላም ከውስጥ ይጀምራል የሚባለውም ለዚህ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ከሃይማኖታዊ አስተምህሮና ከባህል ያፈነገጡ ነገሮች ይስተዋላሉ ። ይህን አልፈን ወደ ሰላማዊ ግባችን እንዴት መድረስ ይቻላል?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሰላምን ለመግለፅ የምንቸገር ይመስለኛል። ኢትዮጵያ በብዙ አቅጣጫ የተወጠረች ሀገር ናት። በተለይም በውጭ ያሉ ኃይላት የኢትዮጵያን ሰላም አይፈልጉም። ጦርነት እንዲፈጠርና እርስ በእርስ እንድንጠፋፋ የሚፈልጉ፣ የሚፈለገውን ግብዓት የሚያቀርቡ፤ በዓላማ የሚሠሩ አካላት አሉ። ይህ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እይታ ውጭ አይመስለኝም ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ካለን ተወያይተን የማንፈታው ችግር የለም።

ሁሉም ስለኢትዮጵያ የሚያስብ ከሆነ መነጋገር ይቻላል። አንድ ዓላማ እስካለን ድረስ እንደ ሀገር የምናልመውን ዓላማ ለማሳካት ግላዊ ፍላጎቶቻችንን መገደብ አለብን። የውጪ ጣልቃ ገብነት ካለ ቁጭ ብሎ ለመነጋገር ዕድሉ አይኖርም። የዘር ግንድ፣ የቋንቋ ሥርዓት እና ሌላውንም ነገር በመጠምዘዝ ወደሌላ ይተረጎማል። ተነጋግረን አንግባባም፣ በአንድ ዓላማ ላይ ሆነን ዙሪያ ጥምጥም እንሽከረከራለን። እንደ ሀገር ይህን ዓይነቱን ጉዳይ ያሳለፍነው ይመስለኛል። በማናቸውም ሁኔታ ቅሬታ ያላቸው አካላት ሁሉም በጋራ መቀመጥ አለባቸው። መቀመጥ በራሱ ለሰላም የመጀመሪያው እርምጃ ነው። የሰለጠንን ሰዎች ነን፤ ስለዚህ ከመነጋገር የሚያልፍ ነገር የለም። ከሰው ልጅ አቅምና እውቀት በላይ አይደለም። ብዙ ሀገራት ቁጭ ብለው በመነጋገር ችግራቸውን ፈትተዋል። ስለዚህ የመጀመሪያው ቁጭ ብሎ መነጋገር ነው። ሁለተኛው ደግሞ እውነታውን መነጋገር ነው። ነገሮችን በትክክል ማስቀመጥ ይገባል። የማንስማማባቸው ነገሮችን በመነጋገርና በደልን በይቅርታ ማለፍ ያስፈልጋል። ለዚህ በጋራ መፍትሔ ማምጣት ይቻላል። የችግሩ መንስዔ ነኝ የሚል አካል መፍትሔ ለማምጣት የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም ከችግር የመውጫ መንገዳችን ቁጭ ብሎ መነጋገር፣ እውነታው መቀበልና ይቅር መባባል ናቸው። የደቡብ አፍሪካ የሰላም ሥምምነትን እንደ አብነት እናነሳለን። በዚያ ውስጥ ብዙ አስተማሪ ነገሮች አሉ። ስለዚህ በዳይና ተበዳይ ፊት ለፊት ይቅር መባባል ሲጀምሩ ሰላም ይወርዳል። ይቅርታ ጠያቂና ይቅርታ የሚቀበል ካለ ሰላም ይወርዳል፤ ቂምና በቀል ይረሳል። በይቅርታ የማይፈርስ ተራራ የለም። በዚህ ላይ የእምነት ሊቃውነትና አባቶች፣ እናቶችና ምሑራን ቢለምኑ የመሰማትና የመደመጥ አቅም አላቸው። ባለፉት ዘመናት ተፈጠሩ የተባሉ ግፎችንና በደሎችን በይቅርታ እንባ ማጠብ አለብን። ልብ የሚያርፍበት ሰላም መፍጠር አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያን ሰላም ለመንሳት የውጭ ጣልቃ ገብነት ይታያል። ይሄ ለምን ይሆን?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** ኢትዮጵያ በባህል፣ በሃይማኖት ብሎም በታሪክ ጥንታዊ ሀገር ከመሆኗ የተነሳ በራሷ ብዙ ነገር አላት፤ ለዓለምም ብዙ ታበረክታለች፤ እንደ ጥሬ ሃብት ናት። ዓለምን ወደ መልካም አቅጣጫ ለመውሰድ የሚፈልጉ ካሉ ኢትዮጵያ ሁሉንም ነገር ይዛለች። በዓለም ላይ በብዙ መንገድ አበርክቶዋ ትልቅ ነው። ሆኖም ጥንታዊ እሴት ያላቸውን ሀገራት ማጥፋት ለምን ተፈለገ ሲባል፤ አንድ ጤናማ ያልሆነ ሥርዓትና እንደ ዓለም ሊተገበር የተፈለገ እሳቤ አለ ማለት ነው። ይህን በጥናትና ምርምር ፍንትው አድርጎ ማሳየት ይገባል። በዚህ እሳቤ ጥንታውያንን ማዳከም የፈለጉ ይመስለኛል። ስለዚህ ከእኛ ከሚወስዱት ይልቅ እንደ ስጋት የሚመለከቱን አሉ።

ሌላው ኢትዮጵያን በቅኝ አለመገዛቷን እንደ አደገኛ ሁኔታ እየተመለከቱት ነው። በእርግጥ በአሁኑ ወቅት በባህል ቅኝ ግዛት ውስጥ እየወደቅን ነው። እንደስብዕና የተገነቡ እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ ነው።ኢትዮጵያን ቀና ማለቷ የሚያሰጋቸው ስላሉ ገና ከመቆማችን እንድንቀመጥ፣ ከመነሳታችን እንድንተኛ እየተደረገ ነው። ይህም ከእነርሱ እሳቤ ጋር ስለማይሄድ ኢትዮጵያን ማዳከም ይፈልጋሉ። ስለዚህ ኢትዮጵያን ጨምሮ እነዚህ ጥንታዊት የሃይማኖት፣ ባህል፣ ታሪክ፣ እሴትና ትውፊት መሠረት ያላቸውንም ሀገራት ያናጋሉ።



**አዲስ ዘመን፡- እሳቤው ይህ ከሆነ እንደ ሀገር ምን መሥራት ይጠበቅብናል ?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። «ዩቱዩብ» ላይ የሚሽከረከር አንድ ቪዲዮ አለ። ከሰሐራ በታች ያሉ ሀገራት በማንኛውም ሁኔታ ድሃ ሆነው መቀጠል አለባቸው የሚል አንድ ኒኮላስ የሚባል ኢኮኖሚስት ያቀረበው ሐሳብ አለ። በግልፅ ያስቀመጡትና ያመኑበት ሁኔታ ከቤተሰብ ግንባታ ጀምሮ አካላዊ፣ አዕምሯዊና መንፈሳዊ ግንባታውን ማዳከምን ያካተተ እሳቤ ነው። አዕምሯዊና አካላዊ ብስለትን መገደብ፣ በመንፈሳዊ በጣም መመንደግ የለባቸውም የሚል ነው።

አዕምሯዊ ብስለትና በመንፈሳዊ መመንደግ ካለ የሚቋቋመው አካል የለም። ስለዚህ ይህ እንደ ሀገር እየበዛ ከመጣ ዓላማቸውን ለማሳካት ከቤተሰብ ጀምሮ የተፋለሰ ሥርዓት ለመትከል እየተሯሯጡ ነው። ይህ አንዱ የውጊያ ስልታቸው ነው። ልጅ ወልደው ብቻቸውን ማሳደግ የሚፈልጉ ሰዎች እየተበራከቱ ነው። ይህም ልጅ ከእናት ወይም ከአባት ተነጥለው እንዲያድጉና በተበላሸ ማንነት እንዲመራ እያደረጉ ነው። ሙሉ ስብዕና የሚፈጠርበትን ጋብቻም እያዳከሙት ነው። ስለዚህ በጋብቻ፣ በኢኮኖሚው፣ ሥርዓተ ትምህርቱ፣ ባህል፣ ትውፊትን በሙሉ እየበረዙ ነው።

ኢትዮጵያ ብሎም አፍሪካ የራሳቸው የተፈጥሮ ሃብትና ፀጋ አላቸው። ምዕራባውያን ደግሞ ይህ የላቸውም። ቅኝ ግዛት የመጡትም ዓላማው ለኢኮኖሚያቸው መሠረት ለመጣል ነው። አሁንም ቀጥታ በቅኝ ግዛት ባይኖርም አሁንም የተደገፉት በአፍሪካ ሃብት ላይ ነው። ይህ ሁኔታ እንዲቀየር አይፈለግም።በመሆኑም ሰላም እንድናገኝ አይፈልጉም። ኢትዮጵያም ድሃ እንደተባለች መኖር አለባት፤ አንዱ ጦርነት ሲዘጋ ሌላው የጦርነት ምዕራፍ መከፈት አለበት ብለው የተነሱና በሁሉም መንገድ እንደሚዋጉን በግልጽ ያስቀመጡት መሆኑን በውስጥም በውጪም ያለን ኢትዮጵያውያን ማወቅ አለብን።

እነዚህን ጉዳዮች በደንብ ከተገነዘብን ምን ማድረግ አለብን የሚለውን አይጠፉንም። ዐውዳችንን ቁጭ ብሎ መመልከትና መምከር ይፈልጋል፤ የመጣነበት የታሪክ ዑደት ማጤን፣ ኢትዮጵያ ያላት አቅምና ከውጭ ኃይላት ጋር ያላት ግንኙነት ምን መሆን አለበት፣ በራሳችን እግር የምንቆመው እንዴት ነው የሚለውንና ከጥገኝነት የምንወጣበትን መንገድ ማሰብ ይገባል። አንገታችን ላይ የታሰረውን የጥገኝነት ክር መበጠስ አለብን። ጥገኝነት ክፋቱ፤ እየቻልክ አትችልም፣ አቅም እያለህ አቅም ያሳጣሃል፣መሥራት እየፈለግህ አትሠራም። እየተብሰለሰልክ ትኖራለህ እንጂ ግንዛቤህና ዕውቀትህ ያንተን ችግር አይፈታም። ተምረህ ዕውቀት አግኝተህ እጅህ አምራች ሆኖ፤ አዕምሮህ ተረድቶ ባለህ እውቀትና አቅም ችግሮችህን ልትቀርፍ የማትችል ከመሆን በላይ አስከፊ ገፅታ አለ ብዬ አላስብም። ባርነት ማለት ይህ ነው። ይህን ለመፍታት ከፊትና ከኋላ ያለውን ዐውድ በመመርመር፣ መልክና ቅርጽ በማበጀት፣ ብሎም ነገሮችን በጥልቀት በማየት መፍትሔ ማበጀት ይገባል። ሃይማኖት ጤናማ ማኅበረሰብ ይገነባል። በየትኛውም የእምነት ተቋማት ውስጥ ያለን ሰዎች እንደ ሀገር መጋራት ያለብንን ነገር መጋራትና መነጋገር አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- በሃይማኖታዊ አስተምህሮ ያላችሁን አካፍሉ ይላል። ግን ያለን የምናካፍለው በበዓላት ቀናት ብቻ መገደብ አለበት?**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** በዓል ብዙዎች በቤታቸው ያከብራሉ፤ ከተቸገሩት ጋር የሚካፍሉት ጥቂቶች ናቸው። ነገር ግን የተቸገሩትን ማገዝ ያለብን በበዓላት ወቅት ብቻ አይደለም። አንድ የአረዳድ ስህተት ያለ ይመስኛል። የተቸገረን ሰው ማልበስ ወይንም ማብላት እንደ ጽድቅ ሆኖ እየተቆጠረና ነው። እውነት ነው ጽድቅ ይገኝበታል። ግን እነርሱ ከእኛ ማንነት ውጭ ሆነው እነርሱን ረድተንና ጠቅመን እኛ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንወርሳለን የሚለው አደገኛ አታያይ ነው። እነርሱን መጠቀሚያ ማድረግ ነው። ልብስና ትንሽ ሳንቲም ሰጥቶ እነርሱን እንደ መጠቀሚያ ማሳብ አይገባም።

ሰው የምንም እምነት ተከታይ ቢሆንም፤ ወይንም እምነት አልባም ቢሆን ክቡር ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ ስዕብናን እንደ እቃ ወይንም መሣሪያ መጠቀም አይገባም። እንደ ክርስትናም ያለው አስተምህሮ ይህ አይደለም። የተቸገሩ ሰዎችን የምንረዳው የእኛን ማንነትን እውን ለማድረግ ነው። እነዚያ ሰዎች የእኛ አካል ናቸው፤ስዕብናችን አካል ናቸው። ጎዳና የወደቁ አረጋውያን ሀገር ያቀኑ ናቸው። ለእኛ ማንነት የእነርሱ ላብና ደም አለበት።

የተቸገሩ ሰዎችን ማሰብ ሰብዓዊ ምንነት ሙሉዕ ማድረግ ነው። በግራ እጅ ቀኝ እጅ እንደማከም ነው። የሰውነትና የማንነት አካል ናቸው። ስለዚህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በዓል ሲመጣ ሳይሆን ሁሌም ልናስባቸውና ልናግዛቸው ይገባል። እንደ ሀገርም ማስቀደም ያለብን እነርሱን ነው። ከጎዳና ላይ ሕፃናትና አረጋውያንን ማንሳትና መሰብሰብ አለብን። ከንግግር በላይ ተግባራችን መቅደም አለበት። ሀገር ግንባታም የሚጀመረው ከዚህ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**ቀሲስ ዶክተር መዝገቡ፡-** እኔም አመሰግናለሁ። መልካም የልደት በዓል እንዲሆንልን እመኛለሁ።

# ማህደረ ጤና

# የህክምናን አገልግሎቱን በሌላ አማራጭ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ዶክተር ረቤካ መስፍን በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ ጠቅላላ ሃኪም ናት። በዚሁ ሆስፒታል በተቋቋመው ሴንተር ፎር ፕሮፌሽናል ኤንድ ኢንስቲትዩሽናል ዴቬሎፕመንት ውስጥ የፕሮጀክትና ቢዝነስ ዴቬሎፕመንት ፕሮግራም ኦፊሰር ሆናም ታገለግላለች።

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የእሳት፣ የትራፊክ፣የኤሌክትሪክና ሌሎችም ድንገተኛ አደጋዎች እንደሚከሰቱ የምትናገረው ዶክተር ረቤካ፤ ከነዚህ ድንገተኛ አደጋዎች መካከል በተለይ ደግሞ በተሽከርካሪ የሚደርሰው አደጋ ቀዳሚውን ስፍራ እንደሚወስድ ትጠቁማለች።

በሀገሪቱ ብሎም በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ ለነዚሁ ድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ የሚሰጡ የተለያዩ ጤና ተቋማት ቢኖሩም ከአደጋው ብዛትና ስፋት አንፃር በቂ እንዳልሆኑ ትናገራለች። ተቋማቱ ለድንገተኛ አደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችላቸውን የባለሙያ ቁጥርና የህክምና መሳሪያዎችን እንዳላሟሉም ነው የምትጠቁመው።

እርሷ በምትሰራበት በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ የድንግተኛ አደጋዎች ህክምና መስጫ ማእከል ምንም እንኳን በበቂ ባለሙያና የህክምና መሳሪያዎች የተሟላ ቢሆንም ባለው የባለሙያ ቁጥርና የህክምና መሳሪያ ለአደጋው ምላሽ በመስጠት ሂደት ክፍተቶች እደሚታዩም ትጠቅሳለች።

‹‹በቅርቡ ከእስራኤል ሀገር ፖሪያ ሜዲካል ትምህርት ቤት በመጡ የድንገተኛ ህክምና ባላሙያዎች ቡድን በድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የአራት ቀናት ስልጠና አግኝቻለሁ›› የምትለው ዶክተር ረቤካ፤ የህክምና አገልግሎቱ በኢትዮጵያ እየተሰጠ ቢሆንም አሰልጣኞቹ አገልግሎቱን ያሳዩበት መንገድ ከእኛ ሀገር የተለየ ነው ትላለች።

በተለይ ደግሞ በድንገተኛ አደጋ ህክምና ወቅት አንድ ነገር ቢከሰት በምን መልኩ ታካሚውን መንከባከብና ተገቢውን የህክምና አገልግሎት ሰጥቶ ወደጤና መመለስ እንደሚቻል አይን በሚገልጥ መልኩ ከእነርሱ ሙያዊ እውቀት እንዳገኘች ታስረዳለች። በተለይ ደግሞ በድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ጨብጨያለሁ ብላ ታስብ እንደነበር፤ ነገር ግን ከስልጠናው በኋላ አገልግሎት አሰጣጡን ከተለያዩ አንግሎች እንድትረዳ እንዳስቻለት ታብራራለች።

በተለይ የህክምና ቡድኑ አባላት በዚሁ ዘርፍ የተለያዩ ልምዶች ያሏቸው በመሆኑና በተለያዩ ሀገራት በመንቀሳቀስ ያላቸውን ልምድና ተሞክሮ ያካፈሉ እንደመሆናቸው በዘርፉ ያላትን የእውቀትና ክህሎት አድማስ እንዳሰፋላትም ነው ዶክተር ረቤካ የምትናገረው።

ይህም ቀደም ሲል በድንገተኛ አደጋ ህክምና ምላሽ አሰጣጣ በነበራት እውቀት ላይ ተጨማሪ ግንዛቤ እንዲኖራት ማስቻሉንም ትጠቁማለች። በተለይ ደግሞ በደንገተኛ አደጋ ህክምና አሰጣጥ ሂደት ምን አይነት ችግር ሊገጥም እንደሚችልና ይህን ችግር እንዴት መፍታት እንደሚቻል ከህክምና ቡድኑ በቂ ክህሎትና እውቀት እንዳገኘችም ትገልፃለች።

የስልጠና አሰጣጡም በሲሙሌሽንና በትክክልም ታካሚ በሚመስሉ አሻንጉሊቶች የተደገፈ መሆኑንም ጠቅሳ፤ እንስሳትንም ጭምር እንደታካሚ በመጠቀም አደጋ ቢደርስ እንዴት ማከምና ህይወት ማዳን እንደሚቻል እንደተማረች ታስረዳለች።

በኢትዮጵያ የድንገተኛ አደጋ ምላሽ የሚሰጡ የህክምና ተቋማት እንዳሉ ሆነው በውስጣቸው ለዚሁ ህክምና አገልግሎት የሚያግዙ የህክምና መሳሪያዎች ብዙም እንደሌሉ የምትናገረው ዶክተር ረቤካ፤ ይህን በማየት የህክምና ቡድኑ ድጋፍ ለማድረግ ቃል እንደገቡም ነው የምትጠቅሰው። በስልጠናው ወቅት ሲጠቀሙባቸው የነበሩትን አንዳንድ እቃዎችን አስረክበው ለመሄድ ዝግጁ መሆናቸውንም ትገልፃለች።

ከሁሉ በላይ ግን በኢትዮጵያ የድንገተኛ አደጋ ህክምና አገልግሎትን በተሟላ መልኩ ለመስጠት አሁንም ብዙ የሚቀሩ ነገሮች ቢኖሩም ባለው ሀብት ሌሎች አማራጭ መንገዶችን በመጠቀም የህክምና አገልግሎቱን የተቃና ማድረግ እንደሚቻል ትልቅ ትምህርት መውሰዷን ትናገራለች።

ስልጠናው በድንገተኛ አደጋ ህክምና አገልግሎት ወቅት ‹‹ይሄ ስለጎደለ ይህን አይነት ህክምና መስጠት አይቻልም›› የሚለውን የሰበረና አማራጮች ሁሌም እንዳሉ ግንዛቤ ያስጨበጣት ስለመሆኑም ነው የምታስረዳው።

‹‹የህክምና ቡድኑ ከሰጠው የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በቂ እውቀትና ክህሎት አዳብሪያለሁ›› የምትለው ዶክተር ረቤካ፤ የህክምና መሳሪያዎች እጥረት እንዳለ ሆኖ መሳሪያዎቹ ቢሟሉ ብዙ መስራት እንደሚቻልና ባይሟሉም ባለው መሰሪያ ተጠቅሞ ብዙ ማድረግ እንደሚቻል ከስልጠናው እንደተረዳች ትናገራለች።

በሌላ በኩል ደግሞ አሁን የተጀመረው ስልጠና በኢትዮጵያና እስራኤል መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር ከድንገተኛ አደጋ ህክምና በዘለለ በሌሎችም የጤና ዘርፎች ያሉ ትምህርቶችን ለመቅሰም እድል እንደሚሰጥም ትጠቁማለች። ኢትዮጵያውን ከእስራኤላውያን በድንገተኛ አደጋ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪ ትልቅ ትምህርት እንደወሰዱ ሁሉ እስራኤላውያንም ከኢትዮጵያ ተመሳሳይ ትምህርት መውሰዳቸውን ትጠቅሳለች።

የህክምና ቡድኑ ስልጠናውን የሰጠው በንድፈ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር በመሆኑ በስራ ላይ ተግበራዊ የሚሆንና እርሷም ያገኘቸውን የንድፈ ሃሳብና የተግባር ትምህርት በስራዋ ላይ ተግበራዊ እንደምታድርግም ነው የምትናገረው። እንዲህ አይነቱ ስልጠና በተመሳሳይ ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን የህክምና ባለሙያዎች ቢደርስ በዚሁ ህክምና ዘርፍ ያለውን ችግር በመጠኑም ቢሆን መቅርፍ የሚያስችል መሆኑንም ትጠቁማለች።

ዶክተር ባራክ ሊቪት እስራኤል ሀገር በሚገኘው ፖሪያ ሜዲካል ሴንተር አጠቃላይ የቀዶ ህክምና ክፍል የድንገተኛ አደጋ ህክምና ዩኒት ዋና ዳይሬክተር ናቸው። በዚሁ ክፍልም የድንገተኛ አደጋ ቀዶ ሀኪም ሆነው ይሰራሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት ከዚሁ የህክምና ማእከል የተውጣጣው ቡድን ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ዋነኛ ምክንያት በኢትዮጵያውያንና በእስራኤላውያን የህክምና ባለሙያዎች መካከል ያለውን እርስ በርስ ግንኙነት በሁለንተናዊ መልኩ ለማጠናከር ነው።

በተጨማሪም የህክምና ቡድኑ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በሁለቱ የህክምና ባለሙያዎች መካከል በተለይ ደግሞ በጤው ዘርፍ ያላቸውን ልምድና ተሞክሮ አንዳቸው ለሌላቸው እንዲያጋሩ ብሎም እንዲማማሩ ያስችላል።

ወደ አፍሪካ ሀገራት በበጎ ፍቃደኝነት ሙያቸውን ለማካፈል ሲመጡ ኢትዮጵያ ሶስተኛቸው መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ባራክ፤ በኢትዮጵያና በእስራኤል መንግስትታ መካከል ባለው ጠንካራ ግንኙነት ተነሳሽነቱን ወስደው እንደመጡ ይናገራሉ።

በድንገተኛ አደጋዎች ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከአዲስ አበባ ከተማ ጤና ተቋማት ለተውጣጡና በዚሁ ዘርፍ ላይ ለሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ ለአራት ቀናት ከሌሎች የስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ስልጠናውን ሲሰጡ መቆየታቸውንም ይጠቁማሉ።

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በነበራቸው የአራት ቀናት ቆይታ ኢትየጵያውያን ሀኪሞችና ነርሶች በድንገተኛ አደጋዎች ህክምና ዙሪያ ያላቸው ልምድና ተሞክሮ ብሎም ሙያዊ ብቃታቸው ከጠበቁት በላይ እጅግ እንዳስደነቃቸው ይናገራሉ። በዚሁ ህክምና ዘርፍ በደምብ የሰለጠኑ መሆናቸውንና ለስራውም የሚመጥኑ ስለመሆናቸው እንደተረዱም ይጠቁማሉ።



**ዶክተር ረቤካ መስፍን፤**



**ዶክተር ባራክ ሲቪት፤**

በድንገተኛ አደጋዎች የህክምና ዘርፍ በእስራኤልና በካናዳ ትምህርታቸውን መከታተላቸውን የሚናገሩት ዶክተር ባራክ፤ ኢትዮጵያውያንም በዚሁ የህክምና ዘርፍ ያላቸው እውቀትና የክህሎት ደረጃ ሌላው አለም ካለው ጋር የሚስተካከል እንጂ የማያንስ መሆኑን እንዳወቁ ይገልፃሉ። አዳዲስ አውቀት የመቀበል ዝንባሊያቸውም ከፍተኛ በመሆኑ የህክምና ቡድኑ ስልጠናውን ሲስጣቸውም ብዙም እንዳለተገሩም ነው የሚናገሩት።

በስልጠናው በአዲስ አበባ ከሚገኙ የጤና ተቋማት የተውጣጡና በተለያዩ ደረጃዎች በድንገተኛ አደጋዎች ህክምና አገልግሎት ላይ የሚሰሩ ነርሶችና ሀኪሞች መሳተፋቸውንና የስልጠና መስጫ ማእከሉን ያመቻቸው ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ ማመቻቸቱን ይጠቁማሉ። በዚህም የህክምና ቡድኑ በድንገተኛ አደጋ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ በኩል ያለውን ልምድና ተሞክሮ ለሰልጣኞች ማካፈሉን ይገልፃሉ።

እንደ ዶክተር ባራክ ገለፃ የህክምና ቡድኑ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የመጀመሪያው ሲሆን በዋናነት በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ስለሚሰጡ ህክምና አይነቶች፣ ቀዶ ህክምናዎችና በአደገኛ ጉዳቶች ወቅት ስለሚሰጡ የህክምና ምላሾች ዙሪያ ያለውን ልምድና ተሞክሮ አካፍሏል።

ግማሹ የስልጠና ክፍለ ግዜ ትምህርታዊ፣ ተግበራዊና የቀዶ ህክምና አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ባሉ የንድፈ ሃሳብ ትምህርቶች ላይ አተኩሯል። በሌላው የስልጠና ክፍለ ግዜ ደግሞ ሰልጣኞች /trauma simulation/ በተግባር የተደገፈ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ፣ የቀዶ ህክምና ሂደትና ትምህርት እንዲወስዱ ተደርጓል።

በመጨረሻም ሰልጣኞች በንድፈ ሀሳብና በተግባር የወሰዱትን ትምህርት በማቀናጀት ከዚህ ቀደም የነበራቸውን እውቀትና ክህሎት በማጣመር እንዲያሳዩ ተደርጓል።

በየትኛውም ሀገር በድንገተኛ አደጋዎች ህክምና አገልግሎት አስጣጥ ሂደት ክፍተቶች አሉ። በኢትዮጵያም የሚታየው ክፍተት ከሌላው አለም የተለይ አይደለም። ስልጠና በተሰጠበት የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በሚገኘው የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና ማእከል ውስጥ አንዳንድ ግዜ በአገልግሎት አሰጣጥ ስርአቱ ላይ ሌላ ግዜ ደግሞ የህክምና መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለመኖር ክፍተቶች ይታያሉ። ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ክፍተት ሌላው ሀገር ላይ ከሚታየው የተለየ አይደለም።

ከዚህ አንፃር የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ስርአቱን በማሻሻልና አገልግሎቱን ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ የህክምና መሳሪያዎችን በማሟላት ለድንገተኛ አደጋዎች የሚሰጠውን ምላሽ ማስተካከል ይቻል። በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና አገልግሎትን የሚሰጡ የጤና ተቋማት ያላቸውን ሃብት በመከፋፈልና በሚፈለገው ቦታ ላይ በመመደብ ያለባቸውን ችግር ማቃለል ይችላሉ።

በተለይ ደግሞ በይበልጥ ህይወት ሊያድኑ የሚችሉ የህክምና መሳሪያዎችን በአግባቡ በመጠቀምና ከሌሉም በማሟላት በድንገተኛ አደጋ ህክምና ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታት ይቻላል። በተቃራኒው ደግሞ ብዙም ወጪ የማያስወጡና ለህክምና አገልግሎቱ ብዙም የማያስፈልጉ የህክምና መሳሪያዎች ላይ የሚወጣውን በጀት መመጠን ያስፈልጋል።

በድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤላውያን የሚጋሯቸው በርካታ ተሞክሮዎች አሉ። በተለይ ደግሞ በእስራኤል ያለው የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና አገልግሎት አሰጣጡ ምንም እንኳን ፍፁም ባይሆንም መልካም የሚባል በመሆኑ ውጤታም የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ በመዘርጋት ሂደት ኢትዮጵያውያን ከእስራኤላውያን ብዙ ትምህርት ሊወስዱ ችላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤላውያን ለጤና ስርአቱ የሚመድቡት በጀት አነስተኛ ነው። ይህም ከኢትዮጵያውያን ጋር ያመሳስላቸዋል። ነገር ግን እስራኤላውያን በጀቱን ለምፈለገው ተግባር በአግባቡ በማዋል ላይ ጥሩ በመሆናቸው ኢትዮጵውያን ከዚህ ጥሩ ትምህርት ሊወስዱ ይችላሉ።

ዶክተር ባራክ እንደሚሉት በእስራኤል በርካታ የጦርነት ቀጠናዎች አሁንም እንዳሉና ድንገተኛ የሽብር ጥቃት ቢደርሱ እንኳን ለዚህ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና ማእከላት እንዳሉ፤ በእንዲህ አይነቱ ክስት ወቅት ሀገሪቱ ሰፊ ተሞክሮ አላት። በጦተርነት ወቅት የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና አገልግሎት ስርአት ውጤታማ ከሆነ በአገልግሎቱ የበርካታ ሰዎችን ህይወት ማዳን ይቻላል። ይህም የሚሆነው በርካታ የሚመለከታቸው ተቋማት ተቀናጅተው ሲሰሩና ሀብትን በአግባቡ ከፍፋሎ ጥቅም ላይ ማዋል ሲቻል ብቻ ነው።

በኢትዮጵያም በህክምና ዘርፉ ያለውን እውቀት፣ክህሎትና ሀብት በአግባቡ መድቦ በመጠቀም ጦርነቱ ካስከተለው የአካል ጉዳት በኋላ ያለውን የስነ ልቦና ስብራት ማከም ይቻላል። በዚህም አስራኤልና ኢትዮጵያ የቆየ ግንኙነት ያላቸው እንደመሆኑ እስራኤል ለኢትዮጵያ በህክምናው ዘርፍ እውቀትና ልምድን ከማካፈል ጀምሮ የህክምና መሳሪያዎችን በማቅረብ የምታደርገውን ድጋፍ አጠናክራ ትጠቀጥላለች።

በኢትዮጵያ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ቁጥር አነስተኛና ውስንና በከተሞች አካባቢ ብቻ የተገደበ መሆኑ ይነገራል። ካለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር አንፃርም ተመጣጣኝ የህክምና ተቋማትና በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሞያዎች አሉ ተብሎ አይታሰብም።

ከዚህ አንፃር ሀገሪቱ ባላት ውስን የድንገተኛ አደጋ ህክምና ተቋማትና የጤና ባለሙያዎች ዜጎቿ ተገቢውን የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የጎደለውን ሞልታ ያላትን ሀብት በተገቢው ቦታ መድባ መስራት ይጠበቅባታል።

ይህ ከሆነ በዚሁ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የሚታዩ ችግሮች ተቀርፈው ስርአቱ እስኪስተካከል ድረስ በድንገተኛ አደጋዎች የሚቀጠፉ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን ህይወት ማዳን ይቻል። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያውያን የህክምና ባለሙያዎች ከእስራኤላውያን ብዙ ትምህርት ሊቀስሙ ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "ሰላም ለሀገራችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ"

### የበዓሉ ልደት ብሥራት፤

ይህ ዛሬ እያከበርነው ያለነው ታላቅ መንፈሳዊ በዓል ለክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ ልዩ ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የድነት ተልዕኮውን ለመፈጸም ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደበት ዕለት መሆኑ ብቻ ሳይሆን የአዲስ ኪዳን መሠረት የተጣለበት ሁነኛ የመታሰቢያ በዓልም ነው፡፡ ጸሐፊው መላውን የክርስትና እምነት ቤተሰቦች "እንኳን በሰላም አደረሳችሁ!" በማለት ምኞቱን የሚገልጸው ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን ተፈጽመው የነበሩ አንዳንድ ታሪካዊ ክስተቶችን በእግረ መንገድ በማስታወስ ጭምር ነው፡፡

ከብሉይ ኪዳን አሥራው መጻሐፍት የመጨረሻው እንደሆነ በሚታመነው ትንቢተ ሚልክያስና በአዲስ ኪዳኑ የመጀመሪያ መጽሐፍ በማቴዎስ ወንጌል መካከል (በመሃከላቸው አዋልድ በመባል የሚታወቁ መጻሕፍት ተጽፈዋል የሚል መከራከሪያ እንዳለ ሆኖ) ያለው የዘመን ርቀት አራት መቶ ዓመታት እንደሚሸፍን በርካታ የሥነ መለኮት ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ እነዚህ አራት ክፍለ ዘመናት በዋነኛነት የሚታወቁት "የእግዚአብሔር የዝምታ ዘመናት" እየተባሉ ነው፡፡ እንደ ዘርፉ ተመራማሪዎች ማብራሪያ ከሆነ የዝምታው መገለጫዎች በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩትም ከዚህ ጽሐፍ ዓላማ ጋር እጅግም ስለማይጎዳኙ ታሪኩን የጥቁምታ ያህል ለማስታወስ እንሞክራለን፡፡

ለመሆኑ "እግዚአብሔር ዝምታን ያውቅበታል ወይ? እንደምንስ አስጨክኖት ለአራት መቶ ዓመታት ያህል ሕዝቡን ባስለመዳቸው መንገድ ሊናገራቸው አልፈቀደም? ወዘተ." ለሚሉት ጥያቄዎች በርካታ ታሪካዊና ሥነ መለኮታዊ ምክንያቶችን መደርደር ቢቻልም "ዝም ለማለት ጊዜ አለው፤ ለመናገርም ጊዜ አለው" (መጽሐፈ መክብብ 3፡7) የሚለውን ቅዱስ ቃል በማስታወስ፤ በራሱ ሁሉን አወቅ ባህርይ ፈጣሪ "ዝምታን" መርጦ አምላካዊ ተግባሩን ለማከናወን ምርጫው ቢያደርግ ሊደንቀን አይገባም የሚለው ምላሽ ተዘውትሮ ይደመጣል፡፡

"እግዚአብሔር ስለ ምን ዝም ሊል ቻለ?" ተብሎ ለሙግት መደፋፈሩም ጉንጭ አልፋነት ነው፡፡ ዋናው ጉዳይ ምንም ይሁን ምን በግለሰብም ሆነ በሀገር ደረጃ ፈጣሪ በድርጊታችንና በበደላችን ምክንያት በዝምታና በፈቀደው ማስተማሪያ እንዳይቀጣን ወይንም እንዳይፈርድብን ከበደላችንና ከኃጢያት መመለሱ ይበልጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

ይልቅስ "እግዚአብሔር ዝምታውን ሰብሮ" ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት በአዲስ ዘመን መባቻ የአይሁዳዊያኑ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሕይወት ምን መልክ እንደነበረው በጥቂቱም ቢሆን አስታውሶ ማለፉ ለዋናው ሀገራዊ የመዳረሻ ሃሳባችን ጥሩ መደላድል ሊሆን ስለሚችል ዋና ዋና አንኳር ክስተቶችን ለመጠቋቆም እንሞክር፡፡

እስራኤላዊያን አይሁዶች እንደ ሕዝብ ተስፋ በተገባላቸው ምድር ላይ ለመሰባሰብና ሀገረ መንግሥታቸውን ከመሠረቱም በኋላ የደረሰባቸው መከራ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በስፋት ተዘርዝሮ እናነባለን፡፡ በጠላቶቻቸው ተደጋጋሚ አሸናፊነት የባርነትን ኑሮ በሚገባ አልፈውበታል፡፡ በመሳፍንቶቻቸው ዘመን የነበረው የርሃብና የእርስ በእርስ መቆራቆዝም አድቅቋቸዋል፡፡ በምርኮ ተሰደው ሀገር አልባ እንዲሆኑ ተፈርዶባቸዋል፡፡ የሃይማኖታቸው ማዕከላዊ ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ የሚቆጠረው ቤተ መቅደሳቸው በማራኪዎቻቸው የፍርስራሽ ክምር ሆኗል፡፡ ሀብታቸው ተበዝብዟል፡፡ ክርስታቸው ተነቅለውም በመላው ዓለም ሊበተኑ ግድ ሆኗል፡፡

በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ዝርዝሩን እንደምናነበው ባቢሎናዊያን (ቅ.ል.ክ 423 - 372) ነገደ አይሁድን ማርከው አሰቃይተዋቸዋል፡፡ የሜዶ ፋርስ ነገሥታትም (ቅ.ል.ክ 372 - 348) ለባርነት አፍልሰው አስገብረዋቸዋል፡፡ የዚህ ገናና መንግሥት ኃይል ሲዳከምም የግሪክ መንግሥት አንሰራርቶ (ቅ.ል.ክ 371 - 141) በብረት በትር ተቀጥቅጠው ተገዝተዋል፡፡ ባህላቸውና ቋንቋቸውም በሄለናዊያን ተጽእኖ ሥር ውድቆ የማንነታቸውን ክብር እስከማጣት ደርሰዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የመጀመሪያዎቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ሊሆን ግድ ሆኗል፡፡

ሥልጣን አንዴ ወዲህ አንዴ ወዲያ መገለባበጡ የተለመደ ነውና የግሪኮች ጉልበት መላላቱን ያስተዋለው የሮም መንግሥትም (ቅ.ል.ክ ከ69 ጀምሮ) የተረኛነቱ ጊዜ ደርሶ ኃይላቸውን በማሽመድመድ ሌላ ጌታ ሆኖ አስገብሯቸዋል፡፡ በጭካኔያቸው ወደር አልተገኘላቸውም የሚባሉት ሮማዊያን ጌቶቻቸው ካስገበሯቸው በኋላ የፈጸሙባቸው ግፍና የጫኑባቸው የመከራ ዓይነቶች በእጅጉ የሚሰቀጥጡና የዘመኑን የጠለሸ ታሪክ በግልጽ የሚወክሉ ናቸው፡፡ ክርስቶስ የተወለደው ይህን መሰሉ ውጥንቅጡ በበዛበት ዘመን ነበር፡፡

ጆሲፈስን የመሳሰሉ የዘመኑ ታሪክ ጸሐፊዎች በጽሑፍ ያስተላለፏቸው ሰነዶችና የብራና ጥቅልሎች እንደሚመሰክሩት ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ተቀራራቢ ዓመታት ውስጥ በቄሳራዊያን ገዢዎቻቸው የግፍ ድርጊት ምክንያት በርካታ አይሁዳዊያን በጭካኔ ተጨፍጭፈዋል፡፡ የሮም መንግሥትን ትቃወማላችሁ እየተባሉም ብዙዎች በአደባባይ ተሰይፈዋል፡፡ ከፈሪሳዊያንና ከሰዱቃዊያን የአይሁድ እምነት አስተማሪዎችና መምህራን መካከልም ብዙዎች ተገድለዋል፡፡

እነዚህን መሰል መከራዎችና ግፎች የተሸከመው የአይሁድ ሕዝብ ምንም እንኳን ሰማይ ምድሩ እንደ ወስከንባይ የተደፋበት ቢሆንም ተስፋ ቆርጦ ለጠላቶቹ አልተበገረም፡፡ አምላካቸው ያህዌም እስከ መጨረሻው በዝምታው ሊገፋ አምላካዊ ፍቅሩ አላስቻለውም፡፡ ስለሆነም ከአራት መቶ የዝምታ ዓመታት በኋላ ቀደም ሲል በነብያቱ የተነገሩ የተስፋና የትንቢትን መልእክቶችን ለመፈጸም ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ተጸንሶና ሥጋ ለብሶ ከቅድስት ድንግል ማርያም እንዲወለድ ሉዓላዊው አምላክ አንድያ ልጁን መሲህ አድርጎ ወደ ምድር ላከ፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት በዚያ ሌሊት የመላእክት ሠራዊት ፡- "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድር፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ" በማለት የልደቱን የምሥራች ያበሰሩት በሌሊት መንጎቻቸውን ሲጠብቁ ላደሩት እረኞች ነበር፡፡ ለዘመናት መከራና ፍዳ ሲያስተናግዱ ለኖሩት ግፉዓን ይህ የምሥራች ትርጉሙ ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡

ተስፋቸው ወድቆና እግዚአብሔር ረስቶናል "በዝምታውም ቀጥቶናል" ባሉበት በዚያ አስጨናዊ ወቅት የምሥራች ብሥራት መስማት ምን ያህል ከፍ ያለ የትድግና መገለጫ እንደሆነ ለመገመት አይከብድም፡፡ የክርስቶስ መወለድ የትንቢቶች ሁሉ ፍጻሜ ማረጋገጫ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች ሁሉ የተገባው የመጭው አዲስ ዘመን አዲስ ኪዳን ማብሰሪያም ጭምር ነበር፡፡

እውነታው ይህን ይምሰል እንጂ ይህ አምላካዊ የተስፋ ብርሃን ለብዙ አይሁዳዊያን ሊበራላቸውና እንደ በረከት ሊቀበሉት አልፈለጉም፡፡ አለመፈለግ ብቻም ሳይሆን የሰውን ሥጋ ልብሶ በመካከላቸው የተገኘውን የሰላም አምላክ "የሰላም ግብዣ ባቀረበላቸው" እንደምን በጭካኔ ተነሳስተው ለመስቀል ሞት አሳልፈው እንደሰጡት በክርስትና አማኒያን ዘንድ በሚገባ ይታወቃል፡፡ ይኼኛውን ታሪክ በተመለከተ በዕለተ ፋሲካ የምንመለስበት ይሆናል፡፡

### "ሀገራዊው የአዲስ ኪዳን አዲስ ዘመን መባቻ"

ኢትዮጵያዊያን የክርስትና እምነት ተከታዮች ይህንን የዛሬውን የጌታችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት የሚያከብሩት ምናልባትም እንዳለፉት ዘመናት በተለመደ የባህል አከባበር ወግና ሥርዓት ብቻ እንደማይሆን ይታመናል፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታትና ወራት ሀገራችን በምን ዓይነት የእርስ በእርስ መራራ ጦርነት ውስጥ እንዳለፈች በፍጹም የሚዘነጋ አይደለም፡፡

ዓላማ ቢስ በሆነ ጦርነትና የሽምቅ ውጊያ ደማቸው በከንቱ የፈሰሰው ዜጎቻችን ቁጥር በአግባቡ ተሰልቶ "ይህን ያህል ነው" የሚለው ሪፖርት ገና ለሕዝቡ ይፋ አልሆነም፡፡ በሚሊዮን ይቆጠር ወይንም በመቶ ሺህዎች እውነቱ ይፋ ሲሆን የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡ ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉት ዜጎች ቁጥርም እንዲሁ በዋዛ በእርግጠኛ አሀዝ የሚገለጥ አይደለም፡፡

የወደመው የዜጎችና የመንግሥት ንብረትም በገንዘብ ተተምኖ ጠቅላላ ግምቱ "ይህን ያህል ቢሊዮን" ይገመታል ለማለት የዓመታት ሥራ ሳይጠይቅ አይቀርም፡፡ ለተመን የማይመቸው የዜጎች የሥነ ልቦና ቀውስ፣ የፈሰሰው የንጹሐን ደምና እምባ በቁጥርም ሆነ በስፍር ከቶውንም ሊለካ አይችልም፡፡

በአጭሩ ያለፉት ዓመታት ለኢትዮጵያ የመከራና የስቃይ ዓመታት ነበሩ ብሎ መደምደሙ ይቀላል፡፡ የውስጥ የፖለቲካ ትርምሱን፣ የኑሮውን ጫናውን የብረት ቀንበር፣ የውጭ ጠላቶችን ሴራና ተንኮል፣ በእኩይ የዲፕሎማሲ ጫና የተረባረቡብንን በሙሉ ስሌት ውስጥ እናስገባ ብንል በምንም ዓይነት መለኪያና መስፈሪያ የጉዳቱን ተመን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

"የዛሬው ይበልጥ አንዘረዘረኝ" እንዲል ባለ ሀገሩ ወገኔ፤ የትናንቱ የሀገራችን ታሪክም ቢሆን እንደ ምንጭ ውሃ የኮለለ፣ እንደ ማር የጣፈጠ አልነበረም፡፡ በጥቂቱ እናስታውሰው፡- ኢትዮጵያ እንደ ሉዓላዊ ሀገር ተረጋግታና ሰክና ኖራለች የሚባልላቸው ዘመናት ከመከራዋና ከፈተናዋ ዘመናት ጋር ሲነጻጸሩ በእጅጉ አናሳ እንደሆኑ ማረጋገጫችን በጥቁር ቱቢት የተለበጠው መልከ ብዙው የሀገራዊ ታሪካችን ውሎ ነው፡፡

ባእዳን ወራሪዎች ሉዓላዊ አንድነታችንንና ድንበራችንን ለመዳፈር ያልሞከሩበት ዘመን አልነበረም፡፡ በአያት በቅድመ አያቶቻችን ዘመን ብቻም ሳይሆን፤ በእኛ ዘመንም በስንቱ ፈተና ውስጥ ለማለፍ እንደተገደድን የበቀደሙ ታሪክ ሊዘነጋ የሚችል አይደለም፡፡ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ተንበርካኪነት ሳይሆን በአንበርካኪነት ምሥጢር የጸና ስለሆነ ወራሪና ተስፋፊ ጠላቶቻችን በሙሉ ወደመጡበት የተመለሱት በፍጥነት እርምጃ እየገሰገሱ ሳይሆን "የወኔ ብራኳቸው ተሰብሮ" በእንፋቅቅ ዳዴ እያሉ ነበር፡፡

ባዕዳኑን ወራሪ ጠላቶች በመራራ መስዋዕትነት ለመመከትና ድል በድል ላይ ለመረማመድ የተቻለውን ያህል ተፈጥሮን አስገብረን ከድህነትና ከርሃብ ግዞት ነፃ ለመውጣት ግን ወኔና ቁርጠኝነት አልነበረንም፡፡ በዚህም ምክንያት በዓለም ማኅበረሰብ ፊት የሀገራችን መታወቂያ እንደምን የከፋ እንደነበር የምናስታወሰው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ የትናንትናና የትናንት ወዲያዎቹ ሀገራዊ ፈተናዎቻችንና መከራዎቻችን ያነሱ ይመስል ዛሬ እያለፍንባቸው ያሉት አበሳዎች ምን ያህል ዋጋ እያስከፈሉን እንዳሉ መዘርዘሩ "የአዋጁን በጓዳ" እንዳያሰኝ እናልፈዋለን፡፡

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው የዜጎች ሞትና መፈናቀል፣ የንብረት መውደምና የእርስ በእርስ ሽኩቻችን የት አድርሶ ወዴት እንደተመለሰን "ጣዕሙኑ" ገና ስላለቀቀን "ጣታችንን የምንጠቁምባቸው" ሀገራዊ ጉድፎቻችን አበዛዛቸውና ዓይነታቸው ለእኛም ሆነ ለባዕዳን ታዛቢዎች "ዕንቆቅልሽ" እንደሆኑብን መከረማችን አይዘነጋም፡፡

በዚህ ውጥንቅጡና ቀወሱ በበዛበት ሀገራዊ ሁኔታ ውስጥ እያለን ነው ስለ ሰላም ተነጋግረን ወደ መግባባት ለመቀራረብ የተሞከረው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ይህንን የልደት በዓል እያከበሩ ካሉ የዓለም ሀገራትና ሕዝቦች ይልቅ ለእኛይቱ ኢትዮጵያና ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድር፣ ለሰውም በጎ ፈቃድ" (ሉቃስ 2፡14) የሚለው የመላእክቱ የምሥራች ይበልጥ ትርጉም ያለው ይመስለናል፡፡

"እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ስለምን ዝም ይላታል? የመከራችን ማብቂያውስ መቼ ነው? እስከ መቼስ ፈጣሪ ፊቱን አጥቁሮብን እንዘልቀዋለን?" በማለት በየግላችንና በየቤተ እምነታችን እግዚአብሔርን ስንወቅስ መከረማችንን አንክድም፡፡ በየደጃ ሰላሙና በየመስጊዱ የፈሰሰው የእናቶችና የአባቶች እምባ ለዚህ አገላለጽ በአብነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ሰላምን ተርበን፣ ሰላምን ተጠምተን፣ ሰላም ብርቅና ድንቅ ሆኖብንና የሌሎች ሀገራትንና ሕዝቦችን ሰላም እያስተዋልን የቀናንባቸው ዓመታት ርዝመት ይህን ያህል ይሆናል ተብሎ የሚወሰን አልነበረም፡፡ በዘመናችንና በእድሜያችን በሙሉ ስንመኝ የኖርነው፣ ስንቃትት የባጀነው "የሰላም ያለህ!" እያልን ነበር፡፡ ዛሬም ሰላማችን ምልዑ ነው ባንልም አበረታች ለመሆኑ ግን የምንክደው አይደለም፡፡

ሰላም በምልዓት የሚረጋጠው የዜጎች በጎ ፈቃድ ሲታከልበት እንጂ ሰላምን በመናፈቅ ብቻ ምኞታችን ይሞላል ማለት አይደለም፡፡ በጎ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር ነጩ ጥቁር፣ ጣፋጩ መራራ፣ ብርሃኑ ጨለማ፣ በጋው ክረምት መስሎ መታየቱ አይቀርም፡፡ በጎ ፈቃድ ያላቸው ሰብአ ሰገል በይሁዳ ቤተልሔም ተገኝተው "የሰላም አለቃ" ተብሎ በነብያት ለተነገረለት ለሕጻኑ ኢየሱስ እየሰገዱ የወርቅ፣ የእጣንና የከርቤ ስጦታ ሲያዥጎደጉዱለት በአንጻሩ በጎ ፈቃድ የጎደለውና የደም ጥማተኛው ሮማዊው ሄሮድስ በቤተልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን ጨቅላ ሕጻናት በሙሉ ያስጨፈጭፍ ነበር፡፡

በጎ ፈቃድ ሳይኖር ለይስሙላ ያህል "ሰላም! ሰላም! ሰላም!" በማለት ራስንም ሌላውን መሸነገል ከቶውንም የሚከብድ አይደለም፡፡ "ሰላም ለሀገራችን፤ ለሰዎችም በጎ ፈቃድ" የምንለው ሰላምና በጎ ፈቃድ በፍጹም ሊለያዩ ስለማይችሉ ነው፡፡ የዓለም ታላላቅ ሀገራት እስኪደነቁ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ጦርነት አያዋጣንም በማለት ለሰላም እሺታውን ያረጋገጠው ለተከፈለው መስዋዕትነት፣ ለወደመው የዜጎችና የሀገር ሀብት፣ ለቆሰለው የግፉዓን ስሜትና ለደረሰብን ሀገራዊ ስብራት ቁብ ሳይሰጥ ቀርቶ ሳይሆን "በጎ ፈቃድ ከጦርነት ድል እንደሚበልጥ" በማመኑ ነው፡፡

በመንግሥትና በሌላው ወገን ከስምምነት ላይ የተደረሰበት "አዲስ ኪዳን" የምር ሆኖ ዘላቂነት ያለው ሰላም እንዲሰፍን የዜጎች በጎ ፈቃድ ሲታከልበት ስለሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፀብና ለሴራ አሻፈረኝ፣ ለከንቱ መቆራቆዝና ደም መፋሰስም እምቢኝ ብሎ ሊጨክን ይገባል፡፡ በአንጻሩ በየዕለቱ ለሚታዩት መልካም ሀገራዊ የልማት ክንውኖችና ጅምሮች ዜጎች ዕውቀታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ሀብታቸውን አስተባብረው ኢትዮጵያን ከከፍታ ማማ ላይ ለማውጣት እጅ ለእጅ ተያይዘው፤ ልብ ለልብ ተናበው ሊተባበሩ ይገባል፡፡ ሰላም ለሀገራችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ፡፡ መልካም በዓል!

# ተናጋሪው ዶሴ

## አደንዛዥ እፅ አዘዋዋሪዎቹ ብራዚላውያን

አስመረት ብስራት



ብራዚል ከሩሲያ፣ ቻይና፣ ካናዳ እና አሜሪካ ቀጥላ አምስተኛዋ ትልቅ ሀገር ነች። ስፋቷም ከጠቅላላው የደቡብ አሜሪካ አህጉር ግማሽ ያህሉን ይይዛል። የፖርቹጋላዊው የፔድሮ ካብራል ጉዞ የብራዚልን አፈር የረገጠው የመጀመሪያው ሰው እንዲሆን አድርጎታል። ፖርቹጋላውያን ወደ ሕንድ የሚወስዱትን አዳዲስ መንገዶችን እየፈለጉ የነበር ቢሆንም የፈለጉትን ያህል የከበረ ማዕድን ማግኘት አልቻሉም ነበር። ነገር ግን በጉዟቸው አንድ የማይታወቅ መሬት አግኝተዋል። እሱምን "የቅዱስ መስቀል ምድር" ብለው ይጠሩታል።

ፖርቹጋሎች የወርቅ እና የከበሩ ድንጋዮች ክምርን አልመው ነበር። ሆኖም ፍለጋቸው አልተሳካም። በጣም ዋጋ ያለው እንደ ፖርቹጋሎች ሰፋሪዎች በአዲሱ ቅኝ ግዛት ውስጥ ደማቅ ቀይ ቀለም የተገኘበት የፓውብራሲል ዛፍ ነበር። ይህ ቀይ ዛፍም ስያሜው ብራዚል ስለነበር አገሩ በስሙ ተሰይሟል - ብራዚል።

የብራዚል ሁለቱ የተፈጥሮ ክልሎች (በደን የተሸፈነው የአማዞን ወንዝ ሜዳ ፣ ገባር ወንዞቹ እና የብራዚል ፕላቶ) በእጅጉ ይለያያሉ። አማዞን በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ሙሉ በሙሉ ከጠፈር ላይ ብቻ ሊታይ ይችላል። ይህ አረንጓዴ ወሰን የሌለው የማይበገር ስፋት ነው ። አንዳንድ ጊዜ በዚህ አረንጓዴ ጥቅጥቅ ያለ ሰፊ ሰማያዊ ነጠብጣቦች ይታያሉ። ይህ ሰፊ ምድርም በወንዞቹ ሪባን አንድ ላይ ይጣመራል።. ከዚህች የዓለም ሳንባ ከተባለችው ሀገረ ብራዚል፤ በቅርቡ በሞት ከተለየን ከእግር ኳስ ንጉሱ ፔሌ ሀገር የተነሱና መዳረሻቸውንም ደቡብ አፍሪካ ያደረጉትን የሁለት ብራዚላውያን ሴቶችን ታሪክ ላካፍላችሁ ስለወደድኩ ነው ስለብራዚል ያነሳሳሁት።

### እፅ ማዘዋወር መተዳደሪያቸው ያደረጉ ብራዚላውያን

ብራዚላውያን ጓደኛሞች ናቸው። ኤልዳ ሪጂና ሳንቶስና ሚስ ናዲራ ጋብርኤላ። ከልጅነታቸው ጀምሮ የድሆች መንደር ውስጥ በማደጋቸው የዕለት ጉርስ ለማግኘት የተገኘውን ሥራ በሙሉ ለመሥራት ይታትሩ ነበር። መላላክ፤ አነስተኛ ንግዱንም አለ የተባለውን ሥራ በሙሉ በመሥራት የዕለት ምግባቸውን ዳቦ መግዛት ችለውም ነበር። የልጅነት ጊዜያቸውን አንዴ ትምህርት ቤት ሲሄዱ፤ ረሀብና ችግር ሲፈራረቅባቸው ደግሞ ሲቀሩ ፊደል ከመለየትና የተወሰኑ የሂሳብ ቀመሮች ከማወቅ የዘለለ እውቀት የሚያስገኝ የትምህርት ደረጃ ላይ አልደረሱም ነበር።

ለአቅመ ሄዋን እንደደረሱ ብዙም ያልገፉበትን ትምህርት ወደ ጎን በመተው ከእነሱ ሰፈር ወደ ሀብታሞቹ ሰፈር አደንዛዥ እፆችን በማዘዋወር ሥራ ላይ ተጠመዱ ። አንድ ሁለት እያሉ የተሠማሩበት ሥራ ከድህነት አላቆ ከፍ ወዳለ የሀብት ማማ የሚያደርስ መሆኑን ከሚያሠሯቸው ሰዎች ኑሮ ተመልክተው ተረድተዋል።

እነሱም እራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን ከችግር ለማላቀቅ ምርጫቸው ያደረጉት ከልጅነታቸው ጀምሮ ሲያዩት ያደጉትን ሥራ ነበር። ከሰፈር ሰፈር አደንዛዥ እፅ በማዘዋወር የተጀመረው ሥራ በብራዚል ውስጥ የሚገኙ ክፍለ ሀገራትን በሙሉ አዳርሷል። ብራዚል ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች ከግብረ አበሮቻቸው ጋር በመሆን የጀመሩትን ሥራ በዓለም ደረጃ ለማዳረስ አሰቡ ። እቅዳቸውን እውን ለማድረግም መዳረሻቸውን በማስፋት ከትውልድ ቀያቸው በመነሳት የተለያዩ ሀገራትን መርገጥ ጀመሩ።

### ከሀገረ ብራዚል የተነሱት እፅ አዘዋዋሪዎች

በ214 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያላት የዓለማችን አምስተኛዋ ባለብዙ ሕዝብ ሀገር ብራዚል በእግር ኳስ የመታወቋንም ያህል ወንጀል በብዛት ከሚፈፀምባቸው ሀገሮች አንዷ እንደሆነች ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። የኢኮኖሚ የበላይነት የያዙት ሀብታም ብራዚላውያን የሀብት ማማ ላይ ቢቀመጡም ድሆቹ ግን በሴተኛ አዳሪነት፤ በአነስተኛ ሥራዎችና በአደንዛዥ እፅ ዝውውር ስማቸው ይነሳል።

ታዲያ ድህነት እግር ከወርች ያሠራቸው፤ ከድሆቹ ወገን የሆኑት ጓደኛሞች እንደ ልማዳቸው ከትውልድ ቀያቸው ተነስተው የአፍሪካ ኩራት በሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በኩል አደንዛዥ እፅ የተሞሉ ሻንጣዎቻቸውን እንደያዙ ለመሄድ ሲነሱ በቁጥጥር ስር መዋላቸውን ከፍትሕ ሚኒስቴር ድረገፅ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

ኤልዳ ሪጂና ሳንቶስና ሚስ ናዲራ ጋብርኤላ የተባሉ ብራዚላዊ ዜግነት ያላቸው ሁለት ሴቶች እፆችን ለማዘዋወር የፀና ፍቃድ ሳይኖራት መነሻቸውን ብራዚል ሳኦፖሎ ከተማ አድርገው ቀጣይ ጉዞዋቸውን ደቡብ አፍሪካ ጆሃንስ በርግ ከተማ ለማድረግ በኢትዮጵያ በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ለትራንዚት ባረፉበት ወቅት በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሊውሉ ችለዋል።

በቅድሚያ ኤልዳ ሪጂና ሳንቶስ የተባለችው ብራዚላዊ ዜግነት ያላት ተከሳሽ እፆችን ለማዘዋወር የፀና ፍቃድ ሳይኖራት መነሻዋን ብራዚል ሳኦፖሎ ከተማ አድርጋ ቀጣይ ጉዞዋን ደቡብ አፍሪካ ጆሃንስበርግ ከተማ ለማድረግ መስከረም 26 ቀን 2015 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰዓት ከ30 ሲሆን በኢትዮጵያ በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ለትራንዚት ባረፈችበት ጊዜ በፌደራል ፖሊሶች አደገኛ ዕጽዋት ቁጥጥር እና ክትትል ሠራተኞች የያዘችው ሻንጣ ሲፈተሽ በውስጡ 1ሺ 76 ጥቅል ፍሬ ሲመዘን 23 ሺ 73 ግራም የሆነውን ኮኬይን እፅ ደብቃ ለማሳለፍ ስትል ተይዛለች፡፡

ሌላዋ ሚስ ናዲራ ጋብርኤላ የተባለችው ብራዚላዊ ዜግነት ያላት ተከሳሽ ልዩ ፈቃድ ሳይኖራት ሱስ በማስያዝ ለተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች መንስኤ እንዲሆኑ ስለሚገፋፉ እንዳይመረት፣ እንዳይዘዋወርና በጥቅም ላይ እንዳይውል የታገደውን ኮኬይን እፅ በሻንጣዋ ውስጥ ደብቃ ለማዘዋወር በማሰብ መነሻዋን ብራዚል ሀገር ሳኦፖሎ ከተማ አድርጋ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመጓዝ በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ለትራንዚት ባረፈችበት ወቅት ነሐሴ 24 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ ብዛቱ 533 ፍሬ ጥቅል ኮኬይን መያዟ በፍተሻ የተገኘ በመሆኑ በፈፀመችው አደገኛ ዕፅ ማዘዋወር ወንጀል በቁጥጥር ስር ውላለች።

የአንዷ ጥፋትና ቅጣት ያላስተማራት ሌላኛዋም በድፍረት የሀገሪቱን አየር አቋርጠው ያልተገባ ወንጀል ለመሥራት መሞከራቸው የሀገሪቱን ሕግ የጣሰ መሆኑን ፖሊሶች ይናገራሉ።

### የፖሊስ ምርመራ

የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በኢትዮጵያ ሕግ ከተመለከቱ ወንጀሎች ውስጥ ማንኛውንም ወንጀል ቢያደርግ የሀገሪቱ ሕግ ተግባራዊ ተደርጎበት በሀገራችን ሕግ መሠረት የሚቀጣ ሲሆን የኢትዮጵያ ግዛት የብሱን፣ አየሩንና የውሃ አካላቱን የሚያጠቃልል መሆኑን ፖሊሶች ሕግን ጠቅሰው አስረድተዋል። ይህን ሕግ ተጠቃሽ ያደረጉት የአየር መንገዱ የደህንነት አካላት በቁጥጥር ስር የዋሉት ተጠርጣሪዎች ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ጣቢያ ከተወሰዱ በኋላ የዓይን ምስክር የሰነድና በኤግዝቢትነት የተያዙ ዕፆችን ማስረጃዎችን በማያያዝ ፖሊስ ለዐቃቤ ሕግ ያቀርባል።

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ኤልዳ ሪጂና ሳንቶስ የተባለችው ብራዚላዊ ዜግነት ያላት ተከሳሽ ዕፆችን ለማዘዋወር የፀና ፍቃድ ሳይኖራት መነሻዋን ብራዚል ሳኦፖሎ ከተማ አድርጋ ቀጣይ ጉዞዋን ደቡብ አፍሪካ ጆሃንስበርግ ከተማ ያደረገችው ሙከራ የከሸፈባት ተከሳሽም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ችሎት ቀርባ ክሱ ተነቦላት የወንጀል ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ ስትል የእምነት ክህደት ቃሏን ሰጥታለች።

ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው ተከሳሿ ባመነችው መሠረት የጥፋተኝነት ፍርድ እንዲሰጥ ጠይቋል። ፍርድ ቤቱም ተከሳሿ በተከሰሰችበት ድንጋጌ ስር በዝርዝር ያመነች በመሆኑ ባመነችው መሠረት የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

በሌላ የችሎት ውሎ ከ 14 ኪሎ ግራም በላይ የሚመዝን የኮኬይን እፅ ይዛ የተገኘችው ናዲራ ጋብርኤላ ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ 14ሺ 412 ግራም የሚመዝን የኮኬይን ዕፅ በተደረገ ፍተሻ በሻንጣዋ ውስጥ የተገኘባት ብራዚላዊት ናት።

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ሚስ ናዲራ ጋብርኤላ የተባለችው ብራዚላዊ ዜግነት ያላት ተከሳሽ ልዩ ፈቃድ ሳይኖራት ሱስ በማስያዝ ለተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች መንስኤ እንዲሆኑ ስለሚገፋፉ እንዳይመረት፣ እንዳይዘዋወርና በጥቅም ላይ እንዳይውል የታገደውን ኮኬይን እፅ በሻንጣዋ ውስጥ ደብቃ ለማዘዋወር በማሰብ መነሻዋን ብራዚል ሀገር ሳኦፖሎ ከተማ አድርጋ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመጓዝ በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ለትራንዚት ባረፈችበት በፈፀመችው አደገኛ ዕፅ ማዘዋወር ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶ ውሳኔ አሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ 23ሺ 73 ግራም የሆነውን የኮኬይን እፅ ደብቃ ለማሳለፍ ስትል በተደረገ ፍተሻ በተያዘችው ኤልዳ ሪጂና ሳንቶስ የተባለች ብራዚላዊት ዜጋ ላይ ክስ አቅርቦባት በ10 ዓመት ፅኑ እስራት እና በ20 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ አደረገ፡፡

ሌላዋ ጥፋተኛንም በተመሳሳይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ችሎት የቀረበችው ተከሳሽም ክሱ በችሎት ተነቦላት የወንጀል ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ ያለች ሲሆን፣ ዐቃቤ ሕግም ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው ባመነችው መሠረት የጥፋተኝነት ፍርድ ይሰጥልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተከሳሿ በተከሰሰችበት ድንጋጌ ስር በዝርዝር ያመነች በመሆኑ ባመነችው መሠረት የጥፋተኝነት ፍርድ በመስጠት በ10 ዓመት ፅኑ እስራት እና በ20 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ ሲል ወስኖባታል፡፡

መዝናኛ

## ማረፊያ/ ትዝብት

# እናትን ማርከስ፤ መሠረትን ማፍረስ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

በወርሀ ታኅሳስ ዕለተ ቅዳሜ አንድ ቀን ከመሥሪያ ቤት ወጥቼ ወደ ማደሪያዬ ለመንጎድ ተነሳሁ። ከቢሮዬ እንደወጣሁ ዓይኖቼ ታክሲ ወደሚያዝበት አቅጣጫ አማተሩ። ትንሽ ሄድ እንዳልኩ "እ ና ትህ እን......." የሚል ድምጽ ሰማሁ አንገቴን ወደ ኋላ ቀለስ አድርጌ ከእግር ጥፍሩ እስከ እራስ ፀጉሩ በግልምጫ ጠረባ ጥየው ጉዞየን ቀጠልኩ!

አዲስ አበባ ላይ ማህበራዊ መስተጋብር እየላላ ሄዷል ቢባልም፤ ታክሲ ውስጥ ግን ገና አልቀረም። ተቃቅፎ ሚስጥር እንደሚነጋገር ሰው አንዱ ባንዱ ጆሮ ስር ተወሽቆ፤ ያንደኛው እግር በሌላኛው ላይ ተረማምዶ አንዱ ሲረግጥ ሌላኛው ሲረገጥ ችግር የለውም "ችግር የለውም" ተባብሎ በፍቅር ሲጓዝ ይቆይና ፈርማታ ሲደርስ ሁሉም መንጫጫት የተለመደ ነው።

ታድያ በዚህ ጊዜ መደማመጥ ላይኖር ይችላል። "ወራጅ አለ" አንደኛው ተሳፋሪ ከኋላ ሆኖ ተጣራ። ማንም አልሰማውም። ደግሞ "ኧረ ወ..ራ..ጅ!" ከመታፈኑ የተነሳ ድምጹ ተቆራርጦ ነው የሚሰማው። በጣም ተናዶ "እንዴ ኧ ረ ወ ራ ጅ!" አለ። ሾፌሩ "እ፤ ወራጅ አለ?" ሲል ጠየቀ። ተሳፋሪው "አይሰማህም? እናትህ......" ጆሮዬን ጎረበጠኝ። እንደ መጀመሪያው እንዳልገለምጠው ሰው ከመተፋፈኑ የተነሳ ተናጋሪው አይታይም። ብስጭት አልኩ። እሱም ወዲያው እንዴት እንደወጣ ሳላየው ከዓይኔ ተሰወረ።

እኔም ከአንደኛው ወርጄ ወደሌላኛው ታክሲ ገባሁ። አሁን ምንም የለም። "እሰይ ተመስገን!" እንያልኩ ታክሲው እየከነፈ ሦስተኛው ፌርማታ ጋር አደረሰኝ። ወርጄ ሦስተኛውን ታክሲየን ለመያዝ ወደ ፊት እየተራመድኩ ከጎኔ እየተቀላለዱ ከሚሄዱ ሰዎች አጠገብ ደረስኩ። በንግግራቸው መሃል አንዱ "እናትህ....." አለ። "እህ ለካ በቀልድም መሃል ይባላል?" ንዴት የቀላቀለ ግርምት አስተናግጄ ጉዞዬን ቀጠልኩ።

ሦስተኛው ታክሲ ላይ ገብቼ አረፍ እንዳልኩ አንዱ እቃ አሸክሞ መጣና "ረዳት እንካ ጫነው"። ረዳቱም ቀና ብሎ አየና "ከነራስህ..... ትከፍላለህ" አለ። ተሳፋሪውም ኮስተርተር ብሎ "እናትህ.......፤ ዘረፋ ነው የወጣሃው?" የሚገርመው ደግሞ እንዲህ ባዩ ትልቅ ሰው ነው፤ ማለቴ ያው በእድሜው ትልቅ ነው። እንዴ? የዛሬው ደግሞ አያምጣው ነው! አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሦስቴ? ሰቀጠጠኝ!

ከሌላ አካል እጣላ ይመስል ጆሮዬን ለምን ትሰማለህ ብዬ ለመቆጣት ዳዳኝ። ዳሩ ግን ከራሴ ጋር ግብግብ ከመግባት ውጪ ምንም ማድረግ እንደማልችል ሲገባኝ ቶሎ ከታክሲው ወርጄ ኮበለልኩ። ለማንኛውም የዛሬ ትዝብቴ ከትዝብትነት አልፎ ብስጭት አሳድሮብኛል። አንዳንድ ቀን ጆሮዬ ጠላቴ ሆኖ ቀኔን ያበላሸዋል።

ምን አለ ግን ጆሮዬ ለይቶ ቢሰማ ብዬ ከራሴ ጋር ግብ ግብ እገጥማለሁ። እርሱስ ይሁን ከፉንም ደጉንም መስማት መቼም ተፈጥሮው ነው፤ ግን ክፉውን ከበጎው ለይቶ የመያዝ ስልጣን የተሰጠው ሕሊናዬ ሥራው ምን ሆነና ነው እንዲህ ስሆን ዝም ብሎ የሚያየኝ? መቼስ ከራስ መጣላት አያደርገው የለ!

በቃ እንዲህ ዓይነቱን ቃል በሰማሁ ቁጥር ሁሌም እረበሻለሁ፣ ከራሴ ጋር እጣላለሁ። አንዳንዴ ሰዎች ከመሠረታቸው በእምቧይ ካብ የተገነቡ ይመስላሉ፤ የለበጣ ሳቅ ይሳለቃሉ፤ በእጃቸው የጎረሱበትን መሶብ በእግራቸው ይረግጣሉ። "እ ና ትህ/ሽ እንዲ ትሁን" የሚል እጅጉን ፀያፍ ቃል ይጠቀማሉ።

በእርሷ ዘንድ ያለልዩነት እኩል ትዳኛለህ። አንተ በጎም ሆንክ ክፉ፣ ለጋስም ሆንክ ንፉግ፣ አዋቂም ሆንክ አላዋቂ፣ ብልህም ሆንክ ሞኝ፣ ፉንጋም ሆንክ መልከ መልካም እዮርና ራማ በመሰለው ታዛህ እኩል ቦታ አለህ። ሰዓቱ ይለያይ እንጂ በአካላቷ ያልታዘልክበት ጊዜ የለም።

በሆዷ ተሸክማህለች፤ በደረቷ አቅፋ በጡቶቿ ሕይወት ምግብ መግባሃለች፤ በጀርባዋ አመቻችታ አዝላሀለች፤ በከንፈሯ ስማሀለች፤ በእጆቿ ፈትፍታ አጉርሳሃለች፣ እርሷ ተንገላታ፣ ጠቁራና ከስታ አንተን አስመችታ አሳድጋሃለች።

ህልሟ ላንተ መኖር ነው! ከዚያ ውጪ ዓለም ለእርሷ ምንም አይደለም። ሳይኖራት እራሷን መስዋዕት አድርጋ ያኖረችህን መላው ሰውነቷን በወርቅ ብስታጌጣት ውለታዋን ልትከፍላት አችልም። ምክንያቱ ደግሞ እርሷ ሳትሰስት ሁሉንም የሰጠችህ ከሌላት ላይ ሲሆን አንተ ግን ሰጠሁ ብትል እንኳን ኖሮህ ከተረፈህ ላይ ነው።

ይህ ሁሉ ግን በደግነትህ አይደለም። እናት የመሆኗ ድንቅ ሚስጥርና በማያልቀው ፍቅሯ የተነሳ እርሷው ያደረገችው እንጂ። "ዓባይን በጭልፋ እንዲሉ" የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል ትንሽ ስለ እውነታው ልሞነጫጭር አስቤ ነበር። ግን አልቻልኩም በምናብ ቀረሁ። እንዴያው በኮልታፋ አንደበቴ ያቅሜን ልንተባተብ ብዬ እንጂ ድሮስ በምን አቅሜ ችዬ እርሷን ልገልጻት፣ ስለእርሷስ መናገር እችላለሁ! ቃላት አጥንትን የመሰበር ታላቅ ኃይል አላቸው ቢባልም እርሷን ለመግለጽ ግን አቅመ ቢሶች ናቸው።

በዓለም ላይ ውድ የሆኑ እንቁዎችን ገዝተህ ልታጌጥባቸው ትችል ይሆናል። እናትነትን ግን ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ቢል ልትገዛትም ልትሠራትም አትችልም። እሷ የፈጣሪ ስጦታ ናት። ግን እናትን ያህል ነገር ጠርቶ ጸያፍ ቃል መናገር ምን ያህል ትንሽነት ነው? ምን ያህልስ ከሰውነት መውረድ ነው? አንዳንዶች "እናትህ እንዲህ ትሁን፣ እናትህ..." ይሉህና ለምን ስትላቸው "እርድና ነው" ይሉሃል።


እናትንና ሀገርን ተሳድበህ የቀለድክ ቀን ያንተ ቂልነት ገደብ አጥቷል ማለት ነው። ይሁን እንጅ እንደዚህ ዓይነት ቃላትን መስማት እየተለመደ መጥቷል። ሥራ ቦታዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ መዝናኛ ቦታዎች፣ ታክሲዎች ውስጥና ታክሲ ተራዎች......። እንዲህ ዓይነት ሰቅጣጭ ቃላት ባላንጣ አንደበቶች በየቀኑ የሚሰናዘሯቸው የዕለት ተዕለት የአፍ ማሟሻዎች ሆነዋል።

በእርግጥ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሳለሁም እንደዚህ ዓይነት ቃላት "አራዳ ነን" ባዮች አቻዎቼ ይጠቀሙ እንደነበር አስታውሳለሁ። ግን እንደዚህ በትልልቅ ሰዎች አንደበት ጭምር በመስማቴ እጅጉን ገርሞኛል፣ አናዶኛልም። እናትነት ተቀድቶ የማይደርቅ የርህራሔ ምንጭ ነው። እናትነት ተነቦ ያላለቀ ሰምና ወርቅ ነው። ምን አለ ታድያ ውለታቸውን መክፈል ባንችል እንኳን ስማቸውን በመጥፎ ባናነሳ?

እንደዚህ ዓይነቱን ጸያፍ ቃላት የማይጠቀሙ ሰዎችስ ከጥፋተኝነት ድነው ይሆን? "ምናገባኝ" ብለን ዝም ለምንልስ? ለዚህ ጥያቄ መልሱ ሁላችንም ጋር ነው። የሚገስጽና እንደትውልድ ወደተሳሳተ ጎዳና ውስጥ ስንገባ አቅጣጫ የሚያመላክት መጥፋቱ ያሳስበኛል። ከባህል ወግ ልማዳችን ተራቁተን እርቃናችን የቀረን መስሎ ይሰማኛል። እናት ሁሉንም ቻይ ነች። ለሚያጎርሳትም ለሚነክሳትም እኩል ያው እናት ነች። ታድያ እኔ እናትን በምንም ይሁን በምን በበጎ እንጂ በመጥፎ ስሟ ባይጠራ መልካም ነው ባይ ነኝ። አይ ብለህ ብትጠራ ግን እናት ሀገር ናትና መሠረትህን በእምቧይ ካብ ሠርተሀልና መጨረሻህ መናድ ይሆናል። ክብር ለእናቶቻችን!!!

## ዓለም አቀፍ

# ዋትስአፕ ኢንተርኔት ቢዘጋም ሰዎች መልዕክት እንዲለዋወጡ አስችላለሁ አለ




በዓለም ዙሪያ በርካታ ተጠቃሚዎች ያሉት ዋትስአፕ ተጠቃሚዎች ኢንተርኔት ተቋርጦባቸውም መልዕክት እንዲለዋወጡ አስችላለሁ አለ።በሜታ ባለቤትነት የሚተዳደረው የመልዕክት መለዋወጫ መተግበሪያው በኢራን ያጋጠመው ዓይነት 'ዳግም አይከሰትም' ብሏል።

ግዙፉ የቴክኖሎጂ ኩባንያ መንግሥታት ኢንተርኔትን ቢያቋርጡም ሆነ ክልከላ ቢጥሉ በሌላ ስፍራ በሚገኙ ሰርቨሮች አማካይነት ሰዎች ዋትስአፕን መጠቀም እንዲችሉ ይደረጋል ብሏል።የቴክኖሎጂ ባለሙያው ጄራስ ጄረሴናስ ዋትስአፕ ይህን ማድረጉ ኢንተርኔት እንዲቋረጥ በሚደረግባቸው አገራት ያሉ ሰዎች በነጻነት በዋትስአፕ ግንኙነት መፍጠር እንዲችሉ ያስችላል ብለዋል።

በመላው ዓለም ያሉ ሰዎች የኢንተርኔት ግንኙነታቸው ሌላ ዓላማ ባላቸው አካላት እንዲቋረጥ ቢደረግም የኢንተርኔት አገልግሎታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ነው ይላሉ ይህ ባለሙያ።ድርጅቱ አዲስ አግልግሎቱን ይፋ እንደሚያደርግ ባስታወቀበት መግለጫው ሰዎች ሰብአዊ መብታቸው መጠበቅ እንዳለበት ገልጾ፤ "ሰዎች አስቸኳይ እርዳታ እንዳያገኙ ተከልክለዋል" ብሏል።

ዋትስአፕ "ሰዎች በነጻነት መልዕክት እንዲለዋወጡ" በጎ ፍቃደኞች 'ፕሮክሲ ሰርቨሮችን' እንዲለግሱ ጠይቆ፤ ፕሮክሲ ሰርቨሮች ወደ ሥራ እንዴት ማስገባት እንደሚቻል ምክር ለመስጠት ዝግጁ ነኝ ብሏል። "በፕሮክሲ አማካይነት መገናኘት ዋትስአፕ ከሚያቀርበው ከፍተኛ ግለኝነት (ፕራይቬሲ) እና ደኅንነት ጋር ተመሳሳይ ነው" ብሏል የቴክኖሎጂ ኩባንያው።

የግል መልዕክቶች በላኪው እና በተቀባዩ ብቻ እንጂ በዋትአፕም ሆነ በፕሮክሲ ሰርቨሮቹ አማካይነት ሊታዩ እንደማይችሉ በመግለጽ የመልዕክት ሚስጢራዊነት የተጠበቀ መሆኑን ገልጿል።እንደ ስታቲስታ ከሆነ ዋትስአፕ በወር ንቁ የሆኑ 2 ቢሊዮን ተጠቃሚዎችን በመያዝ የዓለማችን ቁጥር አንድ መልዕክት መለዋወጫ መተግበሪያ ነው።

ከዋትስአፕ በመቀጠል ዊቻት እና ፌስቡክ ሜሴንጀር እያንዳንዳቸው 1 ነጥብ 2 ቢሊዮን እና 988 ሚሊዮን ተጠቃሚዎችን በመያዝ በሁለተኛ እና ሦስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል።ዋትስአፕ ሰዎች የጹሑፍ መልዕክት፣ የድምጽ እና የቪዲዮ ጥሪ ማድረግ በተጨማሪ ተጠቃሚዎች ምሥሎችን እንዲላላኩ የሚያስችል መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ዓለማችን ባለሀብቶች የሁለት ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ አጋጠማቸው



በ2022 ዓመት የዓለማችን ባለሀብቶች ሁለት ትሪሊዮን ዶላር መክሰራቸው ተገለጸ። በቅርቡ የተጠናቀቀው የፈረንጆቹ 2022 ዓመት ለዓለማችን ባለጸጋዎች መልካም እንዳልነበር ትኩረቱን በምጣኔ ሀብት ዘገባዎች ላይ ያደረገው ፎርብስ በድረገጹ አስነብቧል።

እንደዘገባው ከሆነ የዓለማችን ባለሃብቶች ሁለት ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ ያስመዘገቡ ሲሆን አሜሪካዊ ባለሀብቶች ደግሞ በአንጻራዊነት ብዙ ኪሳራ ማስመዝገባቸው ተገልጿል። ባለፀጋው ኤሎን መስክ የ200 ቢሊዮን ዶላር ኪሳራ አጋጥሟቸዋል፡ ፡ በፈረንጆቹ 2020 እና 2021 ዓመት ለባለሀብቶች ብዙ ትርፍ እንዲያስመዘግቡ ያገዘ ቢሆንም የተጠናቀቀው 2022 ዓመት ግን ኪሳራን አስከትሏል ተብሏል።

በአውሮፓ የተከሰተው የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት፣ የአክስዮን ገበያ መቀዛቀዝ እና የዋጋ ግሽበት ለዓለማችን ባለጸጋዎች ገቢ መቀነስ ዋነኞቹ ምክንያቶች እንደሆኑ በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።የዓለማችን ባለጸጋዎች በአጠቃላይ 13 ነጥብ 8 ትሪሊዮን ዶላር ሀብት የነበራቸው ሲሆን በ2022 ኪሳራ ማስመዝገባቸውን ተከትሎ የጠቅላላ ሀብታቸው ወደ 11 ነጥብ 9 ትሪሊዮን ዶላር ዝቅ ሊል ችሏል።

ኪሳራውን ተከትሎም የቢሊየነሮች ቁጥርም ከ2 ሺህ 671 ወደ 2 ሺህ 523 ዝቅ ማለቱን በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።ታዋቂው ሙዚቀኛ ካንየ ዌስትን ጨምሮ ሳም ባንክማን እና የሪቪያን መስራቹ አርጂ ስካሪንጅ ከቢሊየነርነት ደረጃቸው ወደ ሚሊየነርነት ዝቅ ያሉ ባለሀብቶች ሁነዋል።

የተጠናቀቀው 2022 ዓመት በሁሉም ቢሊየነሮች ላይ ኪሳራ ያስመዘገቡበት ዓመት ቢሆንም 300 የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ግን ከሁሉም ከፍተኛ ኪሳራ ማስመዝገባቸው ተገልጿል።በተለይም በጄፍ ቤዞፍ የተመሰረተው አማዞን ኩባንያ 80 ቢሊዮን ኪሳራ ሲያስመዘግብ፣ ጎግል ኩባንያ 40 ቢሊዮን ዶላር፣ ቢል ጌት 20 ቢሊዮን ዶላር፣ የሜታ ኩባንያ መስራቹ ማርክ ዙከርበርግ 78 ቢሊዮን ዶላር፣ የትዊትር እና ቴስላ ኩባንያ ባለቤቱ ኢለን መስክ 200 ቢሊዮን ዶላር ኪሳራ ማስመዝገባቸው በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።

በአጠቃላይ በ2022 ዓመት አሜሪካዊያን ባለሃብቶች 660 ቢሊዮን ዶላር በመክሰር ቀዳሚ ሲሆኑ የቻይና ባለጸጋዎች ደግሞ 620 ቢሊዮን ዶላር ኪሳራ በማስመዝገብ በሁለተኝነት መቀመጣቸው ተጠቅሷል፡፡

ከዩክሬን ጋር ጦርነት ውስጥ ያለችው ሩሲያ ደግሞ በባለሃብቶቿ ላይ በተጣለባት ማዕቀብ ምክንያት 150 ቢሊዮን ዶላር ኪሳራ ማስመዝገቧ ተገልጿል፡፡ይህ በዚህ እንዳለ ግን የእስያ ባለሃብቶች በአንጻራዊነት የተጠናቀቀው 2022 ዓመት ምርጥ ዓመት እንደነበረላቸው ተገልጿል፡፡

በተለይም በስፖርት ኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማሩት አሜሪካዊው ቶድ ቦህሊ እና ዲዛይነሩ ቶም ፎርድ 11 ቢሊዮን ዶላር ትርፍ ሲያገኙ ቻይናዊው ኮሊን ዜንግ እና ኢንዶኔዢያዊው የከሰል ድንጋይ ነጋዴ ሎው ተክ ክዋንግ በድምሩ 16 ቢሊዮን ዶላር ማግኘታቸው ተገልጿል። ከቀናት በፊት የተጠናቀቀው 2022 ዓመት ለሕንዳዊው ጉዋተም አዳኒ በታሪኩ ከፍተኛውን ትርፍ ያገኘበት ዓመት ሲሆን በሎጅስቲክስ እና ሀይል ልማት የተሰማሩት ኩባንያዎቹ በድምሩ 55 ቢሊዮን ትርፍ አስገኝተውለታል ተብሏል፡፡

ይህ ሕንዳዊ ባለጸጋ ከፍተኛ ትርፍ ማትረፉን ተከትሎ አጠቃላይ የሐብት መጠኑ ወደ 134 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ሲል ሶስተኛው የዓለማችን ባለጸጋ ለመሆንም መብቃቱን አል ዐይን ዘገባ ያመለክታል፡፡

# መጋቢ አዕምሮ

# “የድህነት ፍልስፍና” ወይስ/እና “የፍልስፍና ድህነት”?

ግርማ መንግሥቴ

> **ችግሮቻችን ተቆጥረው አያልቁም። በተለይ አሁን አሁን በውክልና የዓለምን ችግሮች ሁሉ እኛ እያስተናገድን ይመስላል። ረሀብ አለ። ጦርነት አለ። የእርስ በእርስ መቆራቆስ አለ። ሙስናው ጣራ ነክቷል። ዘረኝነት ተንሰራፍቷል። የትምህርት ጥራት ጉዳይ ተከድኖ ይብሰል ከተባለ ቆየ። የኑሮ ውድነት ቅጡን አጥቷል። ሕገ ወጥነት ሕጋዊ እየሆነ ነው። ሕዝባዊ አገልግሎት ከተመሰቃቀለ ቆየ። እዚህ አገር ምን የሌለ ችግር አለ? ምንም። በመሆኑ የችግሮቻችን ሁሉ መንስኤ “የድህነት ፍልስፍና” ወይስ/እና “የፍልስፍና ድህነት” የሚለው ላይ ከምር መነጋገር ያስፈልጋል**

ዓለማችን ካስተናገደቻቸውና እያስተናገደቻቸውም ካለችው ፍልስፍናዊ ንትርኮች መካከል ሁለቱ፣ እዚህ በርዕሳችን የጠቀስናቸው አወዛጋቢና የዓለምን ፈላስፎች (ወደ ፊትም ይቀጥላል) ቀልብና ትኩረት የሳቡ ጥልቅና ሰፋፊ እሳቤዎች ናቸው።

ፈረንሳዊው የንድፈ ሀሳብ ቀማሪ፣ በግለሰብ እና መንግሥት (Individual and The State) መካከል ስላለውና መኖር ስለሚገባው ግንኙነት ያለ መቋረጥ የጻፈው ጆሴፍ እኤአ በ1846 “The Philosophy Of Poverty” (በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ለምሳሌ Colorado State University ውስጥ በ3 ክሬዲት አዎርስ (Credits) ለ Philosophy and Religious Studies ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን፤ ትኩረቱ (ይዘቱ)ም ስለ ድህነት ምንነት ብያኔ መስጠት፣ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ግንዛቤ መፍጠር፤ እንዲሁም፣ የአሳዛኙን ዓለም አቀፍ ድህነት (the tragedy of global poverty) ምንጭ መመርመርና መፍትሔዎችን መጠቆም ላይ ነው) ብሎ ለጻፈው ጽሑፍ በዛን ወቅት ፓሪስ (ከ1843 እስከ 1849) ይኖር የነበረው እና መጽሐፉን ያነበበው ካርል ማርክስ ከፈረንሳይ ተባሮ ወደ ብራስልስ ከሄደ በኋላ ለፈረንሳዊው ፕሉዶን እኤአ በ1847 አጋማሽ “The Poverty Of Philosophy” (በመጀመሪያ የተጻፈው Misère de la philosophie በሚል የፈረንሳይኛ ርዕስ ነው) ብሎ በጻፈው መጽሐፍ ምላሹን ሰጥቷል።

ባጭር ስናስቀምጠው፣ በተቋም (Institute of Marxism Leninism) አማካኝነት ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው The Poverty Of Philosophy መጽሐፍ፣ ሥራዎቹ በገንዘብ እና የኃይል ፖለቲካ ላይ የሚያተኩሩት፤ ጀርመናዊ ፈላስፋ እና የፖለቲካ ተመራማሪው፤ ደመወዝ ተከፋይ ጉልበት ባለበት ሁሉ የመደብ ትግል ይኖራል፤ ይህ የመደብ ትግል ደግሞ በሠራተኞች አሸናፊነትና የበላይነት የሚደመደም ይሆናል የሚል አቋምን የሚያራምደው ካርል ሔንሪክ ማርክስ (5 ሜይ 1818 - 14 ማርች 1883) ለጆሴፍ (Pierre-Joseph Proudhon (1809-1865)) The Philosophy Of Poverty ምላሽ የሰጠበት ተነባቢ መጽሐፍ ነው። ጆሴፍ የፈረንሳይ ሶሻሊዝም አብዮት አራማጅ (ሶሻሊስት)፣ ፖለቲከኛ፣ ፈላስፋ፣ ኢኮኖሚስት፤ እንዲሁም፣ “የመደጋገፍ ፍልስፍና” (mutualist philosophy) መሥራች ፤ “እኔ ሥርዓት አልበኛ (anarchist) ነኝ” ብሎ በማወጅ የመጀመሪያው ሰው፣ በዚህም ምክንያት ”one of anarchism’s most influential theorists”፣ “father of anarchism” የሚል እውቅናን ያተረፈ፤ የ1848ቱን የፈረንሳይ አብዮት ተከትሎ የፓርላማ አባል የነበረ መሆኑ ነው በሕይወት ታሪኩ ላይ ሰፍሮ የሚገኘው።

ሥርዓተ አልበኝነት ”anarchism” የፖለቲካ ፍልስፍና (political philosophy)፣ ሲሆን፤ “ሥርዓተ አልበኝነት መንግሥት ወይንም ሀገር የተባለ አደረጃጀት ጥቅም የለሽ፣ አላስፈላጊ እና ጎጂ ነው ብሎ የሚያምን የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ነው። ሥርዓት አልበኞች ሁሉም መንግሥታት እንዲፈርሱና በምትካቸው ሰዎች ያለምንም ጉልበት ወይም አስገዳጅ ኃይል፣ በራሳቸው ፈቃድ እየተሰባሰቡ የትብብር ማኅበረሰቦች እንዲመሠርቱ ይታገላሉ። አናርኪስም በአውሮጳ አህጉር በ20ኛ ክፍለ ዘመን ተመሥርቶ ወደ ሌላው ዓለም የተስፋፋ ንቅናቄ ነው።” የሚለው ብያኔ ላይ የጋራ ስምምነት አለ።

ለዚህ፣ ለዛሬው ጽሑፋችን መነሻ የሆነው በአንድ ወቅት በማኅበራዊ ሚዲያው (ወንድወሰን እሸቴ በተባሉ ሰው የሀሳብ መሪነት) የውይይት መነሻ (አልዘለቀም እንጂ ቢቀጥል ጥሩ ነበር) ሆኖ የነበረውና “ኢትዮጵያን ምታት ሆኖ የመታት እና እጅ ሰብ ሆኖ ለብዙ መቶ ዓመታት በችጋር አለንጋ ገርፎ በጣም የሚያሰቃያት የትኛው ነው? ‘የድህነት ፍልስፍና’ ወይስ ’የፍልስፍና ድህነት’?” የሚለው ጠጣርና ምናልባትም አስተማሪ የሆነ ሀሳብ ነው። (ምክንያቱ በርዕሳችን የጠቀስነው ይሁን ወይንም አይሁን በውል ባይታወቅም፣ እኛ ሀገር እንደዚህ ዓይነት አስተማሪ የሆኑ የውይይት ሀሳቦች በማኅበራዊ ሚዲያው ላይ ለሳምንት እንኳን የመዝለቅ አቅም የላቸውም። ሌሎቹ፣ መሰዳደብን የመሳሰሉት ግን ...)

እርግጥ ነው፣ የዚህ ጽሑፍ ዓቢይ ዓላማ፣ አስቀድመው እርስ በርሳቸው የተጠዛጠዙትን፣ እነዚህን ሁለት ምድር አንቀጥቅጥ ሥራዎች እዚህ ለመዳኘት ወይም ለማስታረቅ ወይም የበለጠ ለማጠዛጠዝ ... አይደለም። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በቀጥታ ስለ ሥራዎቹ ለማውራትም አይደለም። የዚህ ጽሑፍ ዐቢይ ዓላማ በእነዚህ ሁለት የዓለማችን እውቅ ሥራዎች ተታክኮ የሀገራችንን ሁኔታ ማስተዋል፤ ነፍሱን ይማረውና ደምሴ ፅጌ የሥነጽሑፋችንን የቁልቁለት ጉዞ አይቶ ”ምን አይነት ዳፍንት ነው ሥነጽሑፋችንን ...” ሲል እንዳሄሰው ሁሉ፣ እኛንም ”ምን አይነት ዳፍንት ... እንደ ሆነ ... እንደዚህ ...”፤ ምን አይነት ግርዶሽ እንደ ሆነ እንደዚህ ... ለማመልከት፣ ከተቻለም የውይይት ርዕስ ለመክፈት ነው። ከተቻለም፣ የእነ ውብሸትን ጥያቄ ለማፅናትና የውይይት ወሰኑን ለማስፋት።

ይህ ጽሑፍ እነዚህን ሁለት ለምድር የከበዱ ሥራዎች በተመለከተ ማለት የሚችለው አንድ ጉዳይ ብቻ ሲሆን፣ እሱም አንባቢ ሥራዎቹን ፈልጎ እንዲያነባቸው፣ በንባብ ሂደቱም በአግባቡ ለመገንዘብ ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጥ ማሳሰብ ብቻ ነው።

ድሮ ድሮ የድህነት ጉዳይ የአገር መሪዎችን፤ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ... ጉዳዮችን የተመለከቱ ፖሊሲ አውጪዎችን ብቻ የሚመለከት ሆኖ ነበር የሚታየው። እነሱም ችግሮችን እኛ ብቻ ነን የምንፈታው በማለት በብቸኝነት ሲዳክሩ ነበር አሉ ዘመናትን ያስቆጠሩት። ይሁን እንጂ፣ጉዳዩ በዚሁ አልዘለቀም። ጉዳዩ ብዙም ሳይቆይ በፈላስፎች ሳይቀር ተጠለፈና መፍትሔውን ፍለጋ መዳከሩ፣ መውጣት መውረዱ የሁሉም ሆነና አረፈው። “የሁሉም ...” እንበል እንጂ በጉዳዩ ላይ ከመቆዘም አኳያ ግን ፈላስፎቹን የሚያክል አልተገኘም። ስለ ሰው ልጅ የሚጨነቁቱ፣ ስለ ዓለማችን የወደ ፊት እጣ ፈንታ የሚያብሰለስሉቱ ... ሁሉ ይህንን ርዕስ ጉዳይ ጉዳዬ ብለው በመያዝ ለመፍትሔው ሲጨነቁ (መልካም ተመኚውን፣ ከድህነት ለመውጣት በርካታ ኢኮኖሚያዊ አማራጮች መኖራቸውን የሚጠቁመውን፣ የጄፈሬይ (Jeffrey Sachs)ን The End of Poverty: Economic Possibilities for Our Time ሥራ፤ እንዲሁም፣ ”Philosophy and Poverty”ምን መጥቀስ ይቻላል) ነው እየተስተዋለ ያለው። ይህ ደግሞ ተገቢና የሚጠበቅ ነውና የሚገርም አይሆንም። የሚገርም ሊሆን የሚችለው ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው፣ የፖለቲካ አመራሩን ጀልባ የሚቀዝፉቱ ፀጥ ረጭ ማለትና ስለ ግል ጉዳያቸው መጨነቅ፣ መጠበባቸው ነው።

እስካሁን ከርዕሰ-ጉዳያችን ጋር በተያያዘ ወደ ውጭ ስናይ ቆይተናል። ቀጥለን ደግሞ ወደ ራሳችን፣ ወደ ውስጥ እንመልከትና ጉድፍ ካለብን እሱን እናንሳ።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ታላቅ እና የረዥም ዘመን ታሪክ ባለቤት፣ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሀብትን አብዝታ የታደለች አገር ነች። ይሁን እንጂ፣ ምን አይነት ዳፍንት ... እንደ ሆነ ባይታወቅም፣ ሁሌም ከችግር ወጥታ አታውቅም። በድሮውና በአሁኑ መካከል ያለው የችግሩ ልዩነት አንድ ሲሆን፣ እሱም የዘንድሮው ችግር ከድጡ ወደ ማጡ የመሆኑ ጉዳይ ነው።

ይህን ችግር ለማብራራት የግድ ወደ ኋላ መሄድና ታሪክን ማጣቀስ የለብንም። ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መሰናበቻ ጀምሮ አሁን እስካለንበት፣ 21ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ያለው የ”ከድጡ ወደ ማጡ” ጉዞ ብቻ በቂ ነውና እሱው ላይ እናተኩርና ሀሳብ እንለዋወጥ።

ታሪክ በአግባቡ ሰንዶ እንዳስቀመጠው የእርስ በ’ርስ ጦርነት ተለይቶን አያውቅም። መግደል፣ መጋደል፣ መገዳደል ... (አንዳንዶች እንደሚሉት፣ የጥላሁን ገሠሠን “ግደል ተጋደል / በርታ ወገኔ ...”ን በተሳሳተ መንገድ የተረዳ ትውልድ ሁሉ ተፈጥሯል) የዕለት ተዕለት ሥራችን ሁሉ እስከመሆን ደርሷል። ችግራችን “የድህነት ፍልስፍና” ይሁን፣ ወይም/እና “የፍልስፍና ድህነት”? ቁርጥ ያለውን እሚነግረን ቢጠፋም ከሁለቱ አንዱ፤ ወይም ሁለቱም ስለ መሆናቸው ግን በርካታ አመላካች ክንውኖች አሉ፤ አናነሳቸውም እንጂ ሁለቱም ችግሮቻችን የነበሩበት ወቅት እንደ ነበር ወዳጅም ጠላትም ያውቃል። ”ተከድኖ ይብሰል” ካልሆነ በስተቀር፣ በተለያዩ ጊዜያት ሁለቱም ሰንገው የያዙን ችግሮቻችን እንደ ነበሩ ሳይጠቅሱ መዝለል አይቻልም።

ችግራ(ሮቻ)ችን “የድህነት ፍልስፍና” ይሁን፣ ወይም/እና ”የፍልስፍና ድህነት”? ለይተን ባንናገረውና ባንጋፈጠውም ችግር መኖሩ ላይ ግን እስካሁን የተከራከረ ለማግኘት አልተቻለም። ምን ለማለት ነው፣ ችግር ብቻ አይደለም ችግሮች አሉ።

የአሁኑን፣ “ከድጡ ወደ ማጡ”ን ጉዞ ከድሮዎቹ ለየት የሚያደርገው በርካታ ባህርያት ያሉት ሲሆን ከሁሉም የከፋው ግን ጭካኔው ነው። ችግሩ “የድህነት ፍልስፍና” ይሁን፣ ወይም/እና ”የፍልስፍና ድህነት”? (ሁለቱንም አያድርግብንና እንዳንል አስቀድሞ ሆኗልና) ከስሩ ለይተን ባናሰምርበትም ግን፣ ችግሩ አለ።

እርግጥ ነው ”የኢትዮጵያ ሕዝብ የዋህ ነው። ‘ተከብቤያለሁ’ ላለ ሁሉ ፈጥኖ የሚደርስ ሕዝብ ነው” የሚል ገራገር ይሁን (ወይም፣ አይሁን) አስተያየት አልፎ አልፎም ባይ(ቢ)ሆን ይሰማል። ጥሩ ነው፤ ለተከበበም ሆነ ላልተከበበ መድረስ ችግር የለውም። ምናልባትም ግደል ሲባል መግደልም ችግር የለውም የሚል ሊኖርም ላይኖርም ይችል ይሆን ይሆናል፤ አናውቅም። እንደ አጠቃላይ ግን ችግራችን “የድህነት ፍልስፍና” ይሁን፣ ወይም/እና ”የፍልስፍና ድህነት”? ተለይቶ ቢታወቅ (”ችግሩን ማወቅ የመፍትሔው ግማሽ አካል ነው” እንዲሉ የጥናትና ምርምር ባለሙያዎች) አይጠቅምም ቢባል እንኳን አይጎዳምና እንደ አማራጭ ቢወሰድ ፋይዳው ለሁሉም ነው።

”ድህነት ኢትዮጵያን የሚጎበኛት በዙር ነው” (cycle of poverty ወይም poverty trap) እያሉ ያሙናል። ሲፈልጉ ደግሞ ”አረንጓዴው ድርቅ” እያሉ ዘጋቢ ፊልም ይሠሩብናል። ይሠሩብንና ዓለሙ ሁሉ ይሳለቅብን ዘንድ ለስክሪን ይዳርጉናል። ”እነዚህ ሰዎች ችግራቸው ምንድን ነው?” ሲሉ ራሳቸውን ይጠይቁና በሆዳቸው ”ችግራቸው ’የድህነት ፍልስፍና’ እና ’የፍልስፍና ድህነት’ ነውን?” ሲሉ መልሰው ራሳቸውን መልስ አከል ጥያቄን ይጠይቃሉ። በዚህ ሳያበቁም ወደ ጦርነት ታሪክና ባህላችን ይመጣሉ።

“እርግጥ የጦርነት ታሪካቸው በጀግንነት የታጀበ፣ በድልም ያሸበረቀ ነው። ወደ እርስ በ’ርሳቸው ሲመጣ (“መ” ይጠብቃል) ግን፣ ይህ የጦርነት ታሪክና ባህላቸው ግን ከደረጃ በታች ያወርዳቸዋል። በደማቁ የተፃፈላቸውን የማንነት፣ የሀበሻነት ታሪካቸውን ... ሁሉ ይዞት ገደል ይገባል። ‘ችግራቸው ምንድን ነው?’ ተብሎ ይጠየቅ ዘንድም ግድ ይላል። ‘የድህነት ፍልስፍና’ ወይስ/እና ‘የፍልስፍና ድህነት’? ተብሎ ይጠረጠር ዘንድም ይጋብዛል። በ21ኛው ክፍለ ዘመን በዚህ አይነት የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ መግባትስ ኢትዮጵያን ይመጥናልን? የሚል ጥያቄ በአዕምሮ ይጫር ዘንድም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።” እያሉ የሚያወሩት፤ በማለትም የሚጽፉት ቁጥራቸው እለት በእለት እየጨመረ ነው።

እንደገናም፣ “ምክንያቱ ምንድን ነው?” ተብሎ ይጠየቅ ዘንድም ያስገድዳል። መልሱንም ሁለቱም (“የድህነት ፍልስፍና” እና “የፍልስፍና ድህነት”) ወይም ”ከሁለቱ አንዱ” ተብሎ ፍርጥ አድርጎ ለመመለስም ያስገድዳል። እውነት እውነት፣ ችግሩ ምንድን ነው ግን???

ድሮ ድሮ በሰላምና በፍቅር አጥብቀው የሚያምኑት ኢትዮጵያውያን ዛሬ ጭር ሲል አይወዱም እያሉም ያሙናል ነው የሚባለው። እውነት ከሆነ በእውነት ያሳዝናል። ችግሩን ለይቶ ለማወቅ ይቻል ዘንድም ችግሩ “የድህነት ፍልስፍና” ወይስ/እና “የፍልስፍና ድህነት”? ተብሎ ይጠየቅ ዘንድም ሁኔታዎች ከታች እስከ ላይ፤ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ፤ ከሰሜን እስከ ደቡብ ... ያስገድዳሉ። ጉዞው ”ከድጡ ወደ ማጡ ...” ቢሆንም፣ በሰላም ውሎ በሰላም እያደረ ያለ ስፍራ እስኪገኝ ድረስ ሁሉ ያስኳትናሉ (ካለ)። ይህም ይመስላል በመግቢያችን ላይ የጠቀስናቸው ሁለት ጎምቱዎች በ”የድህነት ፍልስፍና” እና በ”የፍልስፍና ድህነት” መካከል ሆነው (ለአንድ ዓላማ?) የተፋለሙት።

መቼም፣ የትም ሆነ የት ችግር ያለ ምክንያት አይከሰትም። ማለትም የማይፈታ ችግር የሌለውን ያህል ምክንያት የሌለው ችግርም የለም። ሳቢያና ውጤት የሌለው ችግርም የለም። ችግሩ እነዚህን ለይቶ፣ ፈልፍሎ ማውጣቱና የችግሩ መንስኤ “የድህነት ፍልስፍና” ነው ወይስ/እና የ”የፍልስፍና ድህነት” የሚለውን ማመልከቱ ላይ ነው። ይህን ማድረግ ከተቻለ ከላይ እንዳልነው የችግሮቻችን መፍትሔ በግማሽ ተገኘ ማለት ነውና ሴትየዋ ”እልል በቅምጤ” እንዳሉት እልልልልል... ያሰኛል።

ባጠቃላይ፣ ችግሮቻችን ተቆጥረው አያልቁም። በተለይ አሁን አሁን በውክልና የዓለምን ችግሮች ሁሉ እኛ እያስተናገድን ይመስላል። ረሀብ አለ። ጦርነት አለ። የእርስ በእርስ መቆራቆስ አለ። ሙስናው ጣራ ነክቷል። ዘረኝነት ተንሰራፍቷል። የትምህርት ጥራት ጉዳይ ተከድኖ ይብሰል ከተባለ ቆየ። የኑሮ ውድነት ቅጡን አጥቷል። ሕገ ወጥነት ሕጋዊ እየሆነ ነው። ሕዝባዊ አገልግሎት ከተመሰቃቀለ ቆየ። እዚህ አገር ምን የሌለ ችግር አለ? ምንም። በመሆኑ የችግሮቻችን ሁሉ መንስኤ “የድህነት ፍልስፍና” ወይስ/እና “የፍልስፍና ድህነት” የሚለው ላይ ከምር መነጋገር ያስፈልጋል። ቸር እንሰንብት።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለገና በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ፤ መጪው የገና በዓል የሰላም የጤና የፍቅርና የተስፋ እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቱን ይገልጻል። ክቡራን ደንበኞቻችን ተቋማችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የደንበኞች የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ፈጣን እና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ እየተጋ ይገኛል። ውድ ደንበኞቻችን የክፍያ አገልግሎትን ለማግኘት ሲባል የሚገጭማችሁን የጊዜ ብክነት እና እንግልት ለመቀነስ ተቋማችን ባቀረበው ዘመናዊ የክፍያ አማራጮች ማለትም በሞባይል ባንኪንግ፤ በኢንተርኔት ባንኪንግ፣ በሲቢኢ ብር፤ በቴሌ ብር እና በአቅራቢያችሁ በሚገኝ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በመሄድ ወራዊ የፍጆታ ሂሳባችሁን በተቀመጠላችሁ የመክፈያ ጊዜ እንድትከፍሉ እያሳሰበ ተቋማችን የብልሹ አሰራር ችግሮችን ከመሰረቱ ለመቅረፍ በዋናነት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ እና ጥቆማዎችን ተቀብሎ ተገቢውን የማጣራት ስራ በመስራት አስፈላጊውን እርምጃ እየወሰደ ይገኛል። ውድ ደንበኞቻችን የትኛውንም አገልግሎት ለማግኘት ው አገልግሎት መስጫ ማዕከል ስትመጡ ለሚገጥሟችሁ አንዳንድ ብልሹ አሰራሮች በቢሮ ስልክ 0116366000 ስነ-ምግባር ክፍል በመደወል እና ጥቆማችሁን በማስመዝገብ የበኩላችሁን ድርሻ እንድትወጡ ያሳውቃል። በተጨማሪም በየትኛውም ቦታ ላይ ለህዝብ አገልግሎት ሲባል ተዘርግተው ያሉ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማቶች የሚፈፀሙ ስርቆቶች ሲፈፀሙ አስፈላጊውን ጥቆማ በመስጠት የበኩላችሁን ድርሻ እንድትወጡ እያልን በድጋሚ መጪው በዓል የሰላም፤
የአብሮነትና መተሳሰብ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።

## መልካም የገና በዓል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት

SINCE 1906
ብሔራዊ
NATIONAL
ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ
NATIONAL ALCOHOL & LIQUOR FACTORY




ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለጌታችን ለመድሀኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ በዓሉ የሰላምና የደስታ እንዲሆንልዎ መልካም ምኞቱን ይገልፃል ።

ድርጅታችን በመጠጥ ኢንዱስትሪው ዘርፍ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባለቤት ሲሆን ጥራታቸውን የጠበቁና በህብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፉ የተለያዩ የአልኮል መጠጦችን በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ገበያ እያቀረበ ያለ መንግስታዊ ተቋም ነው። በመሆኑም ድርጅታችን ባስመዘገበው ስኬቶች WorldCOB በሚያዘጋጀው ከዓለም 130 ሀገራት ከሚገኙበት ከ3500 ድርጅቶች ውስጥ ተመርጦ የ2022 BIZZ AWARED ተሸላሚ መሆኑን ስንገልጽ በታላቅ ደስታ ነው።

በዓል አድማቂ በሆኑ ምርቶቻችን ይደሰቱ!!

መልካም በዓል!!
ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ

Phone: - +251 115 15 65 86/ +251 115 15 61 90
Mobile: - +251 941 74 74 74/ +251 960 74 74 74
+251 903 14 44 44
Fax: - +251 115 51 32 99 / P.O.Box: - 3516
Email: - info@nalf.com.et
Website: www.nalf.com.et

ኢኮኖሚ

## መሠረተ ልማት

# አሳሳቢው የቢሮ ህንጻ ኪራይ ወጪ

**መሳኩ ኤርሴ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለመንግስት ተቋማት የቢሮ ኪራይ የሚወጣው ወጪ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት በከተማ አስተዳደሩ ላይ ጫና ማሳደር ከጀመረ ቆይቷል። አብዛኞቹ የከተማ አስተዳደሩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች እና ወረዳዎች የራሳቸው ቢሮ የሌላቸው መሆኑ በከተማ አስተዳደሩ ላይ እያሳደረ ካለው ጫና ባሻገር የሚከራዩ ህንጻዎች ተቋማቱ መደበኛ ሥራዎቻቸውን እንዲያከናወኑ የማይመቹ፣ ለሥራ ተነሳሽነት የማያበረታቱና የማይማርኩ፣ ለተገልጋይ ደንበኛም ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት የማይጋብዙ ናቸው። በሌላ በኩል ከተማ አስተዳደሩ ለሌሎች መሰረተ-ልማቶች ማዋል የነበረበትን ከፍተኛ መዋዕለ-ነዋይ ለኪራይ ወጭ በመዳረጉ ለከተማው እድገት እንቅፋት እንደሚሆን አጠያያቂ አይደለም።

ከአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው፤ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ ካሉት አጠቃላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች 65 በመቶ የሚሆኑት የመንግስት ተቋማት የራሳቸው ህንጻ የላቸውም። እነዚህ መስሪያ ቤቶች ቢሮ ተከራይተው ነው አገልግሎት የሚሰጡት። ህንጻ አላቸው የሚባሉትም ብዙ ችግር የሚስተዋልባቸውና እጅግ የተጣበቡ ናቸው።

የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ስራ አስኪያጅ አቶ የሱፍ ኢብራሂም እንደሚሉት፤ በከተማዋ የክፍለ ከተሞችን የቢሮ ችግር በአመዛኙ መቅረፍ የተቻለ ቢሆንም፣ ለከተማ አስተዳደሩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች እና ለወረዳዎች የሚፈጸመው የቢሮ ኪራይ በጣም አሳሳቢ ሆኗል። የቢሮ ኪራዩ የከተማ አስተዳደሩን የገንዘብ አቅም እየተፈታተነው ይገኛል። ለቢሮ ኪራይ ብቻ በአንድ ዓመት ከአንድ ቢሊየን ብር በላይ ወጪ እየተደረገ ነው። ለቢሮ ኪራይ እየወጣ ያለው ወጪ የከተማውን ሌሎች አንገብጋቢ ችግሮችን ለመፍታት ሊውል የሚገባ ነበር።

የቢሮ ኪራይ እያስከተለ ያለው ችግር በገንዘብ ብቻ የሚተመን አይደለም የሚሉት አቶ የሱፍ፤ የከተማ አስተዳደሩ ለቢሮ ኪራይ የሚያወጣው ወጪ የከተማዋን የህንጻ ኪራይ ስርዓት አጠቃላይ ገበያውንም እየረበሸ ነው ብለዋል። ከመንግስት በጀት የሚከፈል ገንዘብ ነው በሚል የመንግስት መስሪያ ቤቶች በካሬ ሜትር እስከ አንድ ሺህ ብር የሚከራዩበት ሁኔታም እንዳለ ጠቅሰው፣ ይህ የኪራይ ዋጋ እንዲንር እያደረገ ነው ይላሉ። ነጋዴዎች ህንጻ ተከራይተው እንዳይሰሩ እንቅፋት እየሆነ መምጣቱንም ጠቁመዋል።

ለመንግስት ተቋማት የሚፈጸመው ህንጻ ኪራይ ለሙስናና ብልሹ አሰራርም የተጋለጠ መሆኑንም በመጠቆም፣ ሁሉም አመራር በሚመቸው መንገድ በተበታተነ መልኩ የሚመራው መሆኑን ያመለከቱት። ስታንዳርድ የሌለው፣ የገበያ ጥናት የማይደረግበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም በርካታ መዘዞችን ሲያስከትል እንደነበር አቶ የሱፍ ጠቁመዋል።

የባለስልጣኑ ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ ይድነቃቸው በበኩላቸው፤ አቶ የሱፍ ያነሷቸውን ችግሮች ይጋሩና ተጨማሪ ችግሮችንም ይዘረዝራሉ። አብዛኞቹ በኪራይ የሚያዙ ቢሮዎች መደበኛ ሥራዎችን ለማከናወን የማይመቹ፣ ለስራ ተነሳሽነት የማያበረታቱና የማይማርኩ መሆናቸውን ያመለክታሉ። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ችግሩ አገልግሎት አሰጣጡ የተበታተነ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል። ተገልጋዩ በአንድ ቦታ ላይ የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘት አይችልም። የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት በአስሩም ክፍለ ከተሞች የተበታተኑ ቢሮዎች መሄድ ይጠበቅበታል። እነዚህ ቢሮዎች በአንድ ቦታ ተገንብተው አገልግሎት መስጠት ቢጀምሩ በመጀመሪያ የአገልግሎት አሰጣጡን በጣም ያቀላጥፋል። ይህም የመልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ችግር እያስከተለ ነው።

ምቹ የሆኑ ህንጻዎችን መከራየት ብዙ ወጪ ስለሚያስወጣ አብዛኞቹ ተቋማት ወጪ ለመቀነስ በሚል ምቹ ያልሆኑ ህንጻዎች ተከራይተው ለመስራት እንደሚገደዱም አመልክተዋል። አብዛኞቹ ህንጻዎች ለተገልጋዩም ለአገልጋዩም አስቸጋሪና ቀልጣፋና ፈጣን



አገልግሎት ለመስጠት የማይጋብዙ ናቸው።

እንደ አቶ ይድነቃቸው ማብራሪያ፤ አብዛኞቹ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተከራይተው የሚሰሩ በመሆናቸው አገልግሎት መስጫ ህንጻዎች ማሟላት አለባቸው ተብለው በመንግስት የተቀመጡ አገልግሎቶችን ለማሟላት ጭምር ችግር እየሆነ ነው። ለምሳሌ የህጻናት ማቆያዎች አንድ የመንግስት ህንጻ የግድ ማሟላት አለበት። በአዋጁ መሰረት ሴቶች ህጻናትን ይዘው መስሪያ ቤት ድረስ በመሄድ መንከባከብ አለባቸው። ለዚህ ደግሞ እያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት የህጻናት ማቆያ መገንባት እንዳለበት በአዋጅ ተደንግጓል።

የመንግስት ተቋማት ተከራይተው በሚኖሩባቸው ህንጻዎች ላይ በቂ ቦታ ባለመኖሩ የህጻናት ማቆያ ለማዘጋጀት ከለለ። የካፌ አገልግሎት፣ የመኪና ማቆሚያ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ አገልግሎቶችን መስጫዎችም መኖር እንዳለባቸው የተቀመጠ ቢሆንም፣ በኪራይ ቢሮዎች አገልግሎት የሚሰጡ መስሪያ ቤቶች እነዚህን አገልግሎቶችን ለመስጠት አዳጋች ሆኖባቸዋል።

በቋሚነት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ነገሮችን ለመስራትም ችግር እየፈጠረ ነው። ብዙ ተቋማት በቴክኖሎጂ ስራቸውን ማዘመን ቢፈልጉም፣ በተከራዩባቸው ቦታዎች የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶች ቋሚ ስላልሆኑ እንቅፋት እየሆነ ነው። እነዚህ መሰረተ ልማቶች እጅግ ውድ በመሆናቸው ቢሮዎች በተቀየሩ ቁጥር ለመቀየርም አዳጋች ናቸው። መንግስትን ለከባድ ወጪ ይዳርጋሉ። ኪራዩ የሚፈጥራቸው ችግሮች ዘርፈ ብዙ መሆናቸውን አቶ ይድነቃቸው ያብራራሉ።

ከቢሮ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ እንደነበር የሚያነሱት አቶ ይድነቃቸው፣ በተደረገው ጥረት በተለይም በክፍለ ከተሞች ደረጃ የነበረው የቢሮ ችግር በአመዛኙ መቀረፉን አንስተዋል። በክፍለ ከተማ ደረጃ ግን ሁለት ክፍለ ከተሞች ብቻ ናቸው። በኪራይ ቢሮ ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ ያሉት። 9ኙ የራሳቸውን ህንጻ አስገንብተው ባስገነቡት ህንጻ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ጠቁመዋል።

ሁለቱ ክፍለ ከተሞች የራሳቸው ህንጻ ባለቤት ለመሆን ሂደት ላይ መሆናቸውን ያነሱት አቶ ይድነቃቸው፤ የራሱ ህንጻ ግንባታ ያላጠናቀቀው የልደታ ክፍለ ከተማ የግንባታ ስራው መቋረጡን ይጠቅሳሉ። ግንባታው እንዲቋረጥ ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ፈጥኖ በማስወገድ ግንባታውን ማስቀጠል እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

እንደ አቶ ይድነቃቸው ገለጻ፤ አዲስ የተቋቋመው ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ደግሞ የራሱን ለመገንባት ቦታ አዘጋጅቶ ዝግጅት እያደረገ ነው። በክፍለ ከተማ ደረጃ ያለው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የህንጻ ችግር በአጭር ጊዜ ውስጥ ይፈታል ተብሎ ይታሰባል።

በከተማዋ የከፋ የቢሮ ችግር ያለው በወረዳ ደረጃ ነው የሚሉት አቶ ይድነቃቸው፤ ወደ 120 የሚሆኑ የወረዳ የመንግስት ተቋማት ህንጻ ተከራይተው አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን ጠቁመዋል። የራሳቸው ህንጻ ያላቸው ጥቂት ወረዳዎች ቢኖሩም፣ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ህንጻዎች እጅግ ጠባብ መሆናቸውን ይገልጻሉ። ቀደም ሲል 70 የሰው ሀይል ይይዛሉ ተብለው የተሰሩ እንደሆኑም ተናግረው፣ የወደፊት ሁኔታን ታሳቢ ሳያደርጉ የተገነቡ እንደሆኑም ነው ያመለከቱት። በአሁኑ ወቅት ወረዳዎች ከ400 እስከ 500 የሰው ሀይል አላቸው ይላሉ።

የባለስልጣኑ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ የሱፍ እንደሚሉት፤ የመንግስት ቢሮዎች ከኪራይ ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ አማራጭ በመፍትሄነት እየተወሰዱ ነው። ችግሩን በዘላቂነት መፍታት የሚቻለው ሁሉም ተቋማት የራሳቸው ህንጻ እንዲኖራቸው በማድረግ ሲሆን ፣ የራሳቸው ህንጻ እስኪኖራቸው ድረስ ደግሞ ከቢሮ ኪራይ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ የእርምት እርምጃዎች ተወስደዋል።

ከዚህ በፊት ከቢሮ ኪራይ ጋር ተያይዞ ይፈጸሙ የነበሩ ህገ ወጥ ተግባራትን ለመከላከል የቢሮ የኪራይ ጣራ ተቀምጧል፤ ስታንዳርድም ተዘጋጅቷል። የትኛውም መስሪያ ቤት ከዚያ ጣራ እና ስታንዳርድ ውጭ መከራየት አይችልም። በገበያ ውስጥ የዋጋ ለውጥ ካለ ደግሞ የገበያ ጥናት በየስድስት ወሩ እየተካሄደ ነው። ማሻሻያ መደረግ ካለበትም በዚያ የገበያ ዋጋ ላይ በመመርኮዝ ይታያል። በተጋነነ ዋጋ ተከራይተው የነበሩትን ባለስልጣኑ ከነበሩበት ህንጻ ማስወጣቱን ነው የጠቆሙት።

ለአብነት ያህል በየካ ክፍለ ከተማ በካሬ እስከ አንድ ሺህ ሲከፈል የነበረ ሲሆን፣ የኪራዩ ዋጋ የተጋነነ በመሆኑ ባለስልጣኑ አስወጥቷል። በዚህም በክፍለ ከተማው የነበረው የተጋነነ የህንጻ ኪራይ ቀንሷል። በየካ በካሬ እስከ ከ200 እስከ 350 ብር ወርዷል። እነዚህ የመንግስት ተቋማት በብዙ ሺህ ካሬዎች የሚለካ ህንጻ በሚከራዩበት ወቅት በመንግስት በጀት ላይ ያለው ጫና ከፍ ያለ ነው ይላሉ።

በተለይም ለሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚሆን ህንጻ ተገንብቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ የግብር ከፋዩን ገንዘብ ከብክነት በጸዳ መንገድ በአግባቡ መጠቀም እንዲቻል እንዲሁም ህገ ወጥ ተግባራትን በሚፈጽሙት ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል ስርዓት እየተገነባ ነው።

ማንኛውም ቢሮ ያለ መዋቅር በራሱ ቢሮ መከራየት አይችልም ያሉት ዋና ስራ አስኪያጁ፣ የውል መነሻ እና የባለስልጣኑን ጥናት መሰረት አድርገው እንዲከራዩ መደረጉን ይገልጻሉ። ያም ቢሆን በጨረታ ህጉ መሰረት ነው ውድድር የሚደረገው ይላሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት ግን የጨረታ ህጉን ወደ ጎን በመተው ኪራይ ሲፈጸም ነበር። ያ ደግሞ ከጀርባ ችግር ሲፈጥር ቆይቷል። ተገልጋዩን እና አገልጋዩን ለችግር ሲያጋልጥ ነበር። መንገድ በሌለበት፣ ለትራንስፖርት ምቹ ባልሆነበት እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ባልተሟሉበት አመራሩ ሰራተኛውን በመጫን ምቹ ያልሆነ ቦታ ላይ ሲያስገባ ቆይቷል።

አቶ የሱፍ ከቢሮ ኪራይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ችግሮችን በመሰረታዊነት መቅረፍ የሚቻለው ለከተማው ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚሆን ግዙፍ ህንጻ በመገንባት እንዲሁም እያንዳንዱ ወረዳ የራሱ የቢሮ ህንጻ ባለቤት እንዲሆኑ በማድረግ ነው ሲሉ ያብራራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ በዚህም መሰረት ለሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚሆን ግዙፍ ህንጻ ለመገንባት ዝግጅት እየተደረገ ነው። ለአብነትም ግዙፍ ህንጻ መገናኛ አካባቢ ለመገንባት ዝግጅት ተደርጎም ነበር። ለህንጻው የሚሆን 6 ነጥብ 2 ሄክታር መሬት ከተዘጋጀ በኋላ የአዋጭነት ጥናት ሲካሄድ ቦታው በጣም የተጨናነቀ ስለሆነ፤ ተጨማሪ ግዙፍ ህንጻ በአካባቢው ሲገነባ በቀጣይ የበለጠ መጨናነቅ ስለሚፈጠር ቦታውን መቀየር አስፈልጓል።

በአሁኑ ወቅት ጥቁር አምበሳ አካባቢ ከተክለ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን እስከ ጎማ ቁጠባ ወደ 11 ነጥብ 6 ሄክታር ቦታ ተዘጋጅቷል። ይህንን ቦታ የመጥረግ እና የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ ነው። የሚገነባው ህንጻ 20 የሚሆኑ ሴክተር መስሪያ ቤቶችን በአንድ ላይ ለማሰባሰብ ያስችላል። ካርታው በመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ስም ተሰርቷል። የጨረታ እና ቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቀዋል።

በቦታው ላይ ያሉ ባለመብቶችን ህግን በተከተለ መንገድ የማስነሳት ስራ እየተሰራ መሆኑን የሚያነሱት አቶ የሱፍ፣ ፕሮጀክቱ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ ትልቅ ፕሮጀክት መሆኑን ያመለከቱት። ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የሴክተር መስሪያ ቤቶችን የቢሮ ችግር በዘላቂነት እንደሚፈታና ለከተማ አስተዳደሩ እፎይታ እንደሚሰጥና በየዓመቱ የሚወጣውንም ወጪ እንደሚያስቀር መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የፕሮጀክቱ ግንባታ በቀጣይ አንድ ዓመት ውስጥ ለመጀመር ታስቧል። ባለስልጣኑ ለፕሮጀክቱ ግንባታ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጓል። የሚቀረው የበጀት ጉዳይ ነው። ፕሮጀክቱ የሚጠይቀው ገንዘብ ከፍተኛ ስለሆነ ሀገሪቱ አሁን ካለችበት የኢኮኖሚ ሁኔታ አንጻር ሌሎች አንገብጋቢ ፕሮጀክቶችን የማስቀደም ፍላጎቶች በመንግስት በኩል ስለታየ የጊዜ ማስተካከያ ሊኖር ይችላል።

በወረዳዎች የሚስተዋለውን የቢሮ ችግር ለመቅረፍ ደግሞ ለወረዳ ስማርት ቢሮዎችን ለማዘጋጀት ባለስልጣኑ ከሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ጋር በመተባበር በጣም ውጤታማ ስራዎች እየተሰሩ ነው ብለዋል። ስማርት ቢሮዎች ተገንብተው ሲጠናቀቁ በወረዳዎች የሚታዩ ከቢሮ እጥረት ጋር የተያያዙ ችግሮች ይቀርፋሉ ተብሎ ይታሰባል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጸብና መለያየትን በመሻር "በጌታ ኢየሱስ" ልደት የተገኘውን አንድነት ማጽናት ይገባል

የሰው ልጅ በምድር ሲኖር፤ በጸብ ፈንታ ፍቅርን፣ በልዩነት ፈንታ አንድነትን፣ በስንፍና ፈንታ ታታሪነትን፣ በቂምና በቀል ፈንታ ይቅር ባይነትና እርቅን፣... ይላበስ ዘንድ የተገባ ነው፡፡ ሆኖም ለጽድቅ የተፈጠረው ሰው ሐጢያትን፣ ለፍቅር የተፈጠረው ሰው ጸብን፣ ለአብሮነት የተፈጠረው ሰው መገፋፋትና መለያየትን፣ ለሰላም እና ይቅር ባይነት የተፈጠረው ሰው ቂምና በቀልን፣ ሰርቶ በላቡ እንዲኖር የተፈጠረው ሰው ሌብነትና ቀማኛነትን፤... በመምረጡ ጽድቁ ወደ ሃጥያት፤ ሰላሙም ወደ ጭንቀት፣ ፍርሃትና ጦረኝነት፣ ክብሩም ወደ ውርደት፣ ልጅነቱም ወደ ተቅበዝባዥነት እንዲለወጥ ሆነ፡፡

በዚህም የሰው ክቡርነት፣ የሰው ኃያልነት፣ የሰው መልካምነት፣ የሰው የጽድቅ መንግስት ወራሽነት ተሸሮ፤ የሃጢያት ደብዳቤ ተጻፈበት፣ የሞት ፍርድ ወደቀበት፡፡ ይሁን እንጂ ፈጥሮ ፍጥረቱን የማይዘነጋ አምላኩ በይቅርታ ሊመልሰው፤ በምህረት ሊጎበኘው ፈቅዶ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ እና ከሰው ወገን ከሆነችው ድንግል ማርያም ተወልዶ የምህረቱን ልክ፣ የይቅርታውን ጥግ ገልጦ አስተማረው፡፡ ዛሬ በመላው የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ተከብሮ የሚውለው "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ" የልደት በዓል ይሄንኑ በሃጢያት የወደቀና በሞት ፍርድ ውስጥ የነበረን የሰው ልጅ የማዳን ሥራን በልደቱ አንድ ብሎ የጀመረበትን ድንቅ ስራ የሚያሳስብ ነው፡፡

የልደቱን ዕለት የማሰብ ሂደቱ ቀዳሚው ጉዳይ የሰው ልጅ በደሉ ተሰርዮ ከሞት ወደ ሕይወት እንዲሸጋገር የመደረጉ ሥራ ይሁን እንጂ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በልደቱ ሥራ የሰው ልጅ ቀደም ባሉት 5ሺህ 500 ዓመታት ጉዞው ታሪክ የቀየረበት፤ ቂሙን በይቅርታ፤ መለያየቱን በአንድነት እንዲተካ ያደረገበትም ጭምር ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ዛሬ የሚከበረውን የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ ባስተላለፉት መልዕክት፣ "በክርስቲያኖች ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የዕርቅ መጀመሪያ ተደርጎ ይታሰባል" ሲሉ መግለጻቸውም ለዚሁ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው እንዳሰፈሩት፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት በፈጣሪና በፍጡር፣ በሰማይና በምድር፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ታላቅ የጠብ ግድግዳ ተገንብቶ ለብዙ ዘመናት ቆይቷል። በመሆኑም የልደት በዓል "ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ" የሚለው የፈጣሪ ቃል በተግባር መፈጸም የጀመረበት፤ በአምላክና በሰው ልጆች መካከል ዕርቅ የተወጠነበት ዕለት ነው። መለያየት የጠፋበት፣ ኅብረትና አንድነት የጸናበት፤ መለኮትና ሥጋ፣ ህያውና ሟች፣ ዘላለማዊና ጊዜያዊ፣ ፈጣሪና ፍጡር፣ ሰማያዊና ምድራዊ፣ ምሉዕና ውሱን፣ ተዋህደው አንድ ሆነው አዲስ የምሥራች የተበሰረበት ነው፡፡ ዕለቱ የሰማይና የምድር ፍጡራንን በደስታ ሞልቶ በቤተልሔም ከተማ በአንድነት እንዲዘምሩ አድርጓል። ተራርቀው የሚኖሩትን አሰባስቦ በአንድነት እንዲዘምሩ ያደረጋቸው ጉዳይ ከትናንት ለየቅል ታሪካቸው ይልቅ የነገ የጋራ ተስፋቸው ብሩህ ሆኖ ስለታያቸው ነው።

ዛሬም በኢትዮጵያ ይሄንን የአንድነት፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የይቅርታና እርቅ ተግባር አብዝተው የሚሹ አያሌ ጉዳዮች አሉ፡፡ ምክንያቱም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በጠብና በመለየት ምክንያት ኀዘንና ሰቆቃው በዝቶ በሰው ልጆች ታሪክ ጊዜው ዘመነ-ፍዳ ይሰኝ እንደነበረው ሁሉ፤ ዛሬም በኢትዮጵያ የተዛቡ የታሪክ ትርክቶች፣ ይሄን ተከትለው የተገለጡ አለመግባባቶች፣ መገፋፋቶች፣ መለያየቶች፣ ግጭትና ግድያዎች፣ አለፍ ሲልም የእርስ በእርስ ጦርነቶች ከትናታችን እንዳንሻገር፤ ዛሬ ላይ እንድንፈተን፤ ነገን በጋራ እሳቤ በሙላት እንዳንመለከት እንቅፋት እየሆኑብን ይገኛሉ፡፡ እናም ይሄን የመለያየት ግንብ የሚሰብር፣ የነገ የጋራ ተስፋን ግርዶሽ የሚገልጥ፣ የፍቅርና አንድነት፣ የይቅርታና እርቅን መንገድ የሚጠርግ እሳቤ ያስፈልጋል፡፡

ምክንያቱም በፍቅር እና በይቅርታ የተሳሰሩ ሕዝቦች በወል ተስፋቸው የነገውን በጋራ ከተጋሩት፣ በነገው ላይ ከተግባቡ በትናንቱ ላይ መስማማት አይፈትናቸውም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው እንዳሉትም፤ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ መለያየት የመጣው እንዲሁ አይደለም። ሆን ተብሎ ተሠርቶበት ነው። ክፋው ሆን ብሎ የልዩነትን ዘር ዘርቶ፣ የልዩነትን እሾህ አብቅሎ፣ የጠላትነትን ፍሬ እንዲያፈራ አድርጓል። ልዩነቱም ከመለያየት አልፎ ወደ ጠላትነት እንዲሻገር ሠርቷል። ... ጦርነትና ግጭትን አትርፏል። በዚህ ሁሉ ጠላት እንጂ ማንም አልተጠቀመም።

እናም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያውያን የነገዋን ኢትዮጵያ የተሻለች ለማድረግ ከዚህ የልደት ታሪክ ብዙ ትምህርት ብንወስድ ይጠቅመናል። ዛሬ እዚህም እዚያም የምናየው የመለያየትና የመጠፋፋት አባዜ የባህሪያችን አይደለም። የማናችንም ማንነት መገለጫ አይደለም። ይህ የተዘራብን ክፉ ዘር ውጤት ነው። የጠላታችን ዓላማ ደግሞ አንዳችንን ጠቅሞ ሌላችንን መጉዳት ሳይሆን ሁላችንንም ማጥፋት ነው። ጠላታችን አንዱን ሕዝብ ከሌላው በማጋጨት አይቆምም፤ አንዱንም ሕዝብ እርስ በርሱም ያባላዋል። ክልልን ከክልል፣ ዞንን ከዞን፣ ወረዳን ከወረዳ፣ ጎጥን ከጎጥ፣ ቤተሰብን ከቤተሰብ፣ ባልን ከሚስት፣ ልጆችን ከወላጆች እያባላ ዓለምን ሁሉ የግጭትና የጠብ አውድማ ማድረግ ነው ምኞቱ። ስለዚህ ቆም ብለን እናስብ። ምክንያቱም ታሪክ ማለፉ አይቀርም። ታሪክ መለወጡም አይቀርም። ቁም ነገሩ "የታሪክ ተከሳሽና ተወቃሽ ወይንስ ተዘካሪና ተሞጋሽ እንሆናለን?" የሚለው ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን ከፍ ወዳለው ብልጽግና ለማሻገር ፀብና መለያየትን በመሻር "በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ" ልደት የተገኘውን አንድነት ማጽናት ይገባል፡፡

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስተወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

## "ኢትዮጵያውያን የነገዋን ኢትዮጵያ የተሻለች ለማድረግ ከዚህ የልደት ታሪክ ብዙ ትምህርት ብንወስድ ይጠቅመናል"

**- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ**

**/የገናን በዓል አስመልክተው ያስተላለፉት መልእክት ሙሉ ቃል/**

እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ!

በክርስቲያኖች ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የዕርቅ መጀመሪያ ተደርጎ ይታሰባል። ከልደቱ በፊት በፈጣሪና በፍጡር፣ በሰማይና በምድር፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ታላቅ የጠብ ግድግዳ ተገንብቶ ለብዙ ዘመናት ቆይቷል። የልደት በዓል "ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ" የሚለው የፈጣሪ ቃል በተግባር መፈጸም የጀመረበት፤ በአምላክና በሰው ልጆች መካከል ዕርቅ የተወጠነባት ዕለት ናት።

ይህ በዓል መለያየት የጠፋበት፣ ኅብረትና አንድነት የጸናበት፤ መለኮትና ሥጋ፣ ህያውና ሟች፣ ዘላለማዊና ጊዜያዊ፣ ፈጣሪና ፍጡር፣ ሰማያዊና ምድራዊ፣ ምሉዕና ውሱን፣ በተዋሕዶ አንድ ሆነው አዲስ የምሥራች የተበሰረበት ነው። ክፋው በዘራው ዘር መለያየት ነግሦ፣ በሰማይና በምድር መካከል የማይሞላ ገደል ተፈጥሮ እንኖር ነበር። በጠብና በመለየት ምክንያት ኀዘንና ሰቆቃው በዝቶ በሰው ልጆች ታሪክ ጊዜው ዘመነ-ፍዳ ይሰኝ ነበር። የክርስቶስ መወለድ የራቀን አቅርቦ፣ የጠፋውን አግኝቶ፣ የፈረሰውን ገንብቶ፣ የፍዳውን ዘመን ወደ ምሕረት በመቀየር በዘላለማዊ ዕርቅ አንድ አደረገን።

የልደቱ ብሥራት እረኞችን ከሜዳ፣ ሰብአ ሰገልን ከሩቅ ከምሥራቅ ወደ አንድ አምጥቷል፤ ሰዎችን ከምድር ጠርቷል፤ መላእክትን ከሰማይ አውርዷል። ዕለቱ የሰማይና የምድር ፍጡራንን በደስታ ሞልቶ በቤተልሔም ከተማ በአንድነት እንዲዘምሩ አድርጓል። ተራርቀው የሚኖሩትን አሰባስቦ በአንድነት እንዲዘምሩ ያደረጋቸው ጉዳይ ከትናንት ለየቅል ታሪካቸው ይልቅ የነገ የጋራ ተስፋቸው ብሩህ ሆኖ ስለታያቸው ነው። እረኞችና ሰብአ ሰገል በትናንት ታሪካቸው የሚገናኙት በጥቂት ነው። ሰዎችና መላእክት በትናንት ሕይወታቸው የሚገናኙት በጥቂት ነው። የነገው ታሪካቸው ግን አዲስ፣ በደቦ የሚሠሩት፣ በጋራ የሚኖሩት፣ በአንድ የሚወርሱትና በሙላት የሚኖሩበት ነው። ለዚህ ነው ዛሬ የሁሉንም ታሪክ ከክርስቶስ ልደት ጋር አስተሣሥረን የምንተርከው።

ማን ነበርክ? ከሚለው ይልቅ ማን ለመሆን ትፈልጋለህ? የሚለው የአንድነታቸው መሠረት ነው። የነገውን በጋራ ከተጋሩት የትናንቱን በመተሳሰብ መቀበል አይቸግራቸውም። በነገው ላይ ከተግባቡ በትናንቱ ላይ መስማማት አይፈትናቸውም። በረቷ የክርስቶስ በረት፣ እረኞቹ የክርስቶስ እረኞች፣ ጠቢባኑ የክርስቶስ ጠቢባን፣ መላእክትም የክርስቶስ መላእክት፣ ቀኗም የክርስቶስ የልደት ቀን፣ ዘመኑም የክርስቶስ ዘመን ሆነዋል። ያኛው የጥንቱ የብሉይ፣ ይሄኛው ደግሞ አዲሱ የሐዲስ ኪዳንና ታሪክ ሆነ። የጥንቱ በአዲሱ ምክንያት ታወቀ፤ የቀድሞው በአሁኑ ምክንያት ከበረ፤ የትናንቱ በዛሬው ምክንያት ታደሰ።

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ መለያየት የመጣው እንዲሁ አይደለም። ሆን ተብሎ ተሠርቶበት ነው። ክፋው ሆን ብሎ የልዩነትን ዘር ዘርቶ፣ የልዩነትን እሾህ አብቅሎ፣ የጠላትነትን ፍሬ እንዲያፈራ አድርጓል። ልዩነቱም ከመለያየት አልፎ ወደ ጠላትነት እንዲሻገር ሠርቷል። ጠላትነቱም አዳምን ከገነት አፈናቅሏል። አቤልን በቃየል አስገድሏል። በምድር እሾህና አሜከላ አብቅሏል። የጥፋት ውኃን እልቂት አስከትሏል። ጦርነትና ግጭትን አትርፏል። በዚህ ሁሉ ጠላት እንጂ ማንም አልተጠቀመም።

አንድነትም የመጣው በብዙ ልፋትና መሥዋዕትነት እንጂ እንዲሁ በቀላሉ አይደለም። ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ፣ ከልደት እስከ ስቅለት፣ ከበረት እስከ ዕርገት ዋጋ ተከፍሎበት ነው። ዛሬ የምናከብረው ልደት ያስፈለገውም መለያየት ብቻ ሳይሆን በመካከላቸው ጠላትነት እንዲሰፍን የተሠራባቸውን ወገኖች አንድ ለማድረግ ነው። ይህን የወገኖች አንድነት ፍለጋ በሰማይ ያሉት ወደ ታች ወርደዋል። እነርሱ ይሄንን እንደ ውርደትም እንደ ውለታም አልቆጠሩትም። በምሥራቅ ያሉት ወደ ምዕራብ ሲመጡ እንደ ድካም አላዩትም። ሁሉም ሰጥቷል፤ ሁሉም ጎድሎበታል። ሁሉም አግኝቷል፤ ሁሉም ትቷል። ሁሉም ከፍ ብሏል፤ ሁሉም ዝቅ ብሏል። ሁሉንም በሁሉ ሆኖ የሞላውና ያሟላው የተወለደው ከሰማይ ወርዶ በግርግም የተወለደው ክርስቶስ ነው።

ኢትዮጵያውያን የነገዋን ኢትዮጵያ የተሻለች ለማድረግ ከዚህ የልደት ታሪክ ብዙ ትምህርት ብንወስድ ይጠቅመናል። ዛሬ እዚህም እዚያም የምናየው የመለያየትና የመጠፋፋት አባዜ የባህሪያችን አይደለም። የማናችንም ማንነት መገለጫ አይደለም። ይህ የተዘራብን ክፉ ዘር ውጤት ነው። የውስጥ የውጭ ባዳ አንድ ሆነው የዘሩብን ዘር ውጤት ነው። ያለንበት ዘመን ዘሩ የተዘራበት ጊዜ አይደለም።

አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ይመስላቸዋል። ይህ ወቅት ዘሩ ጎምርቶ አፍርቶ ያየንበት ወቅት ነው። የታኅሣሥ መከር የሚዘራው በሐምሌ ነው። አንዳንድ ሰዎች ትናንትኮ እንዲህ ያለ ነገር አልነበረም ይላሉ። ዘሩ ከምድር በታች በመብቀል ላይ ስለነበረ አላስተዋልነውም። ሰርዶው አድጎ እግር መጥለፍ ስላልጀመረ አልተቸገርንም። እንክርዳዱ በዝቶ ራስ ማዞር ስላልጀመረ አልታወቀንም። እሾሁ አፍጥጦ ሰውነት መቧጠጥ ስላልጀመረ አልለየነውም። አሜኬላው በርክቶ እግር ለማድማት ስላልደረሰ ከቁብ አልቆጠርነውም። እንጂ ክፉው ዘርስ እየበቀለ ነበረ።

ወደ አዲሱ ዘመን፣ ወደ አዲሱ ብርሃን እንምጣ። ወደ አዲሱ ማንነት፣ ወደ አዲሱ ምእራፍ እንምጣ። አዲስ የጋራ ታሪክ ስንሠራ፤ የትናንቱ ታሪክ ያግባባናል። አዲስ መንገድ ስንጀምር የትናንቱ መንገድ አያጣላንም። አዲስ ዘመን ስንወጥን ያለፈው ዘመን አያለያየንም። አዲስ ዓላማ አንግበን ከተነሣን፣ የትናንቱ ዓላማ አያጨቃጭቀንም።

የአንዳችን ጠላት ሆኖ የሌላችን ወዳጅ ሊሆን የሚችል የለም። አንዳችን ታምመን ሌላችን ጤነኛ መሆን አይታሰብም። አንዳችን ጎድሎብን ሌላችን ሙሉ ልንሆን አንችልም። አንዳችን ተከፍተን ሌላችን ደስተኛነትን ማጣጣም አንችልም። የሰው ልጅ ከገነት መውጣቱ የመላእክትን ደስታ ነጥቋል። የእንስሳትን ምቾት አጉድሏል። የምድርንና የሰማይን ክብር ገፍፏል። ገነትን ያለ ሰው አስቀርቷል። የሰው ልጅ ጠላት የሆነው ዲያብሎስ ለጊዜው በክፋቱ ስኬት በደስታ ፈንጥዟል። የሁላችንም ደስታ ሙሉ መሆን የቻለው ለሁሉም የሚሆነው ክርስቶስ ሲወለድ ነው።

የጠላታችን ዓላማ አንዳችንን ጠቅሞ ሌላችንን መጉዳት ሳይሆን ሁላችንንም ማጥፋት ነው። ዲያብሎስ መጀመሪያ አዳምና ሔዋንን አካሰሰ። ቀጥሎ ሰውን ከፈጣሪው ነጣጠለ። ከዚያ ሰውን ከመኖሪያው ከገነት አፈናቀለ። እሾህና አሜከላ እንዲበቅል አድርጎ ሰውንና ምድርን አቆራረጠ። ቃየልን በአቤል ላይ አስነስቶ አስገደለው። ጠላታችን አንዱን ሕዝብ ከሌላው በማጋጨት አይቆምም፤ አንዱንም ሕዝብ እርስ በርሱም ያባላዋል። ክልልን ከክልል፣ ዞንን ከዞን፣ ወረዳን ከወረዳ፣ ጎጥን ከጎጥ፣ ቤተሰብን ከቤተሰብ፣ ባልን ከሚስት፣ ልጆችን ከወላጆች እያባላ ዓለምን ሁሉ የግጭትና የጠብ አውድማ ማድረግ ነው ምኞቱ።

ስለዚህ ቆም ብለን እናስብ። መንገዱ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የሚበጅ፣ ለሁላችንም በቅቶ የሚተርፍ፣ አዲስ ማንነትን ይዘን እንደገና መወለድ ነው። ታሪክ ማለፉ አይቀርም። ታሪክ መለወጡም አይቀርም። ቁም ነገሩ የታሪክ ተከሳሽና ተወቃሽ ወይንስ ተዘካሪና ተሞጋሽ እንሆናለን? የሚለው ነው። ከሩቅ መጥተው መሲሑን እንደተገናኙት ጠቢባን ሰብአ ሰገል ታሪክ እንሠራለን ወይስ እንደ ሄሮድስ ታሪክን ለማጥፋት በንጹሐን ላይ ሰይፍ እናነሣለን? የሚለው ነው። እንደ ቅዱሳን መላእክቱ ለአዲስ ታሪክ አዲስ የምሥራች እናበሥራለን ወይስ እንደ ዘመኑ የአይሁድ ልሂቃን ባለፈው ታሪክ ላይ ተተክለን የቀረበልንን ዕድል በንቀት እንገፋለን? የሚለው ነው። የእነዚህን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ማግኘት፣ ኢትዮጵያ በአዲስ ልደት መንገድ እየተጓዘች የጌታችንንና የመድኃኒታችንን ልደት እንድታከብር ባለ በቂ ምክንያት ያደርጋታል።

መልካም የልደት በዓል ይሁንልን!

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!

ታህሳስ 28፣ 2015 ዓ.ም.

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚተጉትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# ከጠባሳው በስተጀርባ ...

መልካምሥራ አፈወርቅ

የኑሮዋን ውጣውረድ የፊቷ ገጽታ ያሳብቃል ። ተጎሳቁላለች፣ ጥርሶቿ ወላልቀዋል፣ እጇቿ በትኩስ ጠባሳዎች ተሸፍነዋል። ደጋግማ ትተክዛለች፣ አንገቷን ደፍታ፣ አገጭዋን ደግፋ አርቃ ታስባለች። ወዲያው በዓይኖቿ ዕንባ ግጥም ይላል። ይህ እውነት የየዕለት ልምዷ ነው። ለእሷ ዕንባና ችግር ብርቅ ሆኖ አያውቅም።ሁለቱም በአንድ ሆነው ከእሷ ኖረዋል።

ሁሌም ውስጧን ለመደበቅ ፣ ከራሷ ጋር ትግል እንደያዘች ነው ። ኑሮዋን ታግላ ህይወትን እያሸነፈች ዛሬ ላይ ብትደርስም ስለነገው አታውቅም። ዘወትር አብሯት ያለው ህመም እንደጥላ ይከተላታል ። በዚህ ምክንያት እንደሌሎች ሰርታ ፣ሮጣ ለማደር ዕንቅፋቷ በዝቷል።

### ቅድመ- ታሪክ ልጅነት

የእህታቸውን መርዶ በድንገት የሰሙት ወይዘሮ ‹‹እዬዬ›› እያሉ ነው። ታናሽ እህታቸው ስለመታመማቸው አስቀድመው ሰምተዋል። እንዲህ በአጭር ጊዜ ሞታቸውን እንደሚረዱ ግን ጠርጥረው አያውቁም ። የአዲስ አበባዋ ሴት አሁን ለሀዘኑ ወደ ቡታጅራ እየሄዱ ነው። ጥቂት ጎረቤቶቻቸው ተከትለዋቸዋል። ከቀብሩ መልስ ሀዘናቸውን በቤታቸው፣ በዕድራቸው ይወጣሉ።

ወይዘሮዋ ውስጣቸው እንዳዘነ ዓይናቸው እንዳነባ ቡታጅራ ደርሰው ከመኪና ወረዱ። ከሀዘኑ ቤት ደርሰው የሟች እህታቸውን ቤተሰቦች በለቅሶ ተቀላቀሉ። ታናሽ እህታቸው በመኖሪያ ዕድሜዋ ልጆቿን በትና መሞቷ ልባቸውን ሰብሮታል።ከሁሉም ግን ከተወለደች ገና ሶስት ወር ያልደፈነችው ጨቅላ ነገር እያሳሰባቸው ነው። ሟች ከማረፏ አስቀድሞ ስለትንሽዋ ልጅ አደራ ብላቸዋለች። እህት ይህን ቃል ፈጽሞ አልረሱም፣አልዘነጉም።

ጨቅላዋ ጡት በወጉ ሳትጠግብ፣ ወዝና ጠረን ሳትለይ እናቷን ሞት ነጥቆባታል። ወይዘሮዋ ህጻንዋን እያዩ አነቡ። ጥቂት ቆይተው ግን በዓይምሯቸው ሲመላለስ የቆየውን ሀሳብ ሊያወጡት ግድ አላቸው። የሟችን ባለቤት ጠጋ ብለው ያሰቡትን ዕውነት አማከሯቸው፤፤

ህጻኗ እናቷን በሞት አጥታለች፣ ከእንግዲህ የእሷ ህይወት አስቸጋሪና ፈታኝ ሊሆን ነው። እናም ካለችበት የተሻለ ሌላ ህይወት ሊኖራት ያስፈልጋል። ይህን ሀላፊነት የመወጣቱ ግዴታ ደግሞ የእሳቸው ይሆናል። አስቀድሞ ጆሯቸው ቃል ሰምቷል። የሙት አደራ አለባቸው።

አባወራው የሚስታቸውን እህት ሀሳብ አልተቃወሙም ።ጨቅላ ልጃቸውን በድንገት አሳልፎ መስጠቱ ቢከብዳቸውም ከእሳቸው ይልቅ አክስት ወስደው ቢያሳድጓት እንደሚሻል አመኑ ። አባት ዕንባ እያነቃቸው፣ ከሲቃና አደራ ጋር ትንሽዋን ልጅ ለሚስታቸው ታላቅ እህት በአደራ አስረከቡ።

### አዲስ አበባ

አሁን ወይዘሮዋ ትንሽዋን የእህታቸውን ልጅ በአደራ ተረክበው አዲስ አበባ ተመልሰዋል። ከእጃቸው ያለችው ህጻን ከሌሎች ሁሉ ትለያለች።እሷ በወጉ ጡት አላገኘችም። ከእናቷ ጉያ ተወሽቃ ፍቅርን፣ሙቀትን አላየችም። ደጓ ወይዘሮ ከልጆቻቸው ሳይለ ዩ፣ እንደራሳቸው ፍሬ እያሳደጉ እየተንከባከቧት ነው። ትንሽዋ ልጅ አድጋለች፣ ተመችቷታል።

ውሎ አድሮ አሳደጊ አክስቷ ለእህታቸው ልጅ ስም አወጡ ። ‹‹እጅግ አየሁ›› ሲሉ ሰየሟት።እጅግ አየሁ ከአክስቷ ቤተሰቦች ጋር በእኩል አደገች። አንዳች መድልኦ ሳያገኛት፣ በደልና ዱላ ሳይርፍባት ልጅነቷን ገፋች ። ሞት ስለነጠቃት ስለ እናቷ ማንነት አታውቅም። በአክስቷ የተከፈለላትን ዋጋና ፍቅር የተረዳችው ዕድሜዋ ከፍ ሲል አቅሟ ሲበረታ ነበር።

የእጅግአየሁ አሳዳጊ አክስት ኑሯቸው እምብዛም የሚባል ነው። ከእጅ ወደአፍ በሆነው ህይወት ኑሮን ለመግፋት፣ ቤተሰብን ለማኖር እንጀራ ጋግረው ይሸጣሉ። ለእሳቸው እንጀራን ሸጦ እንጀራ ለማግኘት ኑሮ አልጋ በአልጋ አይደለም። አህልና ማገዶን መግዛት፣ ያስፈልጋል፣ ለዚህም አቅምና ጉልበት ይጠይቃል ። እጅጋየሁን ጨምሮ ሌሎች የእናታቸውን ፍላጎት ሊሞሉ ሲሮጡ ይውላሉ።

ልጆቹ ለእንጀራው ማብሰያ የአቅማቸውን ማድረግ ግዴታቸው ነው። ከየመንገዱ ካርቶን፣ ቅጠልና እንጨት ይለቅማሉ። ያገኙትን ይዘውም ለእናታቸው ይሰጣሉ ።። ህይወት በእነ እጅጋየሁ ቤት እንዲህ ሆኖ ዘልቋል። የእጅግአየሁ አክስት መልካም ሴት ናቸው። ልጆቻቸውን በፍቅር ያሳድጋሉ። እሷንም ቢሆን ከምትሻው ሁሉ ነጥለዋት አያውቁም።፡ የአቅማቸውን ያደርጋሉ ፣ የቻሉትን ያሟላሉ።

እጅግአየሁ ከአክስቷ አንዳች ፍቅር ሳትነፈግ በሰላም በጤና አደገች። ልጅነቷን አልፋ ከወጣትነት ከአፍላነት ዕድሜ ደረሰች።

አሳዳጊ አክስቷ የአንድ ልጅ እናት ናቸው። ልጃቸውን ጨምሮ አጅግ አየሁን አስተምሮ ለወግ ለማብቃት ሲጥሩ ኖረዋል። ህይወት ከብዶ እጃቸው ቢያጥርም ልጆቹን ለማስተማር ወደ ኋላ አላሉም። ካላቸው እየቆጠቡ ሁለቱንም ሊያስተምሩ ሞክረዋል። እንደሳቸው ልፋት ባይሆንም እጅግአየሁ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምራለች።

እጅግአየሁን በቻሉት አቅም ያሳደጉት አክስት ጥረታቸው ተሳክቷል።አሁን ከጀርባቸው ሆኖ የሚያለቅስ፣ዳቦ የሚል ህጻን የለም። እንደትናንቱ ለወተት ብለው አያስቡም። ሁሉም ቤት ያፈራውን ቀምሶ ያድራል። ዛሬ ላይ የሚያሳስባቸው ቢኖር የእህታቸው ልጅ የእጅግአየሁ ጤና ብቻ ነው።

ልጅቷ ካደገች በኋላ የታየባት ምልክት እሳቸውን ጨምሮ መላ ቤተሰቡን አሳስቧል። ደርሶ በድንገት ይጥላታል። ራሷን አውቃ ስትነቃ ያለችበትን አትለይም። ለችግሩ መላ ብዙ ተሞክሯል ። ቆይቶ ግን የእጅግ አየሁ ችግር የሚጥል በሽታ መሆኑ ታወቀ።

እጅግአየሁ ከዚህ ችግር ጋር ዓመታትን ዘለቀች። ብዙዎች ህመሙ ሲነሳባት እንደሚጥላት ያውቃሉ። እሷ በሽታውን እንደ ባህሪው መያዝ ይቸግራታል ፣ ይህ እውነት ለህይወቷ እንቅፋት መሆኑን ጭምር ታውቃለች። እንዲያም ሆኖ ከራሷ እየታገለች፣ ከመድሀኒቱ እየወሰደች ጊዚያትን ቆጥራለች ።

### ከጊዚያት በኋላ

አሁን እጅግ አየሁ ወጣት ቆንጆ ሆናለች፤፤ ይህን እድሜ በወጉ ካልያዙት ፈተናው ይበዛል ። በተለይ ሴት ልጅ ማንነቷን አውቃ ራሷን ካልገዛች መሰናክሏ ይበረክታል ፣ወጥመዷ ይሰፋል ። በዚህ ወቅት ዓይኖች ሁሉ ከውበት ላይ ያፈጣሉ። በየምክንያት ሰበቡ የሚያደንቁ ፣ ወደድን፣ አፈቀርን የሚሉ ጥቂት አይሆኑም። ወጣትነት ሀይል ነው። ዓለምን መዝነው ፍቅርን ያዩበታል። ውበትን አድንቀው በራስ ይዋቡበታል።

አንዳንዴ ግን ይህ ዕድሜ ባልሆነ መንገድ ሊሰድ፣ ሊያሳስት ይችላል ። ይህኔ አቅጣጨን አይቶ የሚመለስ፣ የሚመክር ልባም ከሌለ ውጤቱ ይከፋል ። አሁን እጅግ አየሁና ወጣትነት ተዋውቀዋል ። ለራሷ ጊዜና ክብር መስጠት የያዘችው ወጣት እርምጃዋ ሳይቀር ተለይቷል፤ ሀሳብ ዕቅዷም መጥቋል።

ትምህርቷ ከስምንተኛ በላይ አልገፋም ። ህመሟ ጭምር ሰበብ ሆኖ ከቤት መዋል ይዘለች። ይህ ጊዜ በትምህርት የሚውለውን ድርሻ ለእሷ ብቻ ሰጥቷል ። አሁን ወጣቷ ወጣ ገባ አብዝታለች፣ ባልንጀሮች ይዛለች፣ ቀጠሮዋ በዝቷል፣ ውበት መልኳ አይን ስቧል።

### አንድ ቀን

እጅግአየሁ ከቀናት በአንዱ ከዘመድ ቤት ጠበል ተጠርታ ሄደች ። ከቤቱ ስትገባ ብዙ ዓይኖች ተከተሏት። አጋጣሚ ሆኖ ከአንድ ወጣት አጠገብ አረፍ ብላ ጨዋታ ያዘች። ወጣቱና እሷ እህል ውሀ እያሉ ጨዋታቸው ደራ፣ ስለማንነቷ ጠየቃት፣ ነገረችው፣ ስለእሱም እንዲያወራት ፈለገች፡ አልደበቃትም። ትዳር መያዝ ልጆች መውለድ እንደሚሻ አሳወቃት።

እጅግአየሁ የወጣቱ ጨዋታ ልቧን ገዛው፣ ስለ ትዳር ያነሳውን ቁም ነገር በዋዛ መተው አልፈለገችም። ሁለቱም የልባቸውን እያነሱ የፍለጎታቸውን መከሩ።ቀልባቸው ተስማማ፣ ውስጣቸው ተፈላለገ። ዳግም ሊገናኙ ወስነው በቀጠሮ ተለያዩ።

ሁለቱ ደጋግመው ተገናኙ። ቅርበታቸው ፍቅር ሆኖ ሀሳብ ተለወጠ። ልባቸው ቁምነገር ቢያስብ በአንድ ጎጆ ሊኖሩ ፣ ያሰቡትን ሊሆኑ ተስማሙ። ሀሳቡ ጊዜ አልፈጀም። ቤት ጎጆ ማለቱ ቀጠለ። እጅግ አየሁ ራሷን ችላ ትዳር መያዟ አክስቷን አላስከፋም። የልቧ ይሆንላት ዘንድ ምኞታቸው በምርቃት ነው።

እጅግአየሁ ከህመሟ አልዳነችም። አልፎ አልፎ የሚጥላት በሽታ ራሷን ያስታታል።አንዳንዴ ከጉድጓድ ከእሳቱ ይጥላታል፣ ከወደቀችበት ስትነቃ አካሏ በእሳት ተቃጥሎ ፣ ጥርሷ ወልቆ፣ ተሸርፎ ራሷን በጉዳት ታገኘዋለች ። እንዴት ብላ አትጠይቅም ። ምክንያቱን ታውቀዋለች ፤እንዲህ የሆነችው በሚጥል በሽታዋ ነው። ለቀናት ቁስሏን አስታማ ጥቂት ታገግማለች። ዘወትር የጠባሳዋን አሻራ እያየች አንገቷን መድፋት መተከዝ ልምዷ ነው።

፡ ሌላ ቀን ደግሞ ከአስፓልት ዳር፣ ከመኪኖች ጎማ ስር ወድቃ ተጎትታ መውጣቷን ይነገራታል ። ይህኔ ውስጧ ዳግም ይከፋል፤ ዕንባዋ በላይ በላይ ይፈሳል። ዕድሏን አብዝታ ታማርራለች፣ ራሷን ደጋግማ ትረግማለች ። ምርጫ የላትም ። የነገ ዕጣ ፈንታዋን እያሰበች በሀዘን ፣ በትካዜ ትከርማለች።

እጅግአየሁ ‹‹ትዳሬ፣ ቤቴ›› እያለች ነው። ጎጇዋን የሚያደምቅላት፣ ህይወቷን የሚያሰምርላት ልጅ ከወለደች ወዲህ ደስታዋ ጨምሯል። ልጇን እያሳደገች ህይወቷን ልታሸንፍ ትሮጣለች ።፡ የነገን ተስፋ ይታያታል፣ ህይወቷ ባይቀናም ኑሮዋ ባይሞላም በልጇ ስጦታ ጎዶሎዋ ተደፍኗል ፣ጨለማዋ በርቷል ።

### ሶስቱ ጉልቻ

የእጅግ አየሁ ትዳር ሰላም ከራቀው ቆይቷል ። ጠዋት ማታ በጭቅጭቅ ውሎ የሚያደርው ጎጆ ሰላም ይሉትን አያውቅም። ባለቤቷ ከእሷ ይልቅ ትኩረቱ ለልጁ ብቻ ሆኗል። የምትለውን አይሰማም ፣ የሚሰራውን አታውቅም። ውሎ ሲገባ በእጁ ያንጠለጠለውን ይወረውርላታል። ከእሱ የሚመጣው ቋጠሮ በቅቷት አያውቅም ። ጎጇዋን ለመሙላት፣ ኑሮዋን ለመግፋት ትሮጣለች።

ሁሌም ከህመም እየታገለች ፣ የልጇን ሆድ ልትሞላ ትታገላለች፤ የራሷን ህይወት ልታቀና አብዝታ ትጥራለች። መርካቶ ገብታ በኪሎ ሀያብር የምትገዛውን ወረቀት በልኩ እየቆረጠች፣ እያሸገች ለሚፈልጉት ታደርሳለች። ገዢዎቿ የእሷን ተቀብለው ለለውዝ፣ ለቆሎና ለሌላም ጥቅም ያውሉታል።የሚከፍሏትን ሳንቲም ይዛ ለጎጇዋ ትደርሳለች። ሲነጋ ሌላ ቀን ነው። እጅግ አየሁ እንደትናቱ ዛሬ እንዳይጎድል ጉልበቷ ይበረታል።

### ሁለተኛው ልጅ

እጅግአየሁ የመጀመሪያ ልጇ እያደገ ነው። ስምንተኛ ዓመቱን ባከበረ ማግስት የወለደችው ልጅ ደግሞ ከእሷ ብዙ ይሻል። ህይወቷ ዛሬም አልቀናም።ከችግር ፣ ከድህነት እየታገለች በልታ ለማደር ትተጋለች።

ለህመሟ አማኑኤል ሆስፒታል ክትትል አላት ። በየጊዜው የምትወስደው መድሀኒት ደግሞ በቂ ምግብና እረፍት ይፈልጋል። እሷ ከጎጆዋ ውሎ የሚያድር ቁራሽ የላትም ። ለዚህ ያልታደለችው ሴት የዛሬን ቀምሳ ለነገው ለመድረስ ልፋቷ የበዛ ፣ ሸክሟ የከበደ ነው።

### በዕንቅርት ላይ...

እጅግአየሁ አሳድገው፣ ለወግ ያበቋት አክስቷ ዛሬም ከጎኗ አልራቁም። ሁሌም በምክር ያበረቷታል፣ ‹‹አይዞሽ ፣አለሁልሽ›› ይሏታል።አክስቷ በቅርብ ጊዜ ያደረባቸው ህመም ቤት እያዋላቸው ነው ። አጠገባቸው ያለችው እጅግአየሁ ጊዜ ወስዳ ማስታመም አልሆነላትም። አልጋ ባይዙም ህመማቸው ስጋት ሆኖ ያሳስባቸዋል።

ለእጅግአየሁ እሳቸው ካሉ ሸክም ሁሉ ይቀላል። ከእሳት ቀርባ ምግብ እንድትሰራ፣ ቡና እንድታፈላ አይፈቅዱም። የጎደለውን ሞልተው ከእሳት ከምድጃው ውለው ፣ የልቧን ይሞላሉ፡

አንድ ቀን ግን ይህ ሁሉ ሀሳብ ፣ ክብርና ፍቅር እስከ ወዲያኛው መቅረቱ አርግጥ ሆነ። አክስቷ ከተቀመጡበት ወንበር ሳይነሱ በሞት አሸለቡ። ድንገቴው ሞታቸው የእጅግአየሁን ኑሮ ‹‹በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› አደረገው። ህይወት ይበልጥ ከበዳት፣ የኑሮ ጫናን ለብቻዋ ልትጋፈጥ ፣ ግድ አላት።

ከባለቤቷ ጋር አሁንም ሰላም አልወረደም ። እንደውም አንዳንዴ በክፉ ንግግሩ ሆድ ያስብሳታል ሁሌም ‹‹እኔ



የምኖረው ለልጆቼ እንጂ ለአንቺ አይደለም›› ይሉትን ቃል ለምዳዋለች። ይህን ስትሰማ ከእንግዲህ ለእሷ የሚኖር ፣ ስለእሷ የሚያስብ የሚጨነቅ እንደሌለ ሆኖ ይሰማታል።

እጅግአየሁ አሁን እሷን ወክሎ ከእሳት ከምድጃው የሚጋፈጥ የልብ ሰው የላትም። ልክ ከፊቷ እንዳሉት ችግሮች ሁሉ አጋጣሚዎችን በራሷ አቅምና ሀሳብ መወጣት ግድ ብሏታል። ሁለት ህጻናት ልጇቿ ሀላፊነቷ ናቸው። እነሱን መያዝና መንከባከብ፣ ማብላትና ማስተማር አይቀሬ ነው ።ወይዘሮዋ አሁን ልደታ አካባቢ በተከፈተው የምገባ ማዕከል ተጠቃሚ ሆናለች፡፤ይህን ያወቀው ባለቤቷ ድርጊቷን ከልመና ቆጥሮ እንድትተው አስጠንቅቋታል።

እጅግ አየሁና ትልቁ ልጇ በቀን የሚያገኙትን የአንድ እንጀራ በወጥ በረከት ፈጽሞ ማለፍ አይፈልጉም። አንዳንዴ ከእንጀራ የዘለለ ምርጫ አላቸው። የተሰጣቸውን በምስጋና አጎንብሰው ይቀበላሉ። ልጇ ሰአት ያለፈ በመሰለው ጊዜ እናቱን እየወተወተ ያስታውሳታል።

እጅግአየሁ በየቀኑ ከስፍራው ደርሳ የተሰጣትን ከልጇ ትካፈላለች። እንዲህ መሆኑ በባዶ ሆድ መድሀኒት ለምትወስደው ህመምተኛ ታላቅ መፍትሄ ሆኗል። አሁን ቀምሶ ፣ ተቃምሶ ለማደር እሳትና የጋለ ምድጃን ብቻ አትጠብቅም። ከተዘጋጀው ለእሷ ቆርሳ፣ ለልጇም አጉርሳ በምስጋና ቤቷ ትገባለች።

ዛሬም እጅግአየሁ ህይወትን ለመግፋት፣ ኑሮን ታግሎ ለማሸነፍ እየታገለች ነው። የባለቤቷ በሀሳብ አለመደገፍ በአንድ እጅ ማጨብጨብ ቢሆንባትም ከትጋቷ ጋር ልጆቿን ማሳደግ ራሷን ማሳደር ቀጥላለች።እሷ ከጠባሳዋ ጀርባ ህይወትን አርቃ፣ታያለች።ካልደነው፣ ካልሻረው ቁስሏ ባሻገር ነገ ሙሉ ተስፋዋ ነው። ፈገግታና ምስጋናም የሁልጊዜ ልማዷ ።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከመምህርነት እስከ ሚሊየነርነት

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

የተወለዱት ደሴ ከተማ ዳውዶ የሚባል ሰፈር ነው። አባታቸው ፖሊስ ነበሩ። ሁለት እህቶችና አንድ ወንድም አላቸው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታውን ጦሳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍልን ደግሞ በቅዳሜ ገበያ ትምህርት ቤት እንዲሁም ዘጠነኛ ክፍልን በሆጤ ትምህርት ቤት ነው የተማሩት። ከ10ኛ እስከ 12ኛ ያለውን ደግሞ በወይዘሮ ስህን ትህምርት ቤት በቮኬሽናል ትምህርት ዘርፍ ተከታትለዋል።

አባታቸው በልጅነታቸው ስለሞቱ የቤተሰቡ መተዳደርያ 50 ብር ብቻ ነበር። እድሜቸው ከፍ ሲል የቤተሰቡን ኑሮ ለመደጎምና ለደብተር መግዣ በሚል እንቁላል መነገድ ውስጥ ገቡ፤ የቀን ሥራም ሞካክረዋል።

በ1977 ዓ.ም ብሄራዊ ውትድርናን ተቀላቀሉ፤ ያኔ ገና 17 ዓመታቸው ነበር። የሁለት ዓመት ግዳጃቸውን ጨርሰው ቢመለሱም፣ ነገሮች እንዳሠቡት አልሆንላቸው አሉ። ድጋሚ ወደ ግንባር እንዲሄዱ ጥሪ ተደረገላቸው። እርሳቸው ግን ያንን ማድረግ አልፈለጉም። አካባቢያቸውን ለቀው ወደ አዲስ አበባ ሄዱ። በዚያም ያገኙትን ሁሉ መሥራት ውስጥ ገቡ፤ በአንድ ብር ከ95 ሳንቲምም የቀን ሥራ ሰርተዋል። የዛሬው የስኬት እንግዳችን አቶ መኮንን ብርሃኑ።

በ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ ተደርጎ ነገሮች ሲረጋጉ ወደ ቤተሰባቸው የተመለሱት አቶ መኮንን፣ በደሴ የመምህራን ማሰልጠኛ ገብተው የመምህርነት ስልጠና ተከታትለው በ1984 ዓ.ም በሰርተፍኬት ተመርቀዋል። ከዚያም በ443 ወርሃዊ ደመወዝ በመምህርነት ተቀጠረው ደሴ ዙሪያ ‹‹ግልብጤ›› በሚባል ትምህርት ቤት ተመደቡ።

ዳሩ ግን ትምህርት ቤቱ የፈረሰ በመሆኑና ተማሪም ስላልነበረው 1984 እና 1985 ዓ.ም እንዲሁ ትምህርት ቤት በመመላለስ አሳለፉ። በወቅቱ ብዙ ትርፍ ጊዜ የነበራቸው አቶ መኮንን እቁብ ገብተው ባገኙት 800 ብር ከደሴ እንቁላል ገዝተው ወደ አዲስ አበባ እያመላለሱ መነገድ ጀመሩ። ይህም ብዙም አትራፊ አልሆንላቸው አለ። ከዚያም ደሴ ከተማ ማርዮን በሚባል ጣሊያናዊ ጣውላ አምራች ቤት መስራት ጀመሩ። ቀጥሎም በዚሁ ጣውላ ቤት ጣውላ እያሰነጠቁ ለአካባባቢው ሰው ቡፌ፣ ቡፌ ቁምሳጥን፣ ረከቦትና የመሳሰሉትን በራሳቸው መስራት ውስጥ ገቡ።

ይህ ሁሉ ሲሆን መምህርነቱ እንዳለ ነው፤ በ1988 ዓ.ም በየወሩ 100 ብር እቁብ እየጣሉ 1000 ብር እቁብ አገኙ። በዚህን ጊዜ ጓደኞቻቸውን ጥድ ገበያ የሚባል አካባቢ ወፍጮ እንትከል ብለው አማከሯቸው፤ ዳሩ ግን ሃሳቡን ሳይቀበሏቸው ቀሩ። እሳቸው ግን አሁንም ተስፋ አልቆረጡም።

በ1990 ዓ.ም ከደሴ በዝውውር ኮምቦልቻ ዙሪያ ‹‹ንባራ ሀገር›› የሚባል ትምህርት ቤት ተመድበው መሥራት ጀመሩ። በቮኬሽናል ትምህርታቸው እንጨት ሥራ ተምረው ስለነበር እንጨት ስራውን አጧጧፉት። ቦርከናን በእግር እየተሻገሩ ግማሽ ቀን አስተምረው ግማሹን ቀን እንጨት ሥራውን ተያያዙት፤ ገበያው ደራ። በ1994 ዓ.ም ትልቅ ማሽን ያለው ቤት በ1000 ብር ተከራይተው ስራውን አስፋፉት፤ ሰው ቀጥሮ መስራት ተጀመረ።

ትዳር መስርተው 1995 ዓ.ም ልዑል የሚባል የበኸር ልጅ አገኙ። ለስራቸው ሲሉ ገጠር ይመላለሱ የነበሩት አቶ መኮንን፣ እየደከማቸው ይቸገሩናም ለመጓጓዣ የሚሆናቸውን ነጭ ሰጋር ፈረስ በ400 ብር ይገዛሉ። ፈረሱን ከረምት ላይ ቀለቡ ሲቸገራቸው ሸጠውት በመስከረም ሌላ ፈረስ ገዙ።

ህዳር 1996 ዓ.ም መምህራን ሙሉ ቀን መሥራት አለባችሁ የሚል አቅጣጫ ወረደ። ይህ ከሥራቸው ጋር አልስማማ አላቸው። በመጨረሻም ቤተሰባቸውን አሳምነው መምህርነቱን ትተው የእንጨት ሥራቸውን አጥብቀው ያዙት።

ጥር 1996 ዓ.ም የዶሮ ጫጩትና የአንድ ቀን የዶሮ ማሳደሪያ አስፈልጎት የከተማው ግብርና ጨረታ አወጣ። እሳቸውም ብዙ ሂደቶችን አልፈው በ57ሺ ብር የጨረታ ሥራ ሠሩ። ይህን እየሰሩ ሚያዚያ ወር ላይ ደግሞ ሌላ ስራ መጣ፤ የንብ ቀፎ የሚሠራ ድርጅት ተፈልጎ አካባቢው ያሉ የእንጨት ባለሙያዎች እንዲሰበሰቡ ይደረጋል።



**አቶ መኮንን ብርሃኑ**

ስራም ይሰጣቸዋል። በዚህ ጊዜ እርሳቸው ሥራቸውን በፍጥነት አጠናቀው አስረከቡ፤ ጥሩ ገንዘብም አገኙበት።

ይህን ስራቸውን ሚዲያዎችም ሰፊ ሽፋን ሰጡት፤ መረጃው ተናፈሰ። ይህን የሰሙ ሰዎች ከወረዒሉ የሽመና መሳሪያ ሥራልን የሚል ጥያቄ አቀረቡላቸው፤ ይህንንም በመስራት ጥሩ ገቢ አገኙ። ዘመናዊ ማረሻ በጨረታ አሸንፈው ሰርተዋል። ይህ ሁሉ ሂደት የገንዘብ አቅማቸው እንዲፈረጥም አረጋቸው።

1997 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ሄደው ቫት ተመዘገቡ። አዲስ ዘመን ጋዜጣን ማየት ጀመሩ። አማራ ክልል 1000 ጥቁር ሰሌዳ የሚሰራ ይፈልግ ነበር። በዚህ ጨረታ ተሳትፈው ጨረታውን ቢያሸንፉም፣ በተለያዩ ምክንያቶች ወድቅ ተደረገባቸው፤ ይሁንና ግን ከዚህም የሕይወት ዘመን ትምህርት እንደወሰዱበት አቶ መኮንን ይናገራሉ።

1997 ዓ.ም የሸዋ ሮቢት ማረሚያ ቤት ለቁም ሳጥንና ጠረጴዛ ስራ ያወጣውን ጨረታም በ100ሺ ብር አሸነፉ። ሥራውን በተባለው መሠረት ቢሰሩም፣ በተባለው ልክ ተጠቃሚ መሆን ግን አልቻሉም፤ 20ሺ ብር ሳይከፈላቸው ቀረ።

በአንድ ወቅት ደግሞ ጉምሩክ የመኪና ሽያጭ ለማድረግ ጨረታ ያወጣል፤ እሳቸውም ጨረታውን አሸንፈው ለስራቸው የሚያግዝ መኪና በ25ሺ ብር ገዙ፤ ሥራውም ይበልጥ አደገ። በ1998 ዓ.ም የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ስር የነበረውን 30 አልጋ ያለውን ብሄራዊ ሆቴል በ1ሺ800 ብር ወርሃዊ ኪራይ መነሻ ጨረታ አወጣ። በብዙ ውጣ ውድ ጨረታውን በ2000 ብር አሸንፈው በመጀመሪያ ልጃቸው ሉዑል ሥም ሰይመውት ሥራውን ጀመሩ፤ ሆቴሉ ያለበት ቦታ የመንገደኞች መናኸሪያ ያለበት ስለነበር ገበያውም እየተበረታታ ብር ያገኙበት ጀመር።

1999 ዓ.ም ወርኃ ታህሳስ ላይ የአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ጭምር የሚሳተፉበት የአንድ ወር ስልጠና ስለነበር ምግብ ለሚያቀርቡ ሆቴሎች ጨረታ ይወጣል። እርሳቸውም በብዙ ፍትጊያ የጨረታው አካል ሆነው ምግብና ለስላሳ መጠጦች ማቅረብ ጀመሩ። ለአንድ ሰው ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና ሁለት ለስላሳ ብሎም በሣምንት አራት ቀን ሥጋ ወጥ ለማቅረብ በአንድ ሰው በቀን 29 ብር ጨረታ ለ340 ሰው ማቅረብ ጀመሩ። ለዚሁ ሥራም 30 ሰዎችን ቀጠሩ። በዚህም የምገባ እውቅና አተረፉ።

ሁለተኛ ዙርም ተመሳሳይ ጨረታ ወጣ። በዚህ ጊዜ ግን እሳቸውን ለማግለል መፈለጉን አቶ መኮንን ያስታውሳሉ። እሳቸውም ይህን ስለተረዱ ቀድሞ ለአንድ ሰው በቀን 29 ብር ይጠይቁ የነበረውን 25 ብር ቁርስ ፣ምሳ እራት አቀርባለሁ ብለው ጨረታ አስገቡ፤ ብቸኛም

**ህዳር 1996 ዓ.ም መምህራን ሙሉ ቀን መሥራት አለባችሁ የሚል አቅጣጫ ወረደ። ይህ ከሥራቸው ጋር አልስማማ አላቸው። በመጨረሻም ቤተሰባቸውን አሳምነው መምህርነቱን ትተው የእንጨት ሥራቸውን አጥብቀው ያዙት**

ሆነው አሸነፉም። በዚህም ከ1000 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ምግብ ማቅረቡን ተያያዙት።

ይህን ስራቸውን ለማጠናቀቅ አራት ቀን ሲቀራቸው ሌላ ችግር የገጠማቸው አቶ መኮንን፣ በሴራ ሥራውን እንዲያቋርጡ መደረጉን ይናገራሉ። ፖለቲካዊ ጫናም ተደርጎባቸው ሥራውን ትተው ወጡ። 1000 ለሚሆኑ ሰዎች ተዘጋጅቶ የነበረው እንጀራም ተረካቢ አጣ። እንጀራውን ቤተክርስቲያን አካባቢ ወስደው ለአቅመ ደካሞች ሰጡ።

የሆነው ሆኖም በሥራው 400ሺ ብር አግኝተው ስለነበር ለሥራ መንቀሳቀሻ አነስተኛ የቤት መኪና በ110ሺ ብር ፣ የመኖሪያ ቤት ደግሞ በ105ሺ ብር ገዙ። ቀሪውን ደግሞ ለባለቤታቸው ስቴሽሪና መሸጫ ሱቅ ለመክፈቻና ለሌላ ዓላማ አዋሉት። መኪናዋም ለሠርግ መከራየት ጀመረች።

በ2000 ዓ.ም ደግሞ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ የኮምቦልቻ ካምፓስ ዘይት፣ ስጋ እና ሌሎች ግብዓቶችን ማቅረብ ጀመሩ። ዩኒቨርሲቲው በ2001 ዓ.ም እንጀራ ለሚያቀርብ ያወጣውን ጨረታ አሸንፈው ለ3000 /ሶስት ሺ / ሰዎች እንጀራ ማቅረብ ጀመሩ፤ በዚህም ጥሩ ገቢ አገኙ። የሆቴላቸውንም ሥራ እየሠሩ መሰል ግዙፍ ድርጅቶችን እየተዋወቁ የሥራ መስካቸውንና የገንዘብ አቅማቸውን አጎለበቱ።

በ2002 ዓ.ም በጨረታ አሸንፈው እየሠሩበት ያለውን ብሄራዊ ሆቴል ሸጡልኝ ብለው ጠየቁ። 400ሺ ብር መግዛት ትችላለህ ቢባሉም፤ አቅማቸው ስላልፈቀደ ቀንሱልኝ በሚል ደጅ መጥናት ጀመሩ። ይህ ግን ሳይሳካ ቀረ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ በከተማዋ ጣና የትራንስፖርት ድርጅት ይዞት የነበረው ሰፊ ቦታ ከከተማ አስተዳደሩ ገንዘብ ስለነበረበት ጨረታ ወጣ። አቶ መኮንንም በጨረታው ተሳትፈው በ250ሺ ብር 4000 ካሬ ሜትር የሚጠጋ መሬት በርካቶችን አሸንፈው ቦታውን የራሳቸው አደረጉ። ከባንክም ተበድረው የበለጠ ሥራ ይሰሩበት ጀመር። በሂደትም ይህን ቦታ አፀዱት፤ ትንሽ ግንባታ አካሄዱበት። ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፈው በዚህ ቦታ ላይ በኮኮብ ደረጃ የሚመጥን ሁኔታ ሆቴል አስገነቡበት።

ሆቴሉን ‹‹ልዑል መኮንን›› የሚል ስያሜ ሰጡት። ለሆቴሉ የሚመጥኑ ግብዓቶችን ለመግዛት ወደ ቻይና ተጉዘው ከ45 ቀናት በላይ ቆይተው እያንዳንዱን ግብዓት አሟልተው ተመለሱ። ሆቴሉም አስፈላጊዎቹ ሁሉ ተሟልተውለት ስራውን ጀመረ። ይህ ሆቴል የብዙዎች የዓይን ማረፊያ፣ የውጭ ዜጎችም ምርጫ ሆነ። በእርግጥ ሆቴሉ ሲገነባ በ10 ሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር ከባንክ ተበድረዋል። ሆቴሉ ከ100 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ፈጥሯል።

ሆቴሉ ሲመረቅ ግን ባለስልጣናት ወይንም ታዋቂ ግለሰቦች እንዳልጠሩ ነው አቶ መኮንን የሚናገሩት። ገንዘቡን ያገኘሁት፤ ለዚህም ደረጃ የደረስኩት ከደሴ፣ ኮምቦልቻና አካባቢው ነዋሪዎች ጋር ሆኜ ነው፤ ማንኛውም ሰው መጥቶ መመረቅ ይችላል በሚል እሳቤ ነበር ይላሉ። እንዳሰቡትም በርካታ ሰዎች ሆቴሉን መረቁት። በኋላ ግን የወቅቱ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የነበሩት አቶ አገኘሁ ተሻገር ወደ ኮምቦልቻ ለሥራ በሄዱ ጊዜ በይፋ እንዲመርቁት ተደርጓል።

እነዚህ ሁነቶችና ሂደቶች አልፈው ስራቸውን ማቀላጠፉን ተያይዙት። ዳሩ ግን በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነትና በአካባቢው በተፈጸመው ወረራ ልዑል መኮንን ሆቴል ቀዳሚ ዒላማ ተደረገ፤ ቀደም ሲል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችና የሀገር መከላከያ መኮንኖች ያርፉበት ስለነበር ጭምር ነው ወራሪዎች ኢላማቸው ያደረጉት። በወረራው ከህንፃው በስተቀር ሆቴሉ ሙሉ ለሙሉ ተዘረፈ፤ ንብረቱ ወደመ።

አቶ መኮንን ሕይወታቸውን ለማትረፍ ወደ ሌላ ስፍራ ሸሹ። ከምቦልቻ በመንግስት ሀይሎች ነጻ ወጥታ ሁኔታዎች ሲረጋጉ እሳቸውም ወደ አካባቢው ተመልሰው ስራቸውን ያቀላጥፉት ጀመር። አቶ መኮንን ሆቴሉ ብዙ ጉድለቶች ቢኖሩበትም፣ ሰላም ከመጣ ዕዳው ገብስ ነው ብለው መትጋታቸውን ቀጥለዋል።

በጦርነቱ ብዙ ሚሊዮን ብር ያጡት አቶ መኮንን፣ መንግስት ጉዳዩን እንዲመለከተው በተደጋጋሚ እየጠየቁ መሆናቸውን ይናገራሉ። በተለይም ጉዳቱ የከፋ መሆኑን በመጥቀስም ባንኮችም የብድር አከፋፈልና ብድር ሥርዓቱን መከለስና መመልከት እንዳለባቸው ይጠይቃሉ። ይህም ሆኖ አሁንም በሥራቸው ላይ እየተጉ ነው።

አቶ መኮንን በዚህ ብቻ አላበቁም ። 35 ሚሊዮን በሚጠጋ ብር የገዙት የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አላቸው። ነገ የተሻለ እንደሆነም ይገልፃሉ። በአሁኑ ወቅት ከ120 ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስመንት እያካሄዱ ነው። በቀጣይም ብዙ ሥራ ለመሥራት ራእዩ አላቸው።

ከእንግዲህ በኋላ ለሀገሬ ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት አስባለሁ የሚሉት አቶ መኮንን፤ ብዙ ውድቀትና መነሳት ቢኖርም፣ ነገ የተሻለ ነገር አለ በሚል ፈተናዎችን አልፈዋል። በቀጣይ ግን ብዙ ያልማሉ፣ ይተልማሉ። በሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ሥራ ዕድል መፍጠር፣ ለመንግስትም ከፍተኛ ግብር ከፋይ መሆን ፈልገዋል። በኢንቨስትመንትም ቢሆን የሀገሪቱን ችግር የሚፈቱ ችግሮች ላይ መሳተፍ የሁልጊዜ ህልማቸው ነው።

በቀጣይ ግን ከሁሉም በላይ ስለሠላምና አንድነት መሥራት አለብን የሚለው ከእግር እስከ ፈረስ፣ ወታደርነት እስከ መምህርነት ከመምህርነትም እስከ ሚሊየነርነት የተጓዙት የረጅም ህልም ባለቤቱ የአቶ መኮንን ብርሃኑ መልዕክት ነው።

# ስፖርት





# የገና ጨዋታ ስፖርት ነው?

**ቦጋለ አበበ**



የገና ጨዋታ ስፖርት ነው አይደለም? የሚሉ ክርክሮች በብዙዎች ዘንድ ይነሳል። መልሱ አጭር ነው፣ የገና ጨዋታ ስፖርት ነው። ስፖርት ለመባልም አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ በኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን እውቅና ተሰጥቶት ውድድሮች ይካሄድበታል። የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ባህል ማዕከል ጋር በሀገሪቱ 2 መቶ 93 በህላዊ ስፖርቶች ላይ ጥናት አካሂዶ ነበር። ለአስራ አንዱ በተካሄደላቸው ጥናት ሕግና ደንብ ወጥቶላቸዋል። ከነዚህ ውስጥ የገና ጨዋታ አንዱ ነው።

በ2006 ተከልሶ በተዘጋጀው የባህልና ስፖርት ሰነድ መሠረት የገና ጨዋታ ወደ 7 የሚደርሱ ሕግና ደንቦች ተዘጋጅቶለታል። አቶ ዓለም እዳብራሩት የተዘጋጀው ሕግና ደንብ የገና ጨዋታ ባህላዊ ይዘቱን ሳይለቅ በሕግና ደንብ እዲመራ የሚያደርግ ነው።

የገና ጨዋታ በዓለም ላይ በብዙዎች እንደሚወደደው የእግር ኳስ ጨዋታ የተመልካቾችን ቀልብ የሚስብ አዝናኝ ጨዋታ ነው። ታዲያ በገና ጨዋታ ደንብ መሠረት የመጫወቻ ሜዳው ምን መሆን እንዳለበት፣ የተጫዋቾች ብዛት፣ የዳኞች ብዛትና ኀላፊነት፣ ውጤት አሰጣጥና ሌሎች አስፈላጊ ደንቦች የተካተቱለት ነው።

ፍጥነትን፣ አካላዊ ጥንካሬንና ትንፋሽን የሚጠይቀው የገና ጨዋታ ሳቢና ተወዳጅ እዲሆን ልክ እንደ እግር ኳስ ጨዋታ ደንቦቹ ይመሳሳላሉ። በመጀመሪያ ለገና ጨዋታ ሁለት ተጋጣሚ ቡድኖች ያስፈልጋሉ፣ ለጨዋታ የሚስፈልገው ሜዳም በደንብ ለጨዋታ ዝግጁ ይሆናል።ልክ እንደ እግር ኳስ ሜዳ የጎል ጠባቂ፣ የተከላካይ የአጥቂ፣ የማዕዘን መምቻ በኖራ ይሰመራል። የሜዳ ስፋቱ ደግሞ ርዝመቱ 90 ሜትር ጎኑ 50 ሜትር የሆነ ሜዳ ያስፈልጋል።

በዚህ ሜዳ ውስጥ ለመጫወት ሁለቱ ተጋጣሚ ቡድኖች 15 ተጫዋቾችን ያቀርባሉ፣ አስሩ ሜዳ ውስጥ ገብተው የሚጫወቱ ሲሆን አምስቱ በተቀያሪ ወንበር ይቀመጣሉ። ጨዋታውን የሚመራ የመሃል ዳኛ፣ ዳኛውን የሚያግዙ መስመር ዳኞች እዲሁም ተቀያሪ ተጫዋቾችን የሚቀይሩ ዳኞችም የገና ጨዋታ ተሳታፊዎች ናቸው።

የገና ጨዋታን ለመጫወት ሩር እየተባለች የምትጠራ ድቡልቡል መጫወቻ ያስፈልጋል። ክብደቷ እስከ 5 መቶ ግራም የሚመዝን ከእንጨት፣ ከጠፍር አሁን አሁን ደግሞ ከፕላስቲክ ይዘጋጃል። ድቡልቡል መጫወቻ ወይም ሩሩን ለመምታትና ወደ ተቃራኒ ቡድን ግብ ለማስገባት ልክ እደ ማንኪያ ቅርፅ ያለው ከ1ሜትር የማይበልጥ ቁመት ያለው የገና ዱላ ያስፈልጋል። የገና ዱላው ለሁሉም ተጨዋቾች በእኩል ቁመት የተዘጋጀ ሆኖ ይታደላል።

ጨዋታው ከመጀመሩ አስቀድሞ ልዩነት አለመኖሩን ዳኛው የማረጋገጥ ኀላፊነት አለበት። ጨዋታው ሲጀመር ሁሉም ተጫዋቾች ተነፋነፍ የሚባለውን ባህለዊ ልብሳቸውን ለብሰው ቦታ ቦታቸውን ይይዛሉ አጥቂው ከአጥቂ፣ ተከላካይ እዲሁ በቦታው፣ በረኛውም በተጠንቀቅ በቦታው ይሰየማል።

ጨዋታውን የሚያስጀምሩት ዳኛ ሶስት "ጊዜ እዚህ እሩር እዛ ገና " ካለ በኋላ ጨዋታው ይጀመራል። በጨዋታው ሕግ መሰረት ሩሯን በእግርና በእጅ መንካት ነጥብ የስቀንሳል። ለ30 ደቂቃ በመጀመሪያው ምዕራፍ ይጫወታሉ ለ10 ደቂቃ እረፍት ከወሰዱ በኋላ የጨዋታ ሜዳ ተቀያይረው ሁለተኛ አጋማሽ ጨዋታቸውን ያካሂዳሉ።ጨዋታው ለዋንጫ ወይም ለደረጃ ከሆነ ቡድኖቹ ካልተሸናነፉ ተጨማሪ ደቂቃ እዲጫወቱ ይደረጋል። በዚህም ካልተሸናነፉ የቅጣት ምት እየተሰጣቸው እስኪ ሸናነፉ ድረስ ይጫወታሉ።

የገና ጨዋታ በሀገራችን ባህላዊና ሀይማኖታዊ ይዘት ያለው፣ ከጥንት ጀምሮ የነበረ ጨዋታ እንደሆነ መዛግብት ያስረዳሉ። መምህር ካህሳይ ገ/እግዚአብሔር የተባሉ የታሪክ ተመራማሪና ደራሲ፣ ስለ ገና ጨዋታ ታሪካዊ አጀማመር ሁለት ትውፊቶች ተደጋግመው እንደሚነገሩ ይገልፃሉ። ጌታ ሲወለድ እረኞች ከመላዕክት ጋር አብረው እንደዘመሩና በወቅቱም የገና ጨዋታ መጫወት እንደጀመሩ አንደኛውን ትውፊት በመጥቀስ ያስረዳሉ።

ሁለተኛው ትውፊት ደግሞ ከሰብዓ ሰገሎች ጋር የሚገናኝ ነው። ንጉስ ሄሮድስ የሚባለው የዘመኑ ንጉሥ አዲስ የሚወለደው ህፃን የበለጠ ዝናና ክብር እንደሚያገኝ የሰማው ትንቢት ስላስደነገጠው በዚያን ጊዜ የተወለዱ ወንድ ህፃናት በሙሉ እንዲገደሉ ትዕዛዝ ሰጥቶ እያሳደደ ያስገድል እንደነበር ይወሳል። ሄሮድስ ታዲያ ጌታ ሊወለድ መሆኑ ተነግሮት ስለነበር የት እንደሚወለድና ስለ አጠቃላይ ሁኔታው በቅርበት ለማወቅ በመፈለጉ አንድ ሰላይ የሰብዓ ሰገሎች ዓይነት ልብስ አስለብሶ፣ ከእነሱ ጋር እንዲቀላቀል ይልካል። ሰላዩ ከሰብዓ ሰገሎች ጋር ተቀላቅሎ ጌታ ወደሚወለድበት ሥፍራ ሲጓዙ፣ ይመራቸው የነበረው ኮከብ ድንገት ቀጥ ይላል። ይኼኔ ተጠራርተው መሃላቸውን ሲፈትሹ፣ ሰላዩን እንዳገኙት ይኸው ትውፊት ያስረዳል። ከዚያም ሰብዓ ሰገሎቹ ሰላዩን ይገድሉና ራሱን ቆርጠው እንደ አሁኑ የገና "እሩር" እየተቀባበሉ ተጫወቱበት ይላል - ሁለተኛው ትውፊት። ከዚያም በመነሳት የገና ጨዋታ ተፈጠረ ይላሉ፣ የታሪክ ተመራማሪው።

ከዚያን ጊዜ አንስቶ ከትውልድ ትውልድ እየተቀባበለው፣ እስከ አሁን የቀጠለው የገና ጨዋታ፣ በየዓመቱ በታህሣሥ ወር በተለይ በኢትዮጵያ የገጠሩ ክፍል እረኞች በድምቀት ይጫወቱታል። በአብዛኛው ጨዋታው ወሩ እንደገባ የሚጀመር ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ከታህሳስ ወር አጋማሽ ጀምሮ እንደሚጧጧፍ ይታወቃል።

የገና ጨዋታ አሁን በዘመናዊ መልኩ በከተሞች ከምናየው ይለያል። በስፖርታዊ ውድድር ውስጥ በገባው ዘመናዊ የገና ጨዋታ ህግ መሰረት፣ ዱላውን (ገናውን) ወደ ላይ ማንሳት አይቻልም። በጥንታዊው ወይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በሚደረገው የገና ጨዋታ ላይ ግን እንደተፈለገው በማንሳት፣ ሩሯን (ጥንጓን) አክርሮ መለጋት ይቻላል።

ሌላው ደግሞ በዘመናዊው የገና ጨዋታ ስፖርት፣ ሩሯ የምትገባበት (የምትለማበት) ሥፍራ እንደ እግር ኳስ የግብ ሥፍራ ያለው ነው። በጥንታዊው ጨዋታ ግን የገና ጨዋታው የሚካሄድበት ሜዳ ወይም የእርሻ ማሣ፣ ሁለቱም ጫፎች የግብ ወይም የመልሚያ ቦታዎች ናቸው። ከሜዳው ወይም ከማሳው ስፋት የተነሳም ተጫዋቾቹ እንደ ልባቸው እየሮጡ ይጫወታሉ። ጨዋታው በውጤት አሊያም በሽንፈት እየታጀበ ይቀጥላል።

መልካም የገና በዓል!


## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር: -SSNT-T357

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ አዲስ አበባ ቦሌ ለሚገነባው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና መሥሪያ ቤት የዲዛይን ግምገማና ማፅደቅ፣ የግንባታ ቁጥጥር እና የኮንትራት አስተዳደር የማማከር አገልግሎት ስራን ማሰራት ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም በደረጃ አንድ እና ከዚያ በላይ ተዛማጅነት ባለው ስራ አማካሪዎች ሆነው የተመዘገቡ እና የ2015 ዓ.ም የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ተመዝጋቢ የሆነ እና የዘመኑን ግብር የከፈለ ተጫራች በጨረታው መሳተፍ ይችላል፡፡

ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት የስራ ቀናት በአቅራቢያቸው በሚገኝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ የማይመለስ ብር 100.00/ አንድ መቶ ብር/ በሂሳብ ቁጥር 1000006958277(E-99) ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ጨረታ ቁጥር SSNT-T357 በሚል ገቢ በማድረግና የከፈሉበትን የገቢ ደረሰኝ ኮፒ (Deposit Slip Copy) ስካን በማድረግ ከታች በተጠቀሰው የኢሜይል አድራሻ በመላክ የጨረታ ሰነዱን በኢሜይል ማግኘት ይችላሉ፡፡ የጨረታ ማስከበሪያ ሀምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር (50,000.00 የአሜሪካ ዶላር) ወይም ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ባንክ ጋራንቲ ማስያዝ ይኖርባቸዋል:: አሸናፊው ከተለየ በኋላ በጨረታው ለተሸነፉት ተጫራቾች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ወዲያውኑ ተመላሽ ይሆናል::

ተጫራቾች በጨረታው ደንብ መሠረት የመጫረቻ ሰነዳቸውን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ስትራቴጂክ ሶርሲንግ ነን ቴክኒካል ክፍል እስከ ጥር 12 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 9:00 ሰዓት ድረስ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቦሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና መሥሪያ ቤት ግቢ ውስጥ በተመሳሳይ ቀን በ9:30 ሰዓት ይከፈታል፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ፡-**

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ**
**ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ዋና መስሪያ ቤት**
**ስትራቴጂክ ሶርሲንግነን ቴክኒካል ክፍል**
**ስልክ ቁጥር፡- 011-517-42-58**
**ኢ-ሜይል: TessemaH@ethiopianairlines.com**

አየር መንገዱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር፡-SSNT-T359

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ GSE/GTV ሞተር እና የተለያዩ የሜካኒካል ክፍሎች የጥገና እና የማሻሻያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ድርጅቶችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ በረጅም ዓመት ኮንትራት ለማሰራት ይፈልጋል::

ስለሆነም ከዚህ በታች የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡

1. ለስራው ብቁ የሆኑ ተጫራቾች በሙያ ዘርፉ "በትንሹ አምስት (5) ዓመት የሰሩ" በሙያ ዘርፉ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ተመዝጋቢ የሆኑ፣ የግብር ከፋይ ሰርተፊኬት ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና በመንግስት ጨረታዎች ለመሳተፍ ፈቃድ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት የስራ ቀናት በአቅራቢያቸው ከሚገኝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ የማይመለስ 100.00 ብር/አንድ መቶ ብር/ በሂሳብ ቁጥር 1000006958277(E-99) ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ጨረታ ቁጥር SSNT-T359 በሚል ገቢ በማድረግና የከፈሉበትን የገቢ ደረሰኝ ኮፒ (Deposit Slip Copy) ስካን በማድረግ ከታች በተጠቀሰው የኢሜይል አድራሻ በመላክ የጨረታ ሰነዱን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ የእቃ ግዢ ክፍል በኢሜይል ማግኘት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ / ባንክ ጋራንቲ ማስያዝ ይኖርባቸዋል:: አሸናፊው ከተለየ በኋላ በጨረታው ለተሸነፉት ተጫራቾች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ወዲያውኑ ተመላሽ ይሆናል፡፡
4. ተጫራቾች በጨረታው ደንብ መሠረት የመጫረቻ ሠነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ የእቃ ግዢ ክፍል እስከ ጥር 17 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 8:30. ሰዓት ድረስ በአካል ወይም ከታች በተጠቀሰው ኢሜል አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቦሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሠራተኞች ካፍቴሪያ ውስጥ በተመሳሳይ ቀን በ 9:00 ሰዓት ይከፈታል፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ:-**

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና መስሪያ ቤት**
**ስትራቴጂክ ሶርሲንግ ክፍል**
**ስልክ ቁጥር: +251115174028**
**ኢሜይል: WoldeM@ethiopianairlines.com**

አየር መንገድ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::